ላይ ነው። ይህ ጉብታ አባ አየለ የተባሉ መነኩሴ የሚኖሩበት ክብ የሣር ክዳን ቤት ነበረበትና ዙሪያውን በረንዳ ተጨምሮለት መቃኞ[86] ሆኖ ተቀደሰበት። የዚህ በዓል የማኅሌቱ ምራት ለራጉኤሎች፣ ቅዳሴው ለእንጦጦ ማርያም ካህናት ስለተሰጠ በዋዜማው ወርደን ስናገለግል አደርን። በማግሥቱም ጧት አቡነ ማቴዎስና እጨጌ ወልደ ጊዮርጊስ መጥተው አዲሱን ቤተ ክርስቲያን ባረኩ። ቀጥሎም ልጅ ኢያሱና ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ መጥተው ታቦት አንግሠውና በዓሉን አክብረው ተመለሱ። በዚህ ቀን ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ (ልጅ ኢያሱ ባሉበት) በአዳራሻቸው ለካህናት ግብር አድርገው ዋሉ። ግብዣውም በዚያ ቀን ለእርሳቸው ተሰጠ። ከዚህም በኋላ በሰጣቂው ዓመት ጥቅምት 27 ቀን 1904 ዓ.ም. የመድኃኔ ዓለም በዓል በዚያው ቦታ እንደገና በታላቅ ክብር ተከበረ። በዚያ ቀን ስለ በዓሉ ክብር ነጋሪት ተመትቷል፣ መድፍም ተተኩሷል።



20 ቀጨኔ መድኃኔ ዓለም

ልጅ ኢያሱ የመድኃኔ ዓለምን ታቦት ለመትከል የፈለጉበት ምክንያት፣ የተወለዱበት ቀን ጥር 27 1889 ዓ.ም. የመድኃኔ ዓለም ዕለት ነበርና የልደታቸው መታሰቢያ እንዲሆን በማሰብ መሆኑን ሰምቻለሁ። የክርስትና ስማቸውም ክፍለ ያዕቆብ ነው።

[86] ትልቅ ቤት ከመሠራቱ አስቀድሞ ለጊዜው ማገልገያ እንዲሆን የሚሠራ ትንሽ ቤት።

# ምዕራፍ 11

## 1904 ዓመተ ምሕረት

**ስለ ኪዳነ ምሕረት ጠበል፣ ናዝራዊና ባሕታዊ አስደንጋጭ ስብከት ስለመስበካቸው፣ የኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ስለመተከሉ፣ ወደ አዲስ አበባ ስለመውረዴ፣ በአዲስ አበባ ሥላሴ ሳለሁ፣ ሥራ ለመያዝ ስለመሞከሬ**

## ስለ ኪዳነ ምሕረት ጠበል

አባ ምትኬ የተባሉ ሰው ከእንጦጦ በስተምሥራቅ በኩል በሚገኝ ሸለቆ ውስጥ (አሁን ገዳመ ኪዳነ ምሕረት ከተባለው ስፍራ ላይ) ሕሙማንን የሚፈውስ ጠበል አገኘሁ ብለው ከሁለት ዓመት በፊት ተናግረው ስለነበረ፣ የእንጦጦ ማርያም ካህናት ወደዚያ ስፍራ ወርደው ጸሎት አድርሰው መስቀል ተከሉበትና ሕዝብ ይጠመቅበት ጀመር። አባ ምትኬ የእንጦጦ ማርያም ቄሰ ገበዝ የነበሩ የጉጃም ሰው ናቸው።

አባ ምትኬ ከዚያ ስፍራ ጥንት ታቦት እንደነበረበትና ጠበል መኖሩም በራእይ ተገለጸልኝ ሲሉ ተናገሩ። በእውነትም በጠበሉ ራስጌ ያለው ጉብታ ሲቆፈር የብረት መስቀልና የብረት ጽና[87] ተገኘ። ቀጥሎም የጥንቱ ቤተ ክርስቲያን የመሠረቱ ግንብ ተገኘ። ከግራኝ ወረራ በፊት በዚያ ቦታ ላይ የማርያም ቤተ ክርስቲያን ነበረበት። ደግሞም የመናገሻው መናኒ አባ ኤልያስ ወደዚህ ገዳም እየመጣ ጸሎት ያደርስ ነበር ይባላል።

ስለ አባ ኤልያስ የሰማሁትም ታሪክ ቀጥሎ ያለው ነው። ይህ ሰው በግራኝ ጊዜ የነበረና በ400 ዓመት ዕድሜው ኅዳር 6 ቀን 1874 ዓ.ም. ሞቶ መናገሻ ተራራ ላይ የተቀበረ ነው። ታሪኩም እንዲህ ሲል ይቀጥላል። አባ ኤልያስ የቤተ መንግሥት ተወላጅነት ያለው ሰው ነው። የተወለደበትም ዘመን በ15ኛ ው ምዕት በሦስተኛው ሩብ ላይ ነው ይባላል። ግራኝ ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ በእምላክ ጸጋ ከተመረጡ ደጋግ ሰዎች ጋር በእግዚአብሔር ኃይል ተሰውሮ መናገሻ ከተራራው ላይ ቀረ። በግራኝ ጊዜና ኋላም በኦሮሞዎች ወረራ ጊዜ አንዳች ጉዳት አልደረሰበትም። ከመናገሻም ወደዚህ ገዳም (ገዳመ ኪዳነ

[87] ከሸክላ ወይም ከብረት የሚሠራ የዕጣን ማጠኛ። በቅዳሴ ጊዜ ወይም ጸሎት ሲደረስ ቄሱ መንበሩንና ሕዝቡን ያጥናል።

ምሕረት) እየመጣ ሱባዔ[88] እየገባ ጸሎት ያደርስ ነበር:: ኦሮሞዎች አያና (ውቃቢ) ኢያሉ ስለሚያምኑበት ምንም ጉዳት አያደርጉበትም ነበር ይባላል::

አባ ኤልያስ በሞተበት ቀን ከዋክብት በሰማይ ላይ ሲበታተኑ ታዩ:: የተጉለቱ አባ በላይነህም በከዋክብት ላይ የተደረገውን ምልክት አይተው የአባ ኤልያስን መሞት ተረዱትና ወደ መናገሻ ቢመጡ ሞቶ ተቀብሮ አገኙት ይባላል:: አባ በላይነህ በአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የነበሩና ከአባ ኤልያስ ጋር ግንኙነት ያላቸው የበቁ[89] ሰው ነበሩ:: የነበሩበትም ዘመን በ19ኛው ምዕት ውስጥ ነው::

ስለ አባ ኤልያስ የሰማሁት ታሪክ እስከዚህ ድረስ ነው:: ታሪኩን የሰማሁትም ከመልአከ ብርሃን አምባዬ ወልደ ያሬድ ነው:: እኚህ የታሪኬ ባለቤት ይህን በጻፍሁበት ጊዜ በሕይወት ያሉ ናቸው:: አባ በላይነህን እርሳቸው ራሳቸው ስለሚያውቋቸው ስለ እርሳቸው ብዙ ነገር ተርከውልኝ ነበር:: ግን እዚህ አልጻፍሁትም::

ስለ ከዋክብቱ መበታተን (መራወጥ) አባቴ አለቃ ወልደ ቂርቆስ በዓይኔ አየሁ ብለው የነገሩኝንም እጨምራለሁ:: ቃሉም ይህ ነው::

"በኅዳር 6 ቀን 1874 ዓ.ም. ጐንደር ከተማ ላይ ነበርሁ" ይላሉ:: "በዚያ ሌሊት ከዋክብት በሰማይ ላይ ሲራወጡ (ሲበታተኑ) አየሁ፣ ጓደኞቼም አይተዋል:: እኛም ምን ነገር ይሆን ብለን ተደነቅን:: ምክንያቱንም ልናውቅ አልቻልንም:: ከአራት ዓመት በኋላ በ1878 ዓ.ም. ወደ ሸዋ ተመልሼ ገባሁ:: በዚህ ጊዜ የአባ ኤልያስን መሞትና በዚያች ሌሊት የከዋክብቱን መራወጥ፣ አባ በላይነህም በከዋክብቱ ምልክትነት የአባ ኤልያስን መሞት እንዳወቁ ታሪኩን ከወዳጆቼ ከነአለቃ ወልደ ያሬድ[90] ሰማሁ:: ይህም የሆነው በኅዳር 6 ቀን 1874 ዓ.ም.

---

[88] ለጸሎት ከሰው መለየት ነው:: ሱባዔ ሰባት ቀን ነው፣ ሊረዝምም ይችላል::

[89] ብቃት ማለት ፍጹምነት ነው:: ሕይወታቸውን ለእውነት አሳልፈው ሰጥተው፣ ዓለማዊ ፍላጎታቸውን አሸንፈው፤ ሕይወታቸውን በእምነት፣ በተስፋና በፍቅር መልተው የተጓዙ ከአምላክ ጋር ይገናኛሉ:: ይህን ጸጋ የተጎናጸፉ የበቁ ይባላሉ::

[90] አለቃ ወልደ ያሬድ በ19ኛው ምዕት የኖሩ የተጉለት ተወላጅ ናቸው:: አባትየው ኤሳርዮን የተባሉ ካህን ነበሩ:: የዜማ መምህር ስለነበሩ ነጭ ገደል በኢታ "ተጉለቴ ዜማ" የሚባለውን ያስተምሩ ነበረ:: ልጃቸውን ወልደ ያሬድን ፊደል አስቈጥረው እስከ ዜማ ያለውን ትምህርት አስተምረዋቸዋል:: ወልደ ያሬድ ከዚህ በኋላ ወደ ዋድላ ሄደው ቅኔ ከነአገባቡ አጠኑ:: በዚህ ትምህርት በአስተማሪነት ተመርቀው ወጥተው አንኮበር ገቡ:: እዚያ ባንድ በኩል ቅኔ እያስተማሩ በሌላ በኩል ደግሞ ብሉይ ከአለቃ ገብረ ክርስቶስ ዘንድ ይማሩ ነበር:: ይህን እንዳጠናቀቁ እዚያው አንኮበር ወደ አለቃ ምላት ተዛውረው ፍትሐ ነገሥትን ቀጸሉ:: እነዋሪ ላይ ማርያም ታቦት ስትተከል አለቃ ወልደ ያሬድ ከመጀመሪያዎቹ ተክለኞች አንዱ ነበሩ:: እዚያ አስተዳዳሪው አለቃ ኪዳነ ወልድ ስለነበሩ አለቃ ወልደ ያሬድ የኢጋፋሪነት ሙያ ነበራቸው:: ከዚህ በኋላ አንኮበር ጊዮርጊስን አልቅና ተሾሙ:: የአዲስ አበባ መካነ ሥላሴ (በኋላ መንበረ ጸባኦት) በ1882 ዓ.ም. ሲተከል አለቃ ወልደ ያሬድ ሹመቱ ተሰጣቸው:: የመጀመሪያ አለቃ እርሳቸው ናቸው:: በዚህ ሹመታቸው ለረጅም ጊዜ ቈይተዋል:: በጥር 8 1917 ዓ.ም. ዐረፉ:: ምንጭ - ሥርግው ሀብለ ሥላሴ፣ የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት:: እና የብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ያልታተመ ጽሑፍ::



መሆኑን ስለነገሩኝ እኔም ያየሁት በዚያው ዕለት መሆኑን ተረዳሁት" ብለው ነግረውኛል:: እንግዲህ አንባቢው ስለ አባ ኤልያስና ስለ አባ በላይነህ ታሪክ የፈቀደውን ያትት፣ የኔ ሥራ የሰማሁትን ነገር በሰማሁት ዓይነት ማቅረብ ነው::

## ናዝራዊና ባሕታዊ አስደንጋጭ ስብከት ስለመስበካቸው

በዚህ ዘመን ናዝራዊና[91] ባሕታዊ በከተማ ውስጥ ከመቼውም ይልቅ በብዛት ይታዩ ነበር:: ናዝራዊው ጎፈሬውን አጎፍሮ ባለ አንካሴ የብረት መስቀሉን ተሸክሞ፣ ባሕታዊው ዳባ ለብሶና ጢሙን አንገዋርጎ በየበዓል ስፍራና በየአደባባዩ እየዞረ ይሰብክ ጀመር:: ስብከቱም "መዓት መጣብህ፣ ጉድ ፈላ፣ እግዚኦ በል፣ ንስሐ ግባ፣ ምጽዋት መጽውት" የሚል ነው:: በተጨማሪም ምጽዓት ደረሰ፣ ዓለም ልታልፍ ነው ሲል ባሕታዊና ናዝራዊ አስደንጋጭ ወሬ ለሕዝቡ አፈሰሱለት:: በዚህ ዓመት የስቅለት በዓል መጋቢት 27 ቀን ፋሲካም መጋቢት 29 ቀን ላይ ውሎ ነበር:: እንዲህ ሆኖ ሲውል ምጽዓት ይሆናል የሚል ወሬ ድሮም ነበር:: ይህ ሁሉ ተጨመረና ሕዝቡን ከሥጋት ላይ ጣለው:: የዋሁ ሕዝብ ስብከቱን ሰምቶ በእውነት ደነገጠ:: ብልጡ ግን "ናዝራዊ ሲያታልል ነው" እያለ እያፌዘ ተቀመጠ:: እንግዲህ ስቅለትና ፋሲካ ደረሰ፣ ነገር ግን ዓለም አላለፈችም:: ባሕታዊና ናዝራዊ ወዲያው ሌላ ዘዴ ፈጥረው "ሕዝቡ እግዚኦ ስላለ ምሕረት ወረደ" ብለው ሰበኩ:: እኔ በሕይወቴ እንደዚያ ዘመን ባሕታዊና ናዝራዊ በከተማ በዝቶ አይቼ አላውቅም::

አባቴ በዚህ ዓመት በበጋው ወራት ከጅሩ ወደ እንጦጦ መጡ:: የመጡበትም ምክንያት የተወሰደባቸውን የደብረ ሊባኖስ መሬታቸውን በፍርድ ለማስመለስ የተመቸ ሰዓት መሆኑን በማሰብ ነው:: ወዲያው አዲስ አበባ ወርደው ጉዳያቸውን ለዘመኑ ባለሥልጣን ለፊታውራሪ ጥላሁን አቀረቡ:: ጉዳዩን ለማቃናት ሲሉ የአድአ መሬታቸውን ለፊታውራሪ ጥላሁን ያወረሱትም በዚህ ዓመት ነው:: እንዲሁ ደግሞ የፊታውራሪ ጥላሁንን ማኅተም (ማዘዣ) ይዘው ከእኔ ጋራ ወደ ደብረ ሊባኖስ የወረዱትና የተመለሱት በዚሁ ዓመት ነበር (ገጽ 47)::

## የኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ስለመተከሉ

የእንጦጦ ማርያም ቄሰ ገበዝ አባ ምትኬ ከእንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በምሥራቃዊ ደቡብ በኩል በሚገኘው ሸለቆ ውስጥ ጠበል ማግኘታቸውንና በዚያው አጠገብ የጥንት ቤተ ክርስቲያን የመሠረት ግንብ መኖሩን በ1902

---

[91] ሰውነቱን ለእግዚአብሔር ስለት የሰጠ፣ ጠጕሩን እያጐፈረ፣ ሰንሰለትን በአንገቱ አጥልቆ በደረቱ እንደ አስኬማ የሚጠመጥም:: ምንጭ - ከሣቴ ብርሃን ተሰማ፣ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ::

ዓ.ም. ስለተናገሩ ሕዝቡ ይህን ወሬ ሰምቶ በጠበሉ እየተጠመቀ ከደዌው ይፈወስ ጀመር።

እቴጌ ጣይቱም ይህን ነገር በሰሙ ጊዜ በዚያ በጥንቱ ስፍራ ላይ በኪዳነ ምሕረት ስም ቤተ ክርስቲያን እንዲተከል ስለአዘዙ፣ የእንጦጦ ማርያም ካህናት ታቦተ ኪዳነ ምሕረትንና ንዋያተ ቅድሳት ይዘው በዓሉን አከበሩ። እኔም በዚሁ በዓል ከካህናቱ ጋር ነበርሁ። በዚያም ስፍራ ላይ የግድግዳና የሣር ክዳን መቃኞ ተሠራበትና ገዳመ ኪዳነ ምሕረት ተተከለበት። ቤተ ክርስቲያኑም ከዚህ በኋላ በየጊዜው እየተሻሻለ በሕንፃ ተሠርቷል።

## ወደ አዲስ አበባ ስለመውረዴ

በ1904 ዓ.ም. በሁዳዴ እንጦጦ ላይ የደብተርነቱን ግብር በአባቴ ስም ስገብር ነበርሁ። አንድ ቀን ርእሰ ደብር ምክሩ ወደኔ ቀረብ አሉና "እንግዲህ የምትገብረው በአባትህ ስም አይደለም፤ መሬቱ ለፊታውራሪ ጥላሁን ስለተሰጠ ስመ ርስቱ ተዛውሯል፤ ሆኖም ለፊታውራሪ ጥላሁን በቶፍነት ልትገብር ትችላለህ" ብለው እያዘኑ ነገሩኝ። እኔም ይህን ከሰማሁ በኋላ እንጦጦ ላይ በቶፍነት መኖርን ጠላሁ። አባቴም አዲስ አበባ ላይ ስለነበሩ ወዲያው ጠርተውኝ አዲስ አበባ ወረድሁ። እዚህ ላይ የእንጦጦ ኑሮዬ ተፈጸመ።

አባቴ በአዲስ አበባ ሥላሴ ካሉት መምህር ከአለቃ ለማ ጋር አገናኙኝና የቅኔ አገባብ ጀመርሁ። በምግብም ረገድ እንዳልቸገር ለዘመዶቻችን ለአለቃ ወልደ ያሬድና ለመልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ፣ ለልጅ ሥዩም ወልደ ያሬድ አደራ ብለው አገባጠሙኝ። እነዚህ ዘመዶቻችን ያደረጉልኝ እርዳታና ደግነት ብዙ ነው።

## በአዲስ አበባ ሥላሴ ሳለሁ

ከዚህ በኋላ በአዲስ አበባ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በደብተርነት ማገልገል ስለጀመርሁ ቀኝ ጌታ ወልደ ጊዮርጊስ አንድ ቶፍነት ሰጡኝ። በዜማና በቅኔ በቂ ሞያ ስለነበረኝ በቶሎ ለመታወቅ ረዳኝ። ስለ ትምህርቴም አለቃ ለማ ኃይሉ በጉባኤያቸው ላይ ለዘወትር የማይገኙልኝ ስለሆኑ ለሌቾኝና ወደ ግራ ጌታ ገብረ መድኅን ተዛውሬ የቅኔ አገባብ እቀጽል ጀመር። ግራ ጌታ ገብረ መድኅን በቅኔ የተመሰገኑ ሊቅ ናቸው። ከደቀ መዛሙርታቸውም መካከል ቅኔ በጉንጬ ሀብተ ማርያም የቅርብ ወዳጅ አድርጎኝ ነበር። እንዲሁም በዚያ ጊዜ ከነበሩት የቅኔ ትምህርት ጓደኞቼ ዕውር ገብረ ሚካኤልንና ዲያቆን ሰይፉን ስለ ፍቅራችን አስታውሳቸዋለሁ።



## ሥራ ለመያዝ ስለመሞከሬ

በዚህ ጊዜ በዕድሜ ስለጎለመስሁ ለመጪው ኑሮዬ የሚሆን ዘላቂ ሥራ ለመፈለግ ምኞት ተነሣሣብኝ። ስለዚህም አንድ ሥራ ለመያዝ በየጊዜው በሦስት መንገድ ፈትኜ ነበር፣ ሆኖም አልተሳካልኝም።

አንደኛ፣ አዲስ አበባ ቂርቆስ በደብተርነት ትክለኛ ለመሆን እኔና ሦስት ጓደኞቼ (እነርሱም ትሳብእተ ወልድ አግዴ፣ አስፋው አንዳርጌ፣ ይፍሩ፣ የሚባሉ) ወደ ቂርቆስ ሄደን ጥያቄ አቀረብን። ነገር ግን የደብሩ ሹም አለቃ ጠብቄ "ቦታ የለም" ብሎ መለሰን።

ሁለተኛ፣ ልጅ ኢያሱ በተከሉት በመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በደብተርነት ለመተከል ከጓደኛዬ ከመርሐ ጽድቅ ፈለቀ ጋር ሄደን ጠየቅን፣ በዚያ ጊዜ አለቃው አባ ወልደ ጊዮርጊስ የተባሉ የጐጃም ሰው ሲሆኑ አጋፋሪውም ግራ ጌታ የሻነው ይባላሉ። እያንዳንዳችን ሦስት ሦስት ብር እንድንከፍል ተጠየቅን። ይኸውም የመዝገብ መጻፊያ የሚሉት ነው። በእውነቱ ግን ለአለቃውና ለአጋፋሪው የሚሰጥ ጉቦ ነበረ። ለአለቃው ሁለት ብር ለአጋፋሪው አንድ ብር ካልተሰጠ በቀር ትክለኛ ሆኖ መጻፍ አይቻልም ነበርና። ጓደኛዬ መርሐ ጽድቅ ሦስት ብር ከፈለና በትክለኛነት ተጻፈ። እኔ ግን ሦስት ብር ስላጣሁ ተመለስሁ። እኔ ለደጅ ጥናት በሄድሁበት ጊዜ ታቦቱ ከዚያ ከጉብታው ስፍራ ተዛውሮ በራስ መኰንን ግቢ አጠገብ በአንድ የግድግዳ መቃኞ ውስጥ ነበረ። መቃኞውም በለጣቂው ዓመት በጥቅምት 27 ቀን በድንገት ስለተቃጠለ ወደ ቀጨኔ ተሻግሮ በአዛዥ መሸሻ ተወንድ በላይ ቤት ውስጥ መግባቱን አስታውሳለሁ።

ሦስተኛ፣ በልጅ ኢያሱ ግቢ በአሽከርነት ደንብ ለመጻፍ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሄጄ አንድ ሌሊት በግቢአቸው አደርሁ። ይህን ሥራ የጠቆመኝ ዳመና ሞላ የተባለ የጅሩ ጓደኛዬ ሲሆን እሱም እንደዚሁ ለመጻፍ አብሮኝ ነበረ። አዲስ አሽከር እየጻፈ የሚቀበለው ሹም አጋፋሪ እንዳይላሉ የተባለ የጅሩ ሰው ነበርና የሀገር ሰው ከሆነ ዘንድ በቶሎ የሚቀናን መስሎን ነበር። አንድ ቀን ከደጅ ጠኚዎች ጋር አጋፋሪውን ስንከተል ዋልን። ማታ በአንድ አዳራሽ ውስጥ በጅምላ አስገቡንና ጋሬ እንጀራ አቅርበውልን እየተሻማን በላን። ሌሊቱንም እዚያው አዳራሽ ውስጥ ተኛንና ቁንጫ ሲጠብሰን አደረ። ይህ ሁሉ ሲሆን ስለመጣንበት ጉዳይ ያነጋገረን ወይም ዘወር ብሎ የተመለከተን አልነበረም። ጧት ሲነጋ በዚህ ዓይነት ኑሮ መኖርን ጠላሁና እኔ ተለይቼ ወደ ተማሪ ቤቴ ተመለስሁ። ሌሎቹ ግን ደጅ ጥናታቸውን ቀጥለው ነበር። ከዚህ በኋላ አባቴ ወደ ወምበር ቤት ለጸሐፊነት እስካስገቡኝ ድረስ (ገጽ 99) ሌላ ሥራ አልተመኘሁም።

# ምዕራፍ 12

## 1905 ዓመተ ምሕረት

ልጅ ኢያሱ ከጊሚራ ዘመቻ ሲመለሱ ስለማየቴ፣ አዲስ አበባ ላይ ስለተደረገ ተኩስ፣ ስወምበር በጸሐፊነት ሥራ ስለመግባቴ

### ልጅ ኢያሱ ከጊሚራ ዘመቻ ሲመለሱ ስለማየቴ

አዲሱ ዓመት፣ መስከረም 1 1905 ዓ.ም. ዘመነ ማቴዎስ፣ ረቡዕ ቀን ባተ። አባቴም ልጅ ኢያሱ ክረምቱን ወደ ጊሚራ ዘምተው እንደከረሙ ናቸው። አባቴም ካለፈው ዓመት ጀምረው ጅሩ በርስታቸው ላይ ተቀማጭ ሆነዋል። ይህም ርስታቸው አዲስ ዓለም ማርያም በደብተርነት የሚገበርበት ነው። በደብሩ ደንብ ትክለኞች ሁሉ በየዓመቱ ጥር 21 ቀን አዲስ ዓለም ላይ መገኘትና በዓሉን ማክበር ግዴታ አለባቸው። ስለዚህም ወደ አዲስ ዓለም ሄጄ በዓሉን እንዳከብር አባቴ ስለላኩብኝ በጥር 20 ቀን ስሄድ መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስን በመንገድ አገኘኋቸውና ተከትዬ ተጓዝሁ። ሆለታ ላይ ስንደርስ ልጅ ኢያሱ ከጊሚራ ተመልሰው ኖሮ በአንድ ጉብታ ላይ ተቀምጠው የሠራዊታቸውን ሰልፍ ሲመለከቱ አየን። የሰልፉ ምክንያት ወደፊት አዲስ አበባ ላይ ለሕዝብ የሚያሳዩትን ሰልፍ አስቀድሞ ለማየት ስለፈለጉ ነው ተባለ። ሰልፉ እጅግ ግሩም ነበር። ነጋሪቱ እየተጎሰመ ቀደመ። ወታደሩ እንደ ማዕርጉ አቡቀዳዲ አስሮ፣ ለምድ ለብሶ፣ አንፋሮ አስሮ፣ እያቅራራ በየደረጃው ተከተለ። ይህ ትርእይት ለእኔ ዓይን የመጀመሪያ ጊዜ ስለሆነ በጣም አስደንቆኝ ነበር። ከዚህ በኋላ መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ ተላልከው ከልጅ ኢያሱ ፊት ቀርበው እጅ ነሡና ወደ አዲስ ዓለም ጉዞአችንን ቀጠልን።

በማግሥቱ ጥር 21 ቀን ልጅ ኢያሱ ወደ አዲስ ዓለም መጥተው በዓሉን አከበሩ። ከበዓሉም በኋላ በሆለታ ቤተ መንግሥት ለካህናትና ለሠራዊት ግብር አደረጉ። እኔ ከግብሩ አልገባሁም። በማግሥቱ ጥር 22 ቀን ወደ አዲስ አበባ ተመለስሁ።

በዚህ ዓመት ጾመ ሁዳዴን ያሳለፍሁት በአዲስ አበባ መካነ ሥላሴ ነው፤ በዚሁም ጊዜ የሐዲስ ትርጓሜ ለመማር ጀምሬ ነበር። ሆኖም ትምህርቱን ሥራዬ ብዬ አልያዝሁትም።

### አዲስ አበባ ላይ ስለተደረገው ተኩስ

አጼ ምኒልክ በዚያው በቤተ መንግሥታቸው እንደ ታመሙ ነበሩ። ሕመማቸውም እየጸና ሄዷል። ልጅ ኢያሱ ከጊሚራ እንደተመለሱ አንድ ወሬ በከተማ ውስጥ በሹክሹክታ ይወራ ጀመር። ወሬው "ልጅ ኢያሱ ጃንሆይን



ከትልቁ ቤተ መንግሥት አስወጥተው በቃሬዛ ወደ እንቁባር ከተማ ሊሰዷቸውና እርሳቸው ከቤተ መንግሥት ገብተው እንዲነግሡ ምክሩ በዚህ ተቈርጧል" የሚል ነበር። የእልፍኝ ዘበኛ ጦር አለቆች ፊታውራሪ ገብረ ማርያምና ባሻ ደቻሣ፣ ሌሎችም ይህን ወሬ በሰሙ ጊዜ «እኛ ሳንሞት ጌታችንን ከቤታቸው የሚያስወጣቸው ማነው?» ብለው ተማማሉና ለውጊያ ቈርጠው ተዘጋጁ። የአቤቶ ኢያሱ ወገን የሆነውም ወደ አጼ ምኒልክ እልፍኝ እንዳይገባ በሩን ይዘው ከለከሉ።



21 አቤቶ ኢያሱ (ፈረስ ላይ የተቀመጡት)

በዚህ ጊዜ አጋፋሪ በየነና በጅሮንድ አሸናፊ የአቤቶ ኢያሱ ዋና ባለሟሎች ስለሆኑ የዘበኞቹ አለቆች በተናገሩት ነገርና በጀመሩት እርምጃ ተናደዱ። ስለዚህም ከቤተ መንግሥቱ በስተውጭ ጭፍሮቻቸውን አስቀምጠው ዙሪያውን ያስጠብቁ ጀመር። አጋፋሪ በየነ በፊት በር በኩል ሲያስጠብቁ በጅሮንድ አሸናፊም በግምጃ ቤት በኩል ሆነው ያስጠብቁ ነበር። በዚህ አኳኋን በግቢና በውጭ ተሰላልፈው ሲጠባበቁ ጥቂት ቀን ከቈዩ በኋላ የካቲት 22 ቀን 1905 ዓ.ም. ቅዳሜ ቀን በዘጠኝ ሰዓት ላይ ግጭት ተጀመረ። በመጀመሪያ አንድ ጥይት ባርቆ ስለተተኰሰ የጠቡ መነሻ ሆነ ተባለ። ዳግመኛም የባሻ ደቻሣ ልጅ፣ ባሻ ዓለሜ ከትልቁ አዳራሽ ጣሪያ ላይ በመሰላል ወጥቶ በፊት በር በኩል ባሉት በአጋፋሪ በየነ ጭፍሮች ላይ አስቀድሞ ስለተኰሰባቸው ግጭት ተጀመረ ተብሎ ተወራ። ያም ሆነ ይህ ከመጀመሪያው ተኩስ ቀጥሎ አምቢጓሮው ተጋጋለና ተኩስ ብቻ ሆነ። የግቢ ዘበኞች ወደ ውጭ ሲተኩሱ በቤተ መንግሥቱ ዙሪያ በስተውጭ ያሉትም የልጅ ኢያሱ ወገኖች ወደ ግቢው ይተኩሱ ጀመር። እኔ በዚያ ጊዜ አዲስ አበባ ሥላሴ ላይ ሆኜ በቅርብ ስለተመለከትሁት ሁኔታውን ሁሉ በሚገባ በውቀዋለሁ። ተኩሱ ሊበርድ

የቻለውም አጼ ምኒልክን እያስታመሙ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ የነበሩት እቴጌ ጣይቱና ወይዘሮ ዘውዲቱ እና ፊታውራሪ ገብረ ማርያምን ስለመከሩና ስለተቈጡ ነው ሲባል ሰምቻለሁ::

በዚህ ተኩስ ከወደ ግቢ የሞተ ሰው መኖሩን አልሰማሁም:: ከወደ ውጭ ግን 17 መንገድ ተላላፊዎች ሞተዋል ሲባል ሰምቻለሁ:: የቈሰሉም ነበሩ:: ቍጥራቸው ግን አልታወቀም:: ከአንዳንድ ሰዎች እንደሰማሁትም የሞተውና የቈሰለው እጅግ ብዙ ነው እያሉ የጅምላ ንግግር ይናገሩ ነበረ:: እኔ ግን አላምነውም::

ፀሐይ ከጠለቀች በኋላ፣ ማታ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ አንድ መድፍ አስይዘው ወደ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን መጥተው እንደ ነበረ እኔ ራሴ አይቻለሁ:: መድፉ በግልጽ እንዳይታይ ከደጀ ሰላም ውስጥ እንዲደበቅ አደረጉት:: እርሳቸው ግን በቤተ ክርስቲያኑ ደረጃ ላይ ተቀመጡና ሰው እየላኩ ወሬውን ሲያስጠይቁና ሲያሰልሉ አመሹ:: በዚያም እስከ አራት ሰዓት ድረስ ቈይተው የተኩሱን መቆም ካረጋገጡ በኋላ ተመልሰው ሄዱ::

## ለወምበር በጸሐፊነት ሥራ ስለመግባቴ

ሥራ ለማግኘት ካሁን በፊት በየክፍሉ ፊትኜ እንዳልተሳካልኝ እላይ ገልጬ ነበር (ገጽ 93):: አሁን ግን አንድ ሥራ ልጀምር ነው:: አባቴ በሁዳዴ ጾም መጨረሻ ከጅሩ ወደ አዲስ አበባ መጡ:: ስለ ኑሮዬም ካሰቡበት በኋላ በጓደኛቸው በደብተራ ፍሬው አማካይነት ከወምበሩ ከቀኛዝማች ናቄ ዘንድ በጸሐፊነት ሥራ እንድገባ አደረጉልኝ:: የገባሁትም ሚያዝያ 17 ቀን 1905 ዓ.ም. ነው:: ቀኛዝማች ናቄ የጅሩና የምሑይ ተወላጅ ናቸው:: ከዚህም በላይ በዚያ ዘመን የጅሩ ወምበር (ዳኛ) ሆነው ተሾመው ነበር:: እንግዲህ የአባቴ ሐሳብ በአንድ በኩል ሥራ እንድለምድ ሲሆን፣ በሌላውም በኩል የወምበር ጸሐፊ ከሆንኩ ዘንድ በባላገር ለሚነሣባቸው ጭቅጭቅ ደጋፊና ረዳት እንድሆናቸው በማሰብ ጭምር ነበር:: የወምበሩ ዋና ጸሐፊ አቶ ይገዙ የተባለ የጠራ ሰው ነው:: እኔም የእርሱ ምክትልና የምሥጢር ጸሐፊ ሆንሁ:: በተጨማሪም እልፍኝ አዳሪ አሽከር አድርገው ስለመረጡኝ ባለሟል እስከ መሆን ደረስሁ:: ዋናው ጸሐፊ የቀላጤ ማዘዣ[92] በጻፈ ቍጥር ከያንዳንዱ ባለጕዳይ አንዳንድ ሩብ ይቀበል ነበርና እርሱ በሌለበት ቀን እኔ እየጻፍሁ የቀላጤ ሩብ ለመቀበል ስለቻልሁ ደስታ ይሰማኝ ጀመር:: ከሥራውም ጋር ተለማምጄ ተመስገኜበት ነበር:: በዚህ ሥራ ላይ የቈየሁት አንድ ዓመት ከሦስት ወር ያህል ነው፣ በኋላ ግን እንዴት እንደ ለቀቅሁት ወደፊት እጽፋለሁ (ገጽ 99)::

---

[92] የማስገደጃና የማዘዣ ደብዳቤ::

# ምዕራፍ 13

## 1906 ዓመተ ምሕረት

**ስለ አጼ ምኒልክ መሞት፣ ስለ መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ መሞት፣ ወምበሩን ተከትዬ ወደ ጅሩ ስለመሄዴና ስለመመለሴ፣ የወምበር ጸሐፊነትን ስለመተዌ**

## ስለ አጼ ምኒልክ መሞት

በዚህ ዓመት አጼ ምኒልክ ሕመም ጸንቶባቸው ነበርና ታኅሣሥ 3 ቀን 1906 ዓ.ም. በዕለተ ዓርብ ሞቱ:: ወዲያው እንደሞቱ የግቢ ሥራ ቤቶች የልቅሶ ድምፅ አሰሙ:: ነገር ግን የልጅ ኢያሱ ባለሟሎች አገር እንዳይሸበር ሠግተው በቶሎ ዝም አሰኟቸው:: አቤቶ ኢያሱ በዚያ ዕለት ያደሩት ፍልውሐ በሚባለው በመታጠቢያ ቤታቸው ነበር:: እዚያው እንዳሉ ማለዳ የአባታቸውን የአጼ ምኒልክን መሞት ሲሰሙ ደንግጠው ወደ ቤታቸው ወጥተው ተቀመጡ:: ሆኖም አገር እንዳይሸበር በማለት ኀዘናቸውን በይፋ አላሳዩም:: እንዲያውም አንዳች ኀዘን አለመኖሩን ለማስመሰልና ለማሳመን ሲሉ በማግሥቱ ቅዳሜ ወደ ጃንሜዳ ወጥተው ከአሽከሮቻቸው ጋር በፈረስ ጉግሥ ሲጫወቱ ዋሉ:: ይህም ለአገር ጸጥታ ሲባል አማካሪዎች ያቀረቡላቸው ዘዴ መሆኑ አይጠረጠርም:: ስለዚህ የአጼ ምኒልክ ሞት ምሥጢር ሆኖ ተደበቀ::

የአጼ ምኒልክን አስከሬን አሽከሮቻቸው እንደ ነገሥታት ማዕርግ አምሮ በተሠራ በብረት ሣጥን አድርገው በቤተ መንግሥቱ ግቢ ውስጥ ባለችው በሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን በክብር አስቀመጡት::

ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱና ልጃቸው ወይዘሮ ዘውዲቱ በሣጥኑ አጠገብ ሆነው መሪር ልቅሶ ያለቅሱ ነበር:: ከዚህ በኋላ አጼ ምኒልክ በሕይወት አሉ እየተባለና እየተወራ እስከ ሰገሌ ዘመቻ ድረስ ሁለት ዓመት ከዓሥር ወር ተደበቀ:: የመንግሥቱ ሥራም በስማቸው ይካሄድ ነበር:: አጼ ምኒልክ የተወለዱት ነሐሴ 12 ቀን 1836 ዓ.ም. ስለሆነ በሞቱበት ጊዜ ዕድሜያቸው ስድሳ ዘጠኝ ዓመት ከአራት ወር ነበር::

አቤቶ ኢያሱ ምንም እንኳ የአጼ ምኒልክን መሞት እንዲደበቅ ቢያደርጉ ወሬውን የከተማው ሕዝብ ሰምቶት ነበርና ሁሉም በየቤቱ በድብቅ እያለቀሰ ኀዘን አደረገ:: አሽከሮቻቸውም በመደበቁ ምክንያት ይህን ለማድረግ ችግር ሆነባቸው:: ስለዚህም በስውር ለማስፈታትና ተዝካር ለማውጣት ልዩ ልዩ ዘዴ ይፈጥሩ ጀመር:: እንዲህ ያደረጉት ሰዎች ብዙ ሲሆኑ፣ አሁን ለምሳሌ ያህል የአንዱን ስም ከዚህ በታች እጠቅሳለሁ::

ቀኛዝማች ገብረ ጊዮርጊስ የተባሉት አሽከራቸው በዚያው ጊዜ ወደ አዲስ ዓለም ማርያም ሄደው "ወንድም ሞቶብኛልና የስዓተ ሲሊት ፍታት ፍቱልኝ፣ የክርስትና ስሙ ሣህለ ማርያም ነው" ብለው ካህናቱን ለመኑ። ሣህለ ማርያም የአጼ ምኒልክ የክርስትና ስም ነበርና ካህናቱ ጥያቄያቸውን ሰምተው ከተመካከሩ በኋላ "የወንድምዎ ስም ሣህለ ማርያም ከአጼ ምኒልክ የክርስትና ስም ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ እንፈታም፣ ልጅ ኢያሱ እንዳይቀጡን እንፈራለን፣ አይሆንልንም" ብለው መለሱላቸው። ይኸውም የካህናቱን ውለታ ቢስነትና የቀኛዝማቹን ቁም ነገራምነት የሚያመለክት ነው። የሆነ ሆኖ ስም ተጠርቶ ፍትሐት አልተፈታም እንጂ፣ ቀኛዝማች ገብረ ጊዮርጊስ ለተዝካር ያሰናዱትን ድግስ ለነዳያንና ለካህናት አብልተውታል። ኀዘናቸውንና ልቅሶአቸውንም በዚህ ዓይነት ዘዴ አብርደውታል።

## ስለ መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ መሞት

የገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አለቃ መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ በታኅሣሥ 18 ቀን 1906 ዓ.ም. ሞተው አዲስ አበባ ሥላሴ ተቀበሩ። እኚህ ሰው በሊቅነታቸው የተመሰገኑና የተከበሩ የአጼ ምኒልክ ፍትሐ ነገሥት አውጭ ነበሩ። እኔንም እንደ ልጅ አድርገው ይመለከቱኝ ነበርና ሞታቸው አሳዘነኝ። የቀብሩ ሥነ ሥርዓት እጬጌ ወልደ ጊዮርጊስና ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ባሉበት በታላቅ ክብር ተፈጸመ። በፍትሐቱ ጊዜ መዋሥዕት[93] የመሩት ካህን የሥላሴው ቀኝ ጌታ ወልደ ጊዮርጊስ ናቸው። እርሳቸው «እስመ በጥበብ ይትናገሮሙ፣ ወስእኑ ተቃውሞቶ ለእስጢፋኖስ ብእሲ ጻድቅ ዘምሉእ ሃይማኖተ»[94] የሚለውን የእስጢፋኖስን መዋሥዕት ለወልደ ዮሐንስ በማወራረስ ስለመሩ ካህናቱ አደነቋቸው። ምክንያቱም በ1870 ዓ.ም. ግንቦት 21 ቀን ቦሩ ሜዳ ላይ በተደረገው የሃይማኖት ጉባኤ[95] ተከራክረው የጸጋ ልጆችን የረቱ መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ ስለሆኑና ያንን ለማሳሰብ ምሥጢሩን አስማምተው ስላመጡት ነው።

## ወምበሩን ተከትዬ ወደ ጅሩ ስለመሄዴና ስለመመለሴ

የወምበሩ የቀኛዝማች ናቂ ጸሐፊ ሆኜ አዲስ አበባ ሳለሁ ወምበሩ ወደ ሄዱበት ሁሉ መከተል ነበረብኝ። በ1906 ዓ.ም. በግንቦት ወር ወምበሩ የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን በዓል ለማክበር ወደ ደብረ ሊባኖስ ሲሄዱ እኔም ተከተልሁ። ከአዲስ አበባ ተነሥቼ እንጦጦ ተራራ ሥር ስደርስ አቶ ሕለተ ወርቅ እሸቴ ከሚባሉት የእንጦጦ ማርያም ካህን (በኋላ ከንቲባ ሕለተ ወርቅ

[93] ስለ ሙታን ፍትንትና በዓበይት በዓላት የሚደረስ ጸሎት።

[94] ሃይማኖትን የተሞላ ጻድቅ ሰው እስጢፋኖስን መቃወም ተሳናቸው፤ በጥበቡ ይናገራቸዋልና።

[95] ሁለት ልደት (ተዋሕዶ) እና ሦስት ልደት (ጸጋ) ስለሚባለው ነገረ ሃይማኖትና ክርክር ገጽ 111 ይመልከቱ።



ከተባሉት) ጋራ በድንገት ከመንገድ ላይ ተገናኘን። እኔ የማኅተም ኮሮጆና ባለ ማኅደር የሆነ አንድ አፈ ድስት ብርሌ በአንገቴ አንጠልጥዬ ነበር። ብርሌው የወምበሩ ጨጅ መጠጫ ነው። አቶ ሕለተ ወርቅ ባዩኝ ጊዜ እየተገረሙ ተመለከቱኝ። ሊያነጋግሩኝም ስለፈለጉ ከጓዙ ለየት አድርገው ወደ ኋላ አስቀሩኝና የሚከተለውን ተናግረው ወቀሱኝ። "ኧረ በል ድጓና ቅኔ የተማርከው እንዲህ ለመሆን ኖሯል? አህያ ይመስል የጓዝ መጫኛ ትሆናለህ፣ የወልደ ቂርቆስን ልጅ እንዲህ ሆነህ በማየቴ አዘንሁ፣ አሁንም ይህን ሥራ እርግፍ አድርገህ ትተህ ወደ ትምህርትህ በቶሎ እንድትመለስ እመክርሃለሁ" አሉኝና ሌላም ብዙ ቃል ጨምረው መከሩኝ። እኔም ተሰናብቻቸው እየሮጥሁ ከጓዙ ዘንድ ደርሼ መንገዴን ቀጠልሁ። አቶ ሕለተ ወርቅ የተናገሩኝ ቃል እያደር ከልቤ እየገባ ያብሰለስለኝ ጀመር። ስለዚህም ሥራውን ለቅቄ ለመሄድ የምችልበትን መንገድ መፈለግ ያዝሁ።

ቀኛዝማች ናቂ ደብረ ሊባኖስ ደርሰው በዓሉን ካከበሩ በኋላ የጅሩ ርስታቸውን ለማየት ወደ ጅሩ ተጓዙ። እዚያም ስንደርስ ለአንድ ቀን ፈቃድ ተቀብዬ ሄጄ አባቴንና ዘመዶቼን ጉበኘሁ። የጸሐፊነት ሥራዬን ስለመተው ከአቶ ሕለተ ወርቅ የተነገረኝን ምክርና የራሴንም ፍላጎት ለአባቴ ብነግራቸው የማይስማሙበት ሆነ። ምክንያቱም ወምበሩን ቅር ለማሰኘት ስላልፈለጉና የርስት ባላንጦቻቸው በየርስቱ ነገር እንዳያጠቋቸው ስለሠጉ ነበር። ስለዚህም የአባቴን ፈቃድ ለመፈጸም ወደ ወምበሩ ተመልሼ የጸሐፊነት ሥራዬን ቀጠልሁ። ከጥቂት ጊዜም በኋላ ወምበሩን ተከትዬ ወደ አዲስ አበባ ተመለስሁ።

አቤቶ ኢያሱ በሰኔ ወር መጨረሻ አዲስ አበባ ላይ ሹም ሽር አድርገው ነበርና ቀኛዝማች ናቂን ከወምበርነት ሻሩዋቸው። በስፍራቸውም ግራ ወምበራቸው የነበሩት አቶ ሞላ ግራዝማች ተብለው ተሾሙበት። ከዚህ በኋላ ቀኛዝማች ናቂ ደጆ ጠኚ ሆነው ከአቤቶ ኢያሱ ግቢና ከባለሟሎች ቤት መመላለስን ያዙ። ነገር ግን ያገኙት ነገር የለም። እኔም እስከ ነሐሴ ድረስ እንደ ጥንቱ ሳገለግል ከቈየሁ በኋላ ሥራውን ትቼ ለመሄድ እሰናዳ ጀመር።

## የወምበር ጸሐፊነትን ስለመተዌ

በነሐሴ 17 ቀን 1906 ዓ.ም. እሑድ ጧት ቀኛዝማች ናቂን ተከትዬ አራዳ ጊዮርጊስ ሄድሁ። ለውትሮው ስከተል የማኅተም ኮረጆ አነግት ነበር። አሁን የወምበርነቱ ሥራ ስለቀረ አንዳች ነገር አልያዝሁም። ቀኛዝማች ናቂ ቅዳሴ ለማስቀደስ ወደ ቅድስት ገብተው ቆሙ። እኔ ግን በዚህ ጊዜ የአቶ ሕለተ ወርቅ ምክር በድንገት ትዝ አለኝና የመሄዴን ነገር አወጣና አወርድ ጀመር። ወዲያው ዝግ ብዬ ከቤተ ክርስቲያኑ ወጣሁና ሰው እንደሚፈልግ ዓይነት ወደ ምሥራቅ ዞርሁ። ከዚያም እርምጃዬን ቀጥዬ በደጃዝማች ውቤ ቤት በኩል አለፍሁና ወደ እንጦጦ ማርያም ገሠገሥሁ። ይህም ከወምበሩ ቤት የመጨረሻ መሰናበቻዬ ሆነ።

እንጦጦ ስደርስ ከአጎቴ ከመምሬ ራስ ወርቅ ቤት ገባሁ። የመጣሁበትንም ምክንያት ከዘረዘርሁ በኋላ ጅሩ ወደ አባቴ ዘንድ ለመሄድ ማሰቤን ገለጽሁላቸው። እርሳቸውም አሁን ክረምት ስለሆነ እስከ መስከረም ብትቈይ ይሻላል ብለው መከሩኝና እዚያው ተቀመጥሁ። ባለቤታቸው ወይዘሮ አስካለ ርኅርኅትና ደግ ሴት ስለሆኑ እንደ ልጃቸው አድርገው ይመለከቱኝ ነበር። ከዚህ በኋላ መምሬ ራስ ወርቅ ወደ ፋሌ ወስደው ከአጎታችን ከአዛዥ ወልደ ሰማዕት ጋር አስተዋወቁኝ። ወደ ፋሌ የሄድንበትም ዋናው ምክንያት መንግሥቱ ወልደ ማርያም የተባለ የልጅነት ጓደኛዬ ፋሌ ላይ ሚስት ስላጨ የቃል ማሠሪያ ውል ለማዋዋል ነው። የእጮኛይቱ አባት አቶ አረሩ የተባለ ባለቀላድ ነው። በቀጠሮው ቀን ነሐሴ 24 እሑድ ከአቶ አረሩ ቤት ደረስንና እንደ ዘመኑ ሥርዓት በእማኝና በዳኛ ቃል ማሠሪያው ተደረገ። መምሬ ራስ ወርቅ ለመንግሥቱ የነገር አባት ሲሆኑ፣ እኔም ሙዜ ሆኜ ነበር። ከዚያ ቀን በኋላ ግን እንጦጦ ላይ ስለሌለሁ ሠርጉ እንዴት እንደተፈጸመ በፍጹም አላውቅም።

# ምዕራፍ 14

## 1907 ዓመተ ምሕረት

**ወደ ጅሩ ስለመሄዱ፣ በሠርፀ ክርስቶስ ማርያም ሳለሁ፣ ወደ አዲስ አበባ ስለመመለሴ፣ ስለ አፈ ንጉሥ ጥላሁን የቤት ሥርዓትና ወግ፣ በቀበና አቦ ሳለሁ**

### ወደ ጅሩ ስለመሄዴ

አዲሱ ዓመት ዘመነ ሉቃስ 1907 ዓ.ም. ዓርብ ባተ። እኔም በመስከረም በመጀመሪያው ሳምንት ላይ ወደ ጅሩ ወርጄ ከአባቴ ጋር ተገናኘሁ። አባቴ ምድቅ አዲስ አምባ በሚባል ቤታቸው ላይ ነበሩ። ወይዘሮ ወለተ ሥላሴ የተባለች የይዘኝ አገር ሴት አግብተዋል። የትምህርት ጉባኤም ተስፋፍቶላቸው ነበርና ከዚያ አገር ልጆች እነ ዘሊባኖስ እነ ወልደ ማርያም ይደመሙ ድጓ ሲማሩ አገኘኋቸው። ሀብተ ማርያም ገብረ መድኅን የተባለም የትጉለት ሰው እዚያው ይማር ነበር። በልጅነቴ የተማርኋቸው ትምህርቶቼ ዜማና ቅኔ እምብዛም አልተዘነጉኝም። ሆኖም ዜማውን ለመከለስ ምኞቴ ሆኖ ሳለ አባቴ የቅኔውን አገባብ እንድከልስ ስለፈለጉ ሠርፀ ክርስቶስ ከአለቃ ጽጌ ገብረ ተክሌ ዘንድ ገባሁ። በዚህ ጊዜ ከነበሩኝ ጓደኞቼ የማነ ብርሃን፣ ዘመደ ብርሃን፣ ከፍሌ፣ ሥነ የተባሉትን አስታውሳለሁ። ስሜን ለውጬ ጌራ ወርቅ እንድባል አደረግሁ። ይህን ስም የመረጥሁበት ምክንያት ከአምስት ዓመት በፊት ሽንኩርት ሚካኤል ላይ ጌራ ወርቅ የተባለ ጓደኛ አበጅቼ ነበርና የእርሱ ፍቅር ከትዝታዬ ስላልተለየ ነበር (ገጽ 84)።

### በሠርፀ ክርስቶስ ማርያም ሳለሁ

በሠርፀ ክርስቶስ ተማሪ ቤት ስድስት ወር ያህል ቈየሁ። የአባቴ ጓደኛ መምሬ ወልደ ዮሐንስና ልጆቻቸው አካሉ፣ ገብሬ በወዳጅነት ተቀብለውኝ ነበር። እንጦጦ ራጉኤል ያሉትም ትልቁ ልጃቸው ቀኝ ጌታ ባልከው (በኋለኛው ጊዜ አፈ ንጉሥ ገብረ ክርስቶስ የተባሉት) የጥር ማርያምን በዓል ለማክበር መጥተው ነበርና እንዲሁ በወዳጅነት ተቀብለውኝ ነበር።

በዚያ ጊዜ ከነበሩት አዳዲስ ነገሮች አንዳንዶቹን እጠቅሳለሁ። አዶ ከበሬ የተባለ የዛር ዓይነት በሽታ ባገሩ ላይ ተናኝቶ ሴቱንም ወንዱንም ያስጨፍረው ነበር። በሽታው ከትግሬ የመጣ ነው ስለሚባል በሽተኛው የትግርኛ ዓይነት ይቀባጥራል። በሽታውን ለመሸኘት ድግስ መደገስ ስለሚያስፈልግ ድኻው ሕዝብ ባለጣጣ ሆኖ ከረመ።

ዳግመኛም ሞያሌ የተባለ በእግር ላይ የሚገባ በሽታ በዚያ ዘመን ስለመጣ የሁሉም እግር በወረንጦ ሲዘነጠል ይውል ጀመር። ስሙ ሞያሌ መባሉም በሽታው የመጣው በቦረና ወስጥ ካለው ሞያሌ ከተባለው ስፍራ በመሆኑ ነው እየተባለ ይነገር ነበር።

ጣጣቴ የተባለም በሽታ በዚሁ ዘመን መጣ። ጣጣቴ የትኩሳት በሽታ ነው። የዣንጥላ መጉተሪያ ብረት በእሳት አግሎ የበሽተኛውን ገላ በተኮሱት ጊዜ ይንጣጣ ነበርና ከዚህ የተነሣ የበሽታው ስም ጣጣቴ ተባለ።

እንዲሁ ደግሞ ዕጣን እየተጨሰ ቡና የመጠጣት ልማድ በባላገር የተጀመረው በዚያው ጊዜ ነው። ከዚያ በፊት ግን ይህ ዓይነት ልማድ የሚታየው በነጋዴዎችና በእስላሞች በተለይም በቃልቾች[96] ዘንድ ነበር። በበረሃ ስፍራ የሚኖሩ ነፍጠኞችም የዚሁ የቡና ልማድ ነበረባቸው።

ስለዚህም እነዚያ ነፍጠኞች ወይም ነጋዴዎች ወደ አገር ቤት በተመለሱ ጊዜ ዕጣን እያጨሱ ቡና ይጠጡ ነበርና ሌላውም እነሱን አይቶ ተከተለ። ይልቁንም የየመንደሩ ሴቶች የቡና ማኅበር እያበጁና ተራ በተራ እየተጠራሩ ቡና ሲያፈሉና ሲጠጡ መዋል ጀመሩ። ይኸውም ልማድ በባላገርም ሆነ በከተማ እየተስፋፋ ስለሄደ ብዙ ሰው የቡና ሱሰኛ ሆነ።

በዚያ ጊዜ ጨዋው ሕዝብና የቤተ ክህነት ሰዎች ዕጣን አጭሶ ቡና መጠጣትን እንደ ነውር ወይም እንደ አምልኮ ባዕድ አድርገው ይመለከቱት ነበር። ስለዚህም እነዚያን የቡና ማኅበረተኞች በመንቀፍ

ነይ ቡና ጠጪ
መቼም አታዳምጪ
ነጭ ቡና[97] እንጠጣ
ድሩም ማገም መጣ

እየተባለ በየሠርግ ቤቱ ይዘፈን ጀመር። ሆኖም ውሎ አድሮ ነቀፌታውና ነውርነቱ እየቀረ ሄዷል።

የባላገሩን የአገር ባህል ለመመልከት የቻልሁትም በዚያው ጊዜ ነው። ይኸውም የደመራና የጥምቀት በዓል፣ የሠርግና የቀብር ሥነ ሥርዓት ማለቴ ነው።

[96] ቃልቻ መሠረታዊ ፍችው የቍርዓን ትምህርት የተማረና በሼህ እየተላከ የተለያዩ የሃይማኖት ተግባራትን የሚያከናውን ማለት ነው። በተለምዶ ግን ቃሉ አውቃለሁ አድናለሁ ባይ ጠንቋይ ወይም ባለዛር ማለት ነው።

[97] በዚያን ጊዜ ድርና ማግ ሲዘጋጅ ደቦ ጠርቶ፣ ቡና እየጠጡ የማስፈተል ባህል ተለምዶ ስለነበር «ነጭ ቡና» ማለታቸው ከድርና ከማጉ ጋር በማያያዝ ዘፋኞች ለፈዝና ለነቀፋ ይዘፍኑት የነበረ ነው። ምንጭ - አቶ ሥዩም ዘነበ (አቶ ሥዩም የታሪክ ጸሐፊው ዘመድ፣ በ90 ዓመት ዕድሜው አሁንም በሕይወት ያለ ነው።)



በዚያው ጊዜ ተዋበች የተባለች ሴት (የአቶ ኮስትር ሚስት) በወባ በሽታ ሞታ ነበርና በቀብሩ ላይ የተፈጸመው የአገሩ ወግና ሥርዓት አስደንቆኝ ነበር።

## ወደ አዲስ አበባ ስለመመለሴ

በዚህ ዓመት፣ (1907 ዓ.ም.) ፋሲካ በመጋቢት 26 ቀን ሆነ። ፋሲካ እንዲህ ባለ ቀን ሲውል የባሕረ ሐሳብ[98] ሊቃውንት «የኢይወርድ ጊዜ»[99] ይሉታል። ይህ የሚያጋጥመውም በአንድ ዐውደ ዐቢይ ቀመር ውስጥ አራት ጊዜ ብቻ ነው። ዐውደ ዐቢይ ቀመር የሚባለውም 532 ዓመት ነው።

ከፋሲካ በኋላ፣ ከአፈ ንጉሥ ጥላሁን የተጻፈ አንድ ደብዳቤ፣ በሚያዝያ ወር ለአባቴ ደረሳቸው። ደብዳቤውም "አዲስ ቤተ ክርስቲያን ስላሠራሁና ስለተከልሁ እፈልግዎታለሁና ወረቀቱ እንደ ደረስዎ በቶሎ ይምጡ" የሚል ነው። በዚያ ዓመት በኅዳር ወር አፈ ንጉሥ ጥላሁን ቀበና ላይ አንድ ቤተ ክርስቲያን ማሠራት ጀምረው ነበር። መጀመሪያ ትንሽ መቃኞ አሠርተው በታኅሣሥ ወር ታቦት አስገቡበት፣ ቀጥሎም በመጋቢት 5 ቀን፤ እሑድ ታቦቱ ነግሦ የአቦ በዓል እንዲከበርበት አደረጉ። ዋናው ቤተ ክርስቲያኑ ግን ገና በሥራ ላይ ነበረ።

አባቴ በግንቦት ወር ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ እኔም ተከትዬ መጣሁ። ከደቀ መዛሙርታቸው ጀሩዬዎቹ ዘሊባኖስ፣ ወልደ ዮሐንስ፣ ወልደ ሐና፣ ወልደ ማርያም፣ መኩሪያ፣ ተጕለቴው ሀብተ ማርያም ተከተሏቸው። አዲስ አበባ እንደ ደረሱ፣ አፈ ንጉሥ ጥላሁን በግቢያቸው ውስጥ ማረፊያ ቤት ሰጥተው አክብረው አስቀመጧቸው። የአፈ ንጉሥ ጥላሁን አበ ነፍስ መምሬ ካሣዬና የወሎው አለቃ ገብረ ሰማዕት እዚያው ነበሩ። በፍቅር ተባብረው ከአፈ ንጉሡ ግቢ በዕለቱ በሚመጣላቸው ደንበኛ ድርጎ ይተዳደሩ ነበር።

## ስለ አፈ ንጉሥ ጥላሁን የቤት ሥርዓት ወግ

በዚያ ዘመን የአፈ ንጉሥ ጥላሁን ቤት ወጉና ሥርዓቱ ልክ በቤተ መንግሥቱ ዓይነት እስከ መሆን ደርሶ እንደ ነበረ እዚህ ላይ መናገር ይገባኛል። የትልልቆቹ ሹማምንታቸውም ስም የሚከተለው ነው። ግራዝማች መብራቴ

[98] ባሕር ማለት ዘመን፣ ሐሳብ ደግሞ ቍጥር ማለት ነው። ባሕረ ሐሳብ ማለት እንግዲህ የዘመን ቍጥር ማለት ነው። ባሕረ ሐሳብ የተቀመረው በአጼ ሱስንዮስ ሦስተኛ ዓመት ማለት በ1600 ዓ.ም. ላይ ነው። ባሕረ ሐሳብ የዓመቱን፣ የዕለቱን፣ የአጽዋማቱንና የበዓላቱን ቀመር (ቍጥር) የሚያወጡበት ነው። ምንጭ - ሥርግው ሀብለ ሥላሴ፣ የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት።

[99] የማይወርድ ማለት ነው። ከመጋቢት 26 ቀን በፊት ምን ጊዜም አይሆንም ማለት ነው። ስለ አጽዋማትና ስለ ዘመናት ማገናዘቢያ በቅርቡ የሚታተመውን የብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ መጽሐፍ፣ የዘመናት ማገናዘቢያን ይመልከቱ።

እንደራሴና አጋፋሪ፣ አቶ ልሳነ ወርቅ እንደ ጸሐፌ ትእዛዝ፣ አቶ ኪዳነ ማርያም ምክትል ጸሐፊ፣ አዛዥ ኪዳኔ ሙሉ ቤት አዛዥ፣ በጅሮንድ ወልደ ሰማዕት በጅሮንድ፣ አቶ ምንተስኖት ወምበር፣ ሻቃ መኩሪያ ሥጋ መልከኛ፣ አቶ እጅጉ ጠጅ መልከኛ፣ አቶ ተገኑ ዋና የእልፍኝ አስከልካይ፣ ወልደ መድኅን ምክትል የእልፍኝ አስከልካይ፣ አቶ ጉዳና የጠጅ ቤት ሹም።



22 አፈ ንጉሥ ጥላሁን

አባቴ በዚያ በአፈ ንጉሥ ጥላሁን ግቢ ሳሉ የዜማ ትምህርት ጉባኤ ዘረጉ። ተማሪዎችም ከጅሩ የተከተሏቸው ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም በብዙ ተሰበሰቡ። ከቀድሞ ደቀ መዛሙርታቸውም ጥቂቶቹ ዜማ ለመከለስ እየመጡ ድጓ ዘረጉ። እነርሱም ደብተራ ዘለቀ (በኋላ መልአከ ፀሐይ የተባሉ)፣ ሊቀ ጠበብት ደስታ የአዲስ አበባ ሩፋኤል፣ ደብተራ ኃይለ ማርያም ገብሩ የቃሊቲ ናቸው። እኔም በዚህ ጊዜ የጾም ምዕራፍና ከድጓ የዘመነ ዮሐንስን ክፍል ከልሻለሁ።

አፈ ንጉሥ ጥላሁን በግቢያቸው ሥዕል ቤት መሳይ አበጅተው ከልደታ እስከ ሥላሴ ድረስ ስብዔውን ሰዓታት ያስቆሙበት ነበር። ሰብዔው ሲፈጸም ለሰዓታት ቋሚዎቹ ሁለት ሁለት ብር ይሰጧቸዋል። የነዚያም መሪና ሰብሳቢ መምሬ ካሣዬ ሲሆኑ አባሎቹ አለቃ ገብረ ሰማዕትና የእኔ አባት አለቃ ወልደ ቂርቆስ፣ ቀኝ ጌታ ተክለ ሚካኤል፣ አቶ አገዘብጤ፣ አበበ ካሣዬ፣ መምሬ



ኃይለ ማርያምና እኔም ጭምር ነበርን። ይኸውም በጊዜው ያስደስተን ስለነበረ አሁን ሳስበው በጊዜው ሁናቴ እደነቃለሁ።

አለቃ ገብረ ሰማዕት የአፈ ንጉሡን ልጆች ዘነበችን[100]፣ ደምሴን፣ ካብትሽ ያመርንና የወዳጆቻቸውን ልጆች እነ ተፈራ አበበን እነ ሰይፉ መሸሻን በተለይ የሚያስተምሩና በጣም የተከበሩ ነበሩ። እኔም በአጋጣሚ ከእነዚህ ልጆችና ከአለቃ ገብረ ሰማዕት ልጅ ከኪዳኔ ጋር በጓደኝነት ደረጃ ስለተቀራረብሁ እንደ ክብር ሆኖ ይሰማኝ ነበር።

## በቀበና አቦ ሳለሁ



23 ቀበና አቦ ቤተ ክርስቲያን

የቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ ተጠናቆ በሰኔ መጨረሻ ላይ ስላለቀ ታቦቱ ከመቃኞ ወደ አዲሱ ሕንፃ ተዛወረ። መምሬ ካሣዬ ቄሰ ገበዝና ተጠባባቂ ሆነው ይሠሩ ጀመር። ትክለኛ ለመሆን ከየደብሩ የመጡት ቀሳውስትና ዲያቆናት ደብተሮችም መምሬ ካሣዬና አጋፋሪ ኃይለ ማርያም ሲመዘገቡ፣ ሀብተ ማርያምና እኔ በደብተርነት ተመዘገብን። ከተመዘገቡት ውስጥ የኔታ ብርሃኑ፣ የኔታ ገብረ ጻድቅ፣ መምሬ ኪዳኔ፣ መምሬ ወልደ ዳዊት፣ መምሬ ዘወልዴ፣ ደብተራ አክሊለ ብርሃን የቅርብ ወዳጆቼ ነበሩ።

---

[100] በኋላ ዘነበ ወርቅ የተባሉት።

አዲሱ ቤተ ክርስቲያን ሐምሌ 5 ቀን ሰኞ ለመጀመሪያ ጊዜ ማኅሌት ተቆመበት:: በዚያ ቀን የተሰበሰበው ደብተራ እስከ 50 ይደርስ ነበርና ማኅሌቱ ደምቆ ዋለ:: እንዲሁ ደግሞ አፈ ንጉሥ ጥላሁን የቤተ ክርስቲያኑን አለቅነት ለአባቴ ለአለቃ ወልደ ቂርቆስ ሰጧቸው:: ስለዚህም አባቴ ከአፈ ንጉሡ ግምጃ ቤት ካባና ድርብ ቀሚስ ተሸልመው ወጥተው በአለቅነት ወምበር ተቀመጡ:: በዚህ ቀን አፈ ንጉሥ ጥላሁን ስለ በዓሉ ክብር ለመኳንንትና ለካህናት ሙሉ ግብር አደረጉ:: ለአባቴም ስለ ሹመቱ የደስታ መግለጫ ብዙ ድግስ እስከ ቤታቸው ላኩላቸው::

ቤተ ክርስቲያኑ ከአድባራት ቍጥር እንዲገባ አፈ ንጉሥ ጥላሁን ለአቤቶ ኢያሱ አመልክተውና አስፈቅደው አስደበሩት:: የማዕርግ ተራውም ከጴጥሮስ ወጳውሎስ እንዲቀጥል ከዮሴፍ እንዲቀድም ሆኖ ተመዘገበ:: እኔም ክረምቱን እዚያው ከአባቴ ጋር ከረምሁ:: በዚህ ዘመን አፈ ንጉሥ ጥላሁን ለካህናትና ለታላላቅ ሰዎች የገዳም ቦታ መስጠት ጀመሩ:: በመጀመሪያው ጊዜ ቦታ የተመሩትና ቤት የሠሩት መምሬ ገብረ ዮሐንስ ናቸው:: እርሳቸው የዑራኤልና የተክለ ሃይማኖት ቄሰ ገበዝ ከመሆናቸውም በላይ የአፈ ንጉሥ ጥላሁን ጸሐፊ ትእዛዝ የአቶ ልሳነ ወርቅ የሚስታቸው አባት ናቸው:: በጣም የታወቁ የእርሻ ከበርቴ ስለሆኑ እጅግ ቸር ነበሩ::

ከመምሬ ገብረ ዮሐንስ ቀጥሎ ቦታ የተመሩት መምህር ፀሐይ፣ መምህር ሀብተ ገብርኤል፣ የእኔ አባት፣ አለቃ መርሻና መምሬ ካሣዬ ናቸው::

# ምዕራፍ 15

## 1908 ዓመተ ምሕረት

**አዲስ አበባ ሥላሴ ለትምህርት ስመላለስ፣ ወደ ጅሩ ስሄድ በመንገድ ላይ ስላጋጠመኝ ችግር**

### በአዲስ አበባ ሥላሴ ለትምህርት ስመላለስ

አዲሱ ዓመት ዘመነ ዮሐንስ 1908 ዓ.ም. እሑድ ባተ:: በመስከረም እኔና ጓደኛዬ መኩሪያ ዝማሬ ለመማር ወደ አዲስ አበባ ሥላሴ ከቀኝ ጌታ ወልደ ጊዮርጊስ ዘንድ መመላለስ ጀመርን:: እኅቴ ወለተ ጻድቅም (አሁን ስምዋ ተለውጦ ቦጋለች ተብሏል) አለቃ መርሻን አግብታ አራዳ ጊዮርጊስ ካህን ሰፈር ነበረች::

### ወደ ጅሩ ስሄድ በመንገድ ላይ ስላጋጠመኝ ችግር

በዚህ ዓመት በሰኔ ወር ስለ ዘጌ ርስታችን ጉዳይ አባቴ ወደ ጅሩ ልከውኝ ሄጄ ተመለስሁ:: በዚያ ሰሞን ሽፍታና ቀማኛ በየመንገዱ በርክቶ ስለነበረ በኔም ላይ የደረሰብኝን ከቶ አልረሳውም:: ሰኔ 11 ቀን እሑድ ጊዳ ላይ በአሴልቱ ወንዝ አጠገብ ከአንድ ኮረብታ ሥር ከመንገደኞች ጋር አደርሁና በማግሥቱ ሌሊት በ10 ሰዓት ተኩል ተነሥቼ ብቻዬን እንገዝ ጀመር:: ልብስ የተቋጠረባትና ስንቅ ያለባት አንዲት ከረጢት በዱላ ሰክቼ በትከሻዬ ላይ አንጠልጥያለሁ:: የአንድ ሰዓት መንገድ ተጕዤ ከአንድ ሰፊ ሜዳ ላይ ስደርስ መንገድ አቋርጦ የሚያልፍ አንድ ኦሮሞ አጋጠመኝ:: ራሱን የተከናነበና ዘንግ የያዘ ነው:: በተያየን ጊዜ ቆም ብሎ አመነታ:: ሊጣላኝ የፈለገ መሆኑም ተሰማኝ:: ሆኖም መሣሪያ ስላልያዘ ዝም ብሎኝ መንገዱን ቀጠለና በአቅራቢያችን ካለው መንደር ሲገባ አየሁት:: እኔም ጠርጥሬአለሁና እየሮጥሁ ሜዳውን ከአጋመስሁት በኋላ ወደ ኋላዬ ዞር ብዬ ብመለከት ያው ሰው በፈረስ ተቀምጦና ጦር ይዞ ወደ እኔ ሲጋልብ አየሁት:: አሁን ከሌሊቱ 12 ሰዓት ያህል ሆኖ ጨለማው መልቀቅ ጀምሯል:: ልብሴን ለመግፈፍና እኔን ለመግደል የሚጋልብ መሆኑ ተሰማኝና ወደ ፊቴ በሩጫ ገሠገሥሁ:: ብርታቱን ለሰጠኝ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባውና ባለፈረሱ ገና በሜዳው ሳለ እኔ በገልማ ወንዝ አፋፍ ከዘብጥ ስፍራ ላይ ደረስሁ:: የመሬቱም ገብታ እኔና እርሱ እንዳንተያይ አደረገን:: በዚህ ጊዜ እንደምንት እንደማመልጥ ጨንቆኝ እግዚአብሔርን ስለምን እንደ አጋጣሚ ከመንገዱ በስተቀኝ እረኞች ለጨዋታ ሲሉ እንደ በረት አድርገው የካቡት የድንጋይ ካብ አገኘሁና እርሱን መከታ አድርጌ እንደ ሚዳቋ ከሥሩ ተደበቅሁ:: ኦሮሞውም በፈረሱ ወዲያው ከተፍ አለ:: እኔ በነብ ቀዳዳ አየሁትና እየተንቀጠቀጥሁ ልቤ ትር ትር እያለ እግዚአብሔርን ለመንሁ:: ኦሮሞውም ግራና ቀኝ ተመልክቶ ቢያጣኝ ሮጦ

ያመለጥሁት መሰለውና በግልቢያ ወደፊቱ ገሠገሠ፡፡ የተደበቅሁበት ቦታ ከመንገዱ ከዓሥር እርምጃ የራቀ ሲሆን እግዚአብሔር እኔን ለማዳን ያንን ካብ ምክንያት አደረገልኝ፡፡

ኦሮሞው ወንዙን ተሻግሮ ሲርቅልኝ ከካቡ ሥር ተነሣሁና ማምለጫ መንገድ እፈልግ ጀመር፡፡ አሁንም ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባውና ከወደታች የነጋዴ ሰፈር ስላየሁ ወደዚያ ሮጬ ተቀላቀልሁ፡፡ ነጋዴዎቹ የወሎ ሰዎች ነበሩ፡፡ የደረሰብኝን ችግር ስነግራቸው ጊዜ "አይዞህ ከእኛ ጋር ትሄዳለህ" ብለው አጽናኑኝ፡፡ ቀጥሎም ነጋዴዎቹ አጋሰሶቻቸውን ጭነው ስለተነሡ አብሬ እጓዝ ጀመር፡፡ ያም ኦሮሞ እስከ ሩቅ ስፍራ ፈልጎ አጥቶኝ ወደ ቤቱ ሲመለስ ከመንገድ ላይ ተያየንና አተኩሮ ተመለከተኝ፡፡ ከንዴቱም ብዛት የተነሣ ወደኔ እያየ "ኤቻባኬቲ" (የት አባትክ) ብሎ ተሳደበና እየጋለበ ወደ ቤቱ ሄደ፡፡ እኔም ከነጋዴዎቹ ጋር ጉዞዬን ቀጠልሁ፡፡ በዚያ ቀን ከሞት ያዳነኝ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን፡፡

# ምዕራፍ 16

## 1909 ዓመተ ምሕረት

**በመጽሐፍ ትርጓሜ ትምህርት ቤት ሳለሁ፣ በሐዲስ ትምህርት ቤት ሳለሁ፣ በትምህርቴ ላይ ስለደረሰው ችግር፣ በተላላፊ በሽታ ስለመታመሜ፣ መኖሪያዬን ስለመለወጤ**

## በመጽሐፍ ትርጓሜ ትምህርት ቤት ሳለሁ

አዲሱ ዓመት ዘመነ ማቴዎስ 1909 ዓ.ም. ስኞ ባተ፡፡ ይህ ዘመን አቤቶ ኢያሱ ከመንግሥት የወጡበትና የሰገሌ ውጊያ የተደረገበት ዘመን ነው፡፡ መስከረም 17 ቀን፣ ረቡዕ በ9 ሰዓት ፊት በር በሚባለው ቤተ መንግሥቱ አደባባይ ነጋሪት እየተመታ ስለ መንግሥት መለወጥ ዓዋጅ ሲነገር በአጋጣሚ ከስፍራው ተገኝቼ የዓዋጁን ቃል ሰማሁ፡፡ ሌላውም የዘመን ታሪክ ስለ ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት በጻፍሁት የታሪክ ጽሑፍ ተዘርዝሮ ይገኛል[101]፡፡

ካሁን በፊት የመጻሕፍተ ሐዲሳትን ትርጓሜ ጀምሬ በትምህርቱ ሳልተጋበት ቈይቼ ነበር፡፡ በዚህ ዓመት ግን ትምህርቱን ሥራዬ ብዬ ያዝሁት፡፡ ዕድሜዬም 17 ዓመት ተኩል ሆኗል፡፡ አስተማሪዬ በመጻሕፍተ ሐዲሳት ትርጓሜ ስመ ጥር የሆኑትና የተመሰገኑት መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ናቸው፡፡ ሀገራቸው ሸዋ ሚጣቅ ሲሆን፣ ትምህርታቸው ግን ጐንደር ከወልደ አብ ወልደ ሚካኤል ነው፡፡ በ1881 ዓ.ም. ከጐንደር ተመልሰው መጥተው በእንጦጦ ራጉኤል እያስተማሩ እስከዚህ ዘመን ድረስ ሐያ ዘጠኝ ዓመታት የኖሩ ናቸው፡፡ በነዚህም ዘመናት ብዙ ደቀ መዛሙርትን እያስተማሩ መርቀዋል፡፡ ከብዙዎቹ መካከል ስማቸውን የማውቀው ርእሰ ደብር ዳኘ፣ አለቃ ተድላ ወልደ ጻድቅ፣ ጕጃሜ ማህሉ፣ አቶ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ[102]፣ ሁለቱ ገብረ መስቀሎች፣ ሊቀ ጠበብት ወልደ ጊዮርጊስ፣ መምህር ጽጌና አለቃ ተገኝ ናቸው፡፡

በዚህ ዘመን ንጉሥ ሚካኤል ሸዋን ለመውጋት ዘምተው ነበርና ፍንጥርኜ ላይ ሰፍረው ሳለ ከአዲስ አበባ አድባራትና ከሌሎች ገዳማት ታላላቅ መምህራን ለገላጋይነት ተመርጠው ሲላኩ ከገላጋዮቹ አንዱ መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ነበሩ፡፡ ገላጋዮቹ ወደ ንጉሥ ሚካኤል ሄዱና መልእክታቸውን አድርሰው ሲመለሱ ገና በመንገድ ሳሉ የሰገሌ ውጊያ ተከተለ፡፡ ውጊያውም በወሎዎች

---

[101] *የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ* በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አሳታሚነት የወጣውን የመርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስን መጽሐፍ፣ ክፍል ሦስት፣ የንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ የዘመን ታሪክ ይመልከቱ፡፡

[102] በኋላ ብላቴን ጌታ፡፡

ድል መሆን ተፈጸመና መልእክተኞቹ ሁሉ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ። በዚህ ጊዜ መምህር ወልደ ጊዮርጊስ እንጦጦ ራጉኤልን ትተው አዲስ አበባ ላይ ቀሩ። የቀሩበትም ምክንያት ቀጥሎ ያለው ነው። አለቃ ወልደ አማኑኤል የተባሉ የእንኮበር ማርያም ደብር አለቃ (ዓይነ ስውሩ) ሐዲስ ከእሳቸው ለመማር ይፈልጉ ነበር። አለቃ ወልደ አማኑኤል የቅኔ መምህር ከመሆናቸው በላይ በዜማም የተመሰገኑ ባለሞያ ሊቅ ናቸው። የአሁኑ ፍላጎታቸውም ሌላ ሞያ ጨምረው የመጻሕፍተ ሐዲሳት መምህር ለመሆን ነው። በዚህም ጊዜ መምህር ወልደ ጊዮርጊስን አገኟቸውና በአዲስ አበባ ቀርተው እንዲያስተምሩ አጥብቀው ለመኗቸው። ለኑሯቸው የሚያስፈልገውንም ከራሳቸው ሀብት ከፍለው አደራጁላቸው። በተጨማሪም በአራዳ ጊዮርጊስ ደብር በሐዲስ መምህርነት በደመወዝ እንዲቀጠሩና በማዕርግ እንዲቀመጡ ለደብሩ አለቃ ለንቡረ እድ አድማሱ ነግረው ተስማሙላቸው። የአዲስ ዓለም ማርያም ሹም ንቡረ እድ አድማሱ[103] በዚያ ጊዜ የአራዳ ጊዮርጊስን ደብር ጨምረው እንደያዙ ነበር። እንግዲህ መምህር ወልደ ጊዮርጊስ እንጦጦን ትተው በአዲስ አበባ የቀሩበትና ጉባኤ የዘረጉበት ምክንያት ይኸው ነው።

## በሐዲስ ትምህርት ቤት ሳለሁ

መምህር ወልደ ጊዮርጊስ በኅዳር ወር አዲስ አበባ በስልከኞች ሰፈር አንድ ቤት ተከራይተው የትምህርት ጉባኤ ከፈቱ። ከዚያ በኋላም በሙሴ አትናቴዎስ ቦታና በገዳም ሰፈር፣ በንቡረ እድ አድማሱ ግቢና በደጃች ሀብተ ሚካኤል ቦታ ላይ በየጊዜው እየተዘዋወሩ ተቀምጠዋል። በመጀመሪያው ጊዜ ዘጠኝ ደቀ መዛሙርት ተሰበሰቡላቸው። እነርሱም አለቃ ወልደ አማኑኤልና የጎሐ ጽዮን ገብረ ማርያም፣ የቅኔው መምህር አለቃ ብርሃኑ፣ ዕውሩ ወልደ ጊዮርጊስ፣ ወልደ ጻድቅና ቀለመ ወርቅ፣ የዜጋመሉ[104] መምህር ተክለ አረጋይና የበጌምድሩ መምህር ኃይለ ሚካኤል (በኋላ አቡነ ሚካኤል የተባሉት) ሲሆኑ ዘጠነኛው እኔ ራሴ ነበርሁ። ከዚያም በኋላ ሌሎች ደቀ መዛሙርት በየጊዜው ስለተጨመሩ ቍጥራችን እስከ ሐያ ደርሶ ነበር።

## በትምህርቴ ላይ ስለደረሰው ችግር

በዚህ ዘመን አባቴ አለቃ ወልደ ቂርቆስ የአቦ እልቅናቸውን ትተው ወደ ሀገራቸው ወደ ጅሩ ስለሄዱና እዚያው ስለተቀመጡ እኔ ያለሁት ከዘመዳችን ከአለቃ ወልደ ያሬድ ቤተሰብ ጋራ ነበር። እርሳቸውም የአዲስ አበባ ሥላሴ

[103] ንቡረ እድ አድማሱ ንቡረ እድ ተብለው የተሾሙት በመጋቢት 16 ቀን 1906 መሆኑን ሰምቻለሁ። (መ.ኅ.ወ.ቂ.)

[104] ዜጋመል ከደብረ ሊባኖስ በስተደቡብ ምዕራብ የአንድ ሰዓት ያህል የእግር መንገድ ርቆ የሚገኝ ቈላማ ስፍራ ነው። በተለምዶ አነጋገር ደብረ ሊባኖስም ዜጋመል ይባላል።



ደብር አለቃ ናቸው። አለቃ ወልደ ያሬድ አንድ ቀን ማታ ስለ ትምህርቴ ጠየቁኝና መጻሕፍተ ሐዲሳትን ለመማር መጀመሬን ነገርኋቸው። የአስተማሪዬንም ስም ገለጽሁላቸው። እሳቸው ግን ጥቂት ካሰቡ በኋላ "አባ ወልደ ጊዮርጊስ በሐዲስ ትርጓሜ የተመሰገኑ ሊቅ መሆናቸው እርግጥ ነው። ነገር ግን የሦስት ልደት ወገን ናቸው ይባላሉና ትርጓሜውን ብቻ ተማር እንጂ ሃይማኖታቸውን እንዳትከተል፣ የአባቶችህን የእነአለቃ ገብረ ክርስቶስን የእነመምህር ወልደ ሥላሴን ሃይማኖት ሁለት ልደትን እንዳትተው" ብለው አስጠነቀቁኝ። እኔም ፍላጎታቸውን ዐውቃለሁና "በሃይማኖትስ በኩል የናንተን የአባቶቼን ባህል በምንም ዓይነት አልለውጠውም" ስላልኋቸው በንግግሬ ደስ ብሏቸው መረቁኝ። ይሁን እንጂ አስተማሪዬ ስለ ሦስት ልደት ባህል አስተምረውኝ ወይም ተናግረውኝ አያውቁም፣ ሐሜተኞች ብቻ በእርሳቸው ላይ ሲናገሩ እሰማ ነበር።

ሁለት ልደትና ሦስት ልደት የሚባለው ነገረ ሃይማኖት እንዴት እንደሆነ አጭር መግለጫ መስጠት ያስፈልጋል። የዚህ ዓይነት ክርክርና የአስተሳሰብ ልዩነት የተፈጠረው ከግራኝ ወረራ ወዲህ በጐንደሮች ዘመነ መንግሥት ነው ይባላል። ካህናቱ በነገረ ስልት ሲራቀቁና ሲመራመሩ ይውሉ ስለነበረ በሐሳብ እየተለያዩ በእግዚአብሔር ባሕርይና በክርስቶስ ሰውነት ላይ ብዙ ጭቅጭቅ አበቀሉ። ሁለት ልደት፣ ሦስት ልደት፣ ወይም ተዋሕዶ፣ ጸጋ የሚባለውም ልዩነት ሊፈጠር ቻለ። ሁለት ልደትና ተዋሕዶ አንድ ዓይነት ስም ሲሆን፣ ሦስት ልደትና ጸጋ እንዲሁ አንድ ዓይነት ስም ነው።

ሁለት ልደት የሚባለው፣ ቃል ከአብ ያለ እናት የተወለደበትን ልደት አንድ ብሎ ቈጥሮ፣ ዳግም «ቃል ሥጋ ሆነ» በሚለው መሠረት ከማርያም ያለ አባት የተወለደውን ልደት ሁለት ብሎ በመቍጠር ነው። በዚህም ባህል ሁሉም ይስማሙበታል። የሚለያዩት ግን ወደፊት በምጽፈው በሦስተኛው ልደት ብቻ ነው።

የሁለት ልደት ወገኖች ምንም እንኳ በየአገሩና በየስፍራው ቢኖሩ አብዛኞቹ በአክሱምና በዲማ በዜና ማርቆስና በሌላም በአንድ አንድ ክፍል ይገኛሉ። የእኔ ዘመዶች እነ አለቃ ገብረ ክርስቶስና እነ አለቃ ወልደ ያሬድም የዚሁ የሁለት ልደት ወገኖች ስለሆኑ ሁለት ልደቶች ወይም ተዋሕዶዎች ይባላሉ። በተጨማሪም ተቃዋሚዎቻቸው ካራዎች እያሉ ይጠሩዋቸዋል። ምክንያቱም ለሃይማኖታቸው በመቅናት ካራ እየመዘዙ ሌሎቹን ያስፈራሩ ወይም ይደባደቡ ስለነበረ ነው እየተባለ ይተረካል።

ሦስት ልደት የሚባለውም አንደኛውና ሁለተኛው ልደት ከዚህ በላይ በተጻፈው ዓይነት ሆኖ በተጨማሪ ክርስቶስ በሰውነቱ የጸጋ ልጅነት አለው የሚሉትን ነገር ሦስተኛ አድርጎ በመቍጠር ነው። የሦስት ልደት ወገኖች ምንም እንኳ በየገሩና በየስፍራው ቢኖሩ አብዛኞቹ በጐንደርና በደብረ ሊባኖስ ቈላ በዜጋመል፣ በሚባለው ይገኛሉ። እነርሱንም ተቃዋሚዎቻቸው ሦስት ልደቶች ወይም የጸጋ ልጆች እያሉ ይጠሩዋቸዋል።

ሦስት ልደቶች ለክርስቶስ የጸጋ ልጅነት አለው የሚሉበትን ምክንያት ሲያስረዱ እንዲህ ይላሉ። "ሰው ሁሉ ከእግዚአብሔር አብ በጸጋ ተወልዷልና የአብ የጸጋ ልጅ ነው፣ ክርስቶስም ከማርያም በተወለደ ጊዜ ከኃጢአት በቀር ፍጹም ሰው ስለሆነ እንደ ሌላው ሰው ሁሉ ለአብ የጸጋ ልጅ መሆን አለበት" እያሉ ይከራከራሉ። የሁለት ልደት ወገኖችም ሰው ሁሉ የአብ የጸጋ ልጅ መሆኑን አይክዱም። ነገር ግን "ለክርስቶስ እንደ ሌላው ሰው ሁሉ የጸጋ ልጅነት አያሻውም፣ ወልደ አብ ወልደ ማርያም በተዋሕዶ ከበረ" እያሉ መልስ ይሰጣሉ። ሁለቱም ወገኖች በየበኩላቸው ማስረጃ ለማቅረብ ከየመጻሕፍቱ ብዙ የጥቅስ ቃል ያጎርፋሉ።

ሁለት ልደቶችና ሦስት ልደቶች በባህል ልዩነት ምንም እንኳ ቢጣሉ በቊርባንና በጸሎት በትምህርትና በሥልጣነ ክህነት ሳይለያዩ ባንድነት ይኖራሉ። ስለዚህ ጠባቸው በቤተሰብ ዓይነት ነው ሊባል ይቻላል። ሆኖም አንዱ የአንዱን ባህል በመንቀፍ መተማማታቸውና በቅኔ መጐሻመጣቸው የማይቀር ነው። ጠባቸው በከረረ ጊዜ ግን ጉባኤ ይደረግልን እያሉ ነገሥታቱን ያስቸግራሉ። ለምሳሌ አጼ ዮሐንስ በነገሡ በሰባተኛው ዓመት ግንቦት 21 ቀን 1870 ዓ.ም. ቦሩ ሜዳ ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ጉባኤ አድርገውላቸው ሁለት ልደቶችና ሦስት ልደቶች ተከራክረው ነበር። በዚህ ጊዜም ሁለት ልደቶች ረትተው ሦስት ልደቶች ተረትተው ክርክሩ ተፈጽሟል[105]።

በእኔ አስተያየት እነዚህ ሁለት ልደቶችና ሦስት ልደቶች እውነተኛውንና የቅንነቱን መንገድ አልተከተሉም። በእልከኝነትና በነገር ስልት ይጨቃጨቃሉ እንጂ በፍሬ ነገሩ የሚያጣላ ነገር አልነበረበትም። እንደ እውነቱ ከሆነ የእግዚአብሔርን ሀልዎት[106] እና የክርስቶስን መድኃኒትነት አምኖ መቀበልና በሰላም ተባብሮ መኖር በቂ ነበር እላለሁ።

የነገረ ሃይማኖት የባህል ልዩነት ይህ ብቻ አይደለም፣ ቅብዓት የተባለ ሌላም አከራካሪ ባህል አለ። ይህ ባህል በጐጃም በአንድ ክፍል በኩል የሚገኝ ነው። ስለ ተዋሕዶና ስለ ቅብዓት ልዩነትም አጭር መግለጫ እሰጣለሁ።

የቅብዓቶች ባህል «የእግዚአብሔር ቃል በድንግል ማርያም ማኅፀን ሲፀነስ ከእርስዋ የተነሣው ሥጋ በመንፈስ ቅዱስ ቅብዓት የአብ የባሕርይ ልጅ ሆነ» የሚል ነው።

[105] የታሪኩ ጸሐፊ ዘመድ አለቃ ወልደ ሐና በ1834 ዓ.ም. በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ችሎት ላይ የሃይማኖት ክርክር ሲደረግ የተዋህዶ (ሁለት ልደት) ልጆችን ወክለው የጸጋ (ሦስት ልደት) ልጆች ጠበቃን አለቃ ዓሥራትን ተከራክረው ረትተውታል። አለቃ ወልደ ሐና ታሪክ ያወቃቸው የተማሩ ሊቅ ነበሩ። የአለቃ ወልደ ሐና ትውልድ እንደሚከተለው ነው፤ የመርስዔ ኀዘን ቅድም አያት፣ የቄስ ደፈር እናት ዘረፉ አቅሌስን ወለደች። አቅሌስ አለቃ ወልደ ሐናን ወለደች። ምንጭ - የብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ያልታተመ ጽሑፍ።

[106] የእግዚአብሔርን መኖር።



የተዋሕዶዎችም ባህል "የእግዚአብሔር ቃል በድንግል ማርያም ማኅፀን ሲፀነስ ከእርስዋ የተነሣው ሥጋ በተዋሕዶ የአብ፣ የባሕርይ ልጅ ሆነ" የሚል ነው።

በቅዱሳት መጻሕፍት ተቀብዐ ተብሎ ስለ ኢየሱስ ቅብዓት የተጻፈውን ሁሉ ሁለቱም ወገኖች ስለሚቀበሉት ከዚህ በላይ በተነገረው ዓይነት ለየባሕላቸው የሚስማማ ትርጉም እየሰጡ ይከሩበታል።

በሊቃውንት አነጋገር ተቀብዐ የሚለው ቃል «ከበረ፣ ተቀደሰ፣ ተለየ» ማለትን የሚያሳይ ነው። በዘመነ ብሉይ ነገሥታትና ካህናት በቅዱስ ዘይት (በቅብዓ ቅዱስ) ሲቀቡ የተከበሩ፣ የተቀደሱ፣ የተለዩ ይሆኑ ነበርና የቃሉ ሥረ ነገር ከዚያም የተያያዘ ነው ይባላል። (ዘጸአ. 30 25 32። 40 9 15። ዘሌዋ. .8 10 13። 21 10 12)

የቅብዓቶችና የተዋሕዶዎች ክርክር በጐንደሮች ዘመነ መንግሥት የከረረ ነበር። በየዘመኑም እየተከራከሩ በየተራ ሲሸናነፉና እርታታቸውን በዓዋጅ ሲያስነግሩ ኖረዋል።

ለምሳሌ በአእላፍ ሰገድ ዮሐንስ ዘመን፣ በ1672 ዓ.ም. ጥቅምት 10 ቀን የሃይማኖት ጉባኤ ቆሞ ነበርና የቅብዓቶች አፈ ጉባኤ አባ አካለ ክርስቶስና የተዋሕዶዎች አፈ ጉባኤ አባ ኒቆላዎስ በየበኩላቸው ከመጻሕፍት እየጠቀሱ በንጉሡ ፊት በብዙ ተከራከሩ። በክርክሩም ላይ አባ አካለ ክርስቶስ ተረትቶ ጳጳሱና እጨጌው አወገዙት። ንጉሡ አእላፍ ሰገድ ዮሐንስም የተዋሕዶዎችን መርታት የቅብዓቶችን መረታት አይተው «ከበረ ሥጋ በተዋሕዶ» ተብሎ ዓዋጅ እንዲነገር አደረጉ። እርሳቸው ራሳቸው ግን የግል እምነታቸውን ሲገልጡ "እኔ ራሴ በተረቺዎቹ በኩል ነኝ" ብለው ተናገሩ ይባላል።

እንዲሁ ደግሞ ቅብዓቶች በአድራር ሰገድ ቴዎፍሎስና በአድባር ሰገድ ዳዊት ዘመን አሸናፊዎች ሆነው ነበርና «በቅብዓት የባሕርይ ልጅ» እንዲባል ዓዋጅ እየተነገረላቸው ደስ የተሰኙበት ጊዜም ነበር።

አባ አካለ ክርስቶስ የሞተው መስከረም 21 ቀን 1700 ዓ.ም. በዕለተ ዓርብ ቀበሮ ሜዳ ላይ በተደረገው ጦርነት ነው። የጐጃም መኳንንት በዚያ ዘመን ዓምደ ጽዮን የተባለ አዲስ ንጉሥ አውጥተው በጐንደሩ ንጉሥ በሉል ሰገድ ተክለ ሃይማኖት አመፁበት። አባ አካለ ክርስቶስም ከወገኖቹ ከቅብዓት መነኰሳት ጋራ የአዲሱ ንጉሥ ወገን ሆኖ ተከተለ። በዚህ ጊዜ ሉል ሰገድ ተክለ ሃይማኖት የላከው ጭፍራ በቀበሮ ሜዳ ላይ ጦርነት ገጥሞ ተዋጋና አዲሱን ንጉሥ ዓምደ ጽዮንን ድል አድርጎ ገደለው። አባ አካለ ክርስቶስና የቅብዓት መነኰሳትም በውጊያ ላይ ሞቱ። አባ ኒቆላዎስም ሚያዝያ 4 ቀን 1712 ዓ.ም. በዕለተ ኀሙስ ጃዊ በተባለ የኦሮሞ ጭፍራ ተደብድቦ ሞቶ አዘዞ ላይ ተቀብሯል።

ከዚህ በላይ በገጽ 110 እንደጻፍኩት አለቃ ወልደ ያሬድ እኔን ለማስጠንቀቅ የተናገሩት ቃል በተማሪ ቤቱ ስለተሰማ (መቼም ወሬ አይደበቅምና) ለትምህርቴ መሰናክል ነገርን ፈጠረብኝ። የትምህርት ጓደኛዬ ገብረ ማርያም ይህን ወሬ ሰምቶ ለአለቃ ወልደ አማኑኤል አስተላለፈላቸው። እንዲያውም ትችት ጨመረበትና "እረ ለመሆኑ የአለቃ ወልደ ያሬድ ወገንና ዘመድ የሆነ ሰው ለደግ ነገር ወደዚህ ይመጣል ወይ፣ የኔታ የሚናገሩትን ሰምቶ ለመንቀፍ ወይም ለማጣላት ይሆናል እንጂ" እያለ እያጋነነና አባብሶ አወራላቸው። እሳቸውም ወሬውን አመኑለትና "እንግዲህ መርስዔ ኀዘን በዚህ ተማሪ ቤት እንዳይማር" ብለው ከትምህርት ከለከሉኝ። እኔም ያላሰብሁት ነገር በድንገት ስለደረሰብኝ ደንግጬ ሳለሁ፣ አስተማሪዬ መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ወሬውን ሰምተው (መቼም ብሩክ ቅዱስ ሰው ናቸውና) "የማንም ወገን ቢሆን ልማር ብሎ ከመጣ አስተምረዋለሁ እንጂ አልከለክለውም" ብለው ለአለቃ ወልደ አማኑኤል ተናግረው ክልከላውን አንሥተውልኝ በማግሥቱ ትምህርቴን ቀጠልሁ። የአስተማሪዬ ፍቅር በሕሊናዬ ተቀርጾ ሊኖር የቻለው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው። አለቃ ወልደ አማኑኤልም አንድ ዓመት ያህል አኩርፈውኝ ከቈዩ በኋላ ነገሩን ሁሉ መርምረው ስለተረዱና አንዳች ምክንያት ስላጡብኝ እንደገና ዋና ወዳጅ አድርገውኝ ኖሩ።

## በተላላፊ በሽታ ስለመታመሜ

በዚህ ዓመት፣ በጥር ወር፣ አንድ ቀን ከትምህርት ቤት ስመለስ ራሴን ያዞረኝ ጀመር። ወዲያው ሌሊቱን ትኩሳት አወረደብኝ፤ ይኸውም ውሎ አድሮ ተላላፊ በሽታ ሆኖ ተገኘ። በዚህ ጊዜ አለቃ ወልደ ያሬድ በልጅ ልጃቸው በአጐናፍር ጎጆ እንድተኛ አደረጉኝና የልጃቸው የአቶ ይመር ልጅ ጌጤነሽ አስታመመችኝ። አምስት ቀን ከቈየሁ በኋላም ጓደኛዬ ሀብተ ማርያም ገብረ መድኅን በበቅሎ ወደ አራዳ ወስዶ ከእኅቴ ከቦጋለች ዘንድ አደረሰኝ። እርሷም አስታማ በእግዚአብሔር ቸርነት አዳነችኝ። የእናቴ ልጅ ቦጋለች እኔን ስታስታምም ብዙ ድካምና ጭንቀት ነበረባት። የቀድሞ ባልዋ አለቃ መርሻ እየተመላለሱ እንደጠየቁኝና ለመታመሚያ ብለው ዓሥር ብር እንደሰጡኝ አስታወሳለሁ።

በጥር ወር መጨረሻ ከሕመሙ ድኜ ወደ ትምህርት ቤት ተመለስሁ። እንዲሁም በየካቲት 4 ቀን ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘውድ ጭነው ሲነግሡ የበዓሉን ሥርዓት ለማየት እከታተል ነበር። ምክንያቱም ንጉሥ እንዴት እንደሚነግሥ ማየት ለኔ የመጀመሪያ ጊዜዬ ስለሆነና እንዳያመልጠኝ ስለፈለግሁ ነበር። የተመለከትሁትንም ሁሉ ስለ ዘመን ታሪክ በጻፍሁበት ላይ ገልጫለሁ።

በዚህ በ1909 ዓ.ም. ትምህርቴን በትጋት ስማር ከረምሁ። የትርጓሜ ትምህርት የጀመርሁት በወንጌል ነበርና በሆሳዕና ሰሞን የማቴዎስን ወንጌል ጨርሼ ወደ ተከታዩ ተላለፍሁ። እንዲሁም በዓመቱ መጨረሻ አራቱን ወንጌላት ጨርሼ ጳውሎስን ጀምሬ ነበር።



ትምህርቴን ለማፋጠን አስተማሪዬ ያደረጉልኝንም እርዳታ በሚከተለው እገልጣለሁ። ወልደ ጊዮርጊስ የተባለ ዓይነ ስውር ልጅ ነበር። በዕድሜ እኩያዬ የሚሆን ይመስለኛል፣ በትምህርት ግን ከእኔ በፊት ሐዲሱን ተምሮ ያወቀና የጨረሰ ነው። አስተማሪዬ ትጋቴን አይተው ስላሰቡልኝ ወልደ ጊዮርጊስ መጀመሪያ እንዲያሄድልኝና እንዲያስጠናኝ አዘዙልኝ። እኔም እርሱን እየተለማመጥሁ በየዜማው ትርጓሜውን አስጠርጌ ከቀጠልሁ በኋላ፣ በማግሥቱ ከየኔታ ዘንድ ሁለት ጊዜ ሳሄደው አንዱን ጉባኤ በትክክል ለማስቀረት እችል ጀመር። ለዚህም ስለበቃሁ የእግዚአብሔርን ቸርነት በብዙ አመሰገንሁ።

ስለ ወልደ ጊዮርጊስ ጠባይና ስለ ችሎታው ጥቂት ቃል መናገር ይገባኛል። ይህ ልጅ ትውልዱ ኦሮሞ፣ አገሩ አድአ ነው። አባቱ የርእሰ ደብር ዳኜ ጭሰኛ [107] የነበረ ሰው ነው። ወልደ ጊዮርጊስ ገና ሕፃን ሳለ በፈንጣጣ በሽታ ዓይኑን ስለታወረ አባቱ ወደ እንጦጦ አምጥቶ እባክዎ ያስተምሩልኝ ብሎ ለርእሰ ደብር ዳኜ ጥሎላቸው ሄደ። እሳቸውም መጀመሪያ ወደ ንባብ ተማሪ ቤት ቀጥሎም ወደ ዜማና ወደ ቅኔ ተማሪ ቤት እያስገቡ እንዲማር አደረጉት። ቅኔውን ከአለቃ ብርሃኑ ዘንድ ተምሮ ከተቀኘ በኋላ፣ ሐዲስ ለመማር ከየኔታ ወልደ ጊዮርጊስ ዘንድ ገባ። አሁን ከቅኔ አስተማሪው ከአለቃ ብርሃኑ ጋር የትምህርት ጓደኛ ሆኖ ሐዲስ ይማር ጀመር። የዚህ ልጅ አእምሮው እጅግ ብሩህ ስለሆነ ትምህርት አልመከተህ አለው። እንዲሁም የሐዲሱን ንባብ ከሥር እስከ ጫፍ በቃሉ ይዞት ነበር። አንዱን ጉባኤ አንድ ጊዜ ብቻ ሰምቶ እስከ መያዝ ድረስ አስደናቂ የማጥናት ችሎታ ነበረው። በይበልጥ የሚያስገርመኝም ያጠናውን አለመግደፉ ነበር። የኔታ ወልደ ጊዮርጊስም በወምበሬ የሚተካ ደቀ መዝሙር አገኘሁ ብለው ደስ ስላላቸው ጀማሪዎቹን ደቀ መዛሙርት እንዲያስተምር ፈቀዱለትና ከእርሳቸው ጋር በቤታቸው እንዲቀመጥ አደረጉት። በጠባይ በኩል ግን የየኔታን ምግባር ሊከተል አልቻለም። የትዕቢት መንፈስ ክፉኛ አደረበት፤ በትምህርት ተወዳዳሪ እንደሌለው ስለተረዳ ሁሉንም ናቀ። ፍላጎቱና ምኞቱም በአንድ ትልቅ ደብር ላይ ለመሾም ብቻ ሆነ። ለዚህም ማስረጃ የሚሆን አንድ ቃል እጨምራለሁ።

በዚያ ዘመን ሊቀ ካህናቱ አቶ ወልደ መስቀል ታሪኩ (በኋላ መልአከ ሰላም የተባሉ) ነበሩና አባ ሻውል በተባሉ ባሕታዊ በኩል ቀርቦ ተገናኝቶ ሹመት ያስጡኝ ብሎ አመለከታቸው። ሊቀ ካህናቱም ነገሩን መርምረው የትምህርት ችሎታውንና ሊቅነቱን ስለተረዱለት እየመጣህ አስታውሰኝ ብለው ባልደረባ ሰጡት። በአጋጣሚም የፍልሰታ ጾም ወዲያው ስለገባ ውዳሴ ማርያም እየተረጐመ እንዲያሰማቸው ጠየቁት። እርሱም ወደ ቤታቸው እየተመላለሰ ሁለቱን ሰባዔ ሙሉ ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም ወንጌልም

[107] ከዋናው ባለ ርስት ተዋውሎ የሚቀመጥ። የርስትነት መብት የሌለው ስለሆነ ቤት ሠርቶ በሚያጨሰው ጭስ ይጠራል። ከሰበሉ አንድ እጅ ለባለርስቱ ሰጥቶ ሁለት እጅ ለራሱ ያስቀራል። ባለ ርስቱ ተነሣ ባለው ጊዜ ይነሣል፣ እስኪሄድ ድረስ ግን በግዴታ ቀን ይሰጠዋል።

ሲተረጉምላቸው ሰነበተ:: በዚህ ጊዜ አቶ ወልደ መስቀል ታሪኩ በሙያው ተደስተው ለንግሥት ዘውዲቱ ነገሩለትና የጉለሌውን የጴጥሮስ ወጳውሎስን ደብር አለቅነት አስፈቀዱለት:: ይህንኑም በነገሩት ጊዜ ለትንሽ ደብር በመታጨቱ ተናደደና "እረ ለመሆኑ ራጉኤልን ማን ሊሾመው ነው?" ብሎ በብስጭት ቃል መለሰላቸው:: ቀጥሎም ይህን ትንሽ ደብር የማይቀበል መሆኑን ገለጸላቸው:: እሳቸው ግን ምንጊዜም ትዕግሥተኛ ናቸውና "ትልቁን ደብር ቀስ በቀስ ታገኘዋለህ በማለት ነው እንጂ አይገባህም በማለት አይደለም፣ እንግዲህ ሌላው እስቲገኝ ድረስ መጠበቅ ነው" ብለው ነግረው አሰናበቱት:: ይህ ወሬ ከተማሪ ቤታችን ደርሶ በተሰማ ጊዜ "ይህ ልጅ ትዕቢት አበዛ፣ ይቀሰፋል" እያሉ ጓደኞቹ ሁሉ አዘኑለት:: ይህም ሲፈጸም ወደፊት እናያለን (ገጽ 119)::

### መኖሪያዬን ስለመለወጤ

መኖሪያዬ በአለቃ ወልደ ያሬድ ግቢ እንደነበረ ባለፈው ገልጫለሁ (ገጽ 110):: በዓመቱ መጨረሻ ላይ ግን እርሱን ትቼ ከአስተማሪዬ ዘንድ እቀመጥ ጀመር:: ምክንያቱም ሽማግሌው አለቃ ወልደ ያሬድ በሐምሌ ወር የአዲስ አበባ ሥላሴ ደብር አለቅነታቸውን ስለተሻሩና ወደ አዲስ ዓለም ሄደው በርስታቸው ላይ ስለተቀመጡ ነበር:: በሹመታቸውም ፍትሐ ነገሥት አውጭው አለቃ ጽጌ ሻውል መልአከ ብርሃን ተብለው ተሾሙበት::

በዚያ ዘመን የካህናት ማዕርግ ከፍ ከፍ ብሎ ስለነበረ በየጊዜው የካህናትን ሹመትና ሽልማት እንሰማ ነበር:: እንደማስታውሰውም ምክትል ፍትሐ ነገሥት አውጭው አለቃ ተሰማ ቀጨኔ መድኃኔ ዓለምን ተሾሙ:: ይህም ደብር የልጅ ኢያሱ ነፍስ አባት የአባ ወልደ ጊዮርጊስ ሹመት የነበረው ነው:: እንደዚሁ ደግሞ ከዲማ የመጡት አለቃ ወልደ ማርያም ቀበና አቦን ተሾሙ:: ይህም የአባቴ የአለቃ ወልደ ቂርቆስ ሹመት የነበረው ነው:: በተከታዩም ዓመት በታኅሣሥ ወር አባ ተድላ መልአከ ገነት ተብለው የአራዳ ጊዮርጊስን ተሾመዋል::

# ምዕራፍ 17

## 1910 ዓመተ ምሕረት

**ትምህርቴን በመቀጠል ላይ ሳለሁ፣ ስለ ሽልማት፣ የተስቦ በሽታ በተማሪ ቤቱ ስለመግባቱ፣ ወደ ሐረር ስለመውረዴ፣ በሐረር ላይ ሳለሁ፣ ስለ ሐረር ከተማ**

### ትምህርቴን በመቀጠል ላይ ሳለሁ

አዲሱ ዓመት ዘመነ ማርቆስ 1910 ዓ.ም. ማክሰኞ ባተ:: በዚህም ዓመት ትምህርቴን እንደቀጠልሁ ነኝ:: ጳውሎስን ጨርሼ ወደ ግብረ ሐዋርያ ተሻልፌአለሁ:: እንዲሁም በቀበና አቦ በትክለኝነት የያዝሁትንና በአዲስ አበባ ሥላሴ በቆፍነት ያለኝን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አላቋረጥሁም:: ቀኝ ጌታ ዮፍታሔም[108] ከአገሩ ከጐጃም መጥቶ በዚሁ ዘመን አቦ ትክለኛ ሆኖ በደብተርነት ተተክሎ ነበርና በዚሁ ጊዜ ተዋውቀን ጓደኝነት ጀመርን::

አባቴ አለቃ ወልደ ቂርቆስ በጥር ወር እኔን ለማየትና ለሌላም ጉዳይ ከጅሩ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ነበርና ስለ ትምህርቴ እርምጃ አስተማሪዬን ጠይቀው በሰሙት ነገር ደስ አላቸው:: ስለዚህም በዐዋቂ ሰው ዓይነት ያነጋግሩኝ ነበር እንጂ እንደቀድሞው በልጅነት ጠባይ አልተመለከቱኝም::

በዚሁም ዘመን የቤተልሔሙ የመዝገበ ድጓ ምስክር አለቃ መርሻ ከበጌምድር መጥተው አዲስ አበባ ላይ ስለነበሩ አባቴ ከእርሳቸው ጋራ አስተዋወቁኝ:: እኒህ ሰው የአባቴ የትምህርት ቤት ጓደኛቸው የነበሩ ናቸው:: በካህናትም

[108] ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ በ1887 ዓ.ም. ጐጃም ደብረ ኤልያስ በተባለ ስፍራ ተወለዱ:: በ1911 ዓ.ም. አዲስ አበባ መጥተው መጀመሪያ በሲ.ጋባ ክፍል የጽሕፈት ሥራ ይሠሩ ነበር:: ከዚያም በኋላ በዳግማዊ ምኒልክና በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት አማርኛ አስተማሪ ነበሩ:: ከዚያም በቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪ ቤት ዲሬክተር ሆነው ሲያስተዳድሩ በነበሩበት ጊዜ ልዩ ልዩ ተውኔቶችና ድርሰቶች ደርሰዋል:: በጠላት ወረራ ዘመን ሱዳን በስደት ቈይተዋል:: ከነፃነት መመለስ በኋላ በጥቅምት ወር 1935 ዓ.ም. የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ምክትል ፕሬዜዳንት ተብለው ተሾሙ:: ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ በዘመኑ ከነበሩት ዕውቅ የሥነ ጥበብ ሰዎች አንዱ ነበሩ:: ዓሥራ ስድስት ያህል ተውኔቶችን፣ መዝሙሮችንና ግጥሞችን ደርሰዋል:: ከጠላት ወረራ በፊት ከደረሱዋቸው ውስጥ ተአምራዊው ዋሽንት፣ ጥቅም ያለበት ጨዋታ፣ አባት ንጉሣችን፣ ጠረፍ ያብበቅ፣ የሕዝብ ጸጸትና ሙሾ በከንቱ ይገኙበታል:: በስደት ሱዳን በነበሩበት ጊዜ አፋጀሽኝና ዓለም አታላይ የተባሉትን ተውኔቶች ደርሰዋል:: ከጠላት ወረራም በኋላ እያዩ ማዘንን፣ እርባዕተ ፀሐይ ን፣ ንጉሥና ዘውዱን ደርሰዋል:: በ1928 ዓ.ም. ጎበዝ አየን የተባለው የተውኔት መጽሐፋቸው ታትሞ ወጥቶ ነበር:: የዮፍታሔ ንጉሤ ድርሰቶች በሀገር ፍቅር፣ ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝነት፣ በትምህርት ጥቅምና በሥራ ክቡርነት ላይ ያተኩሩ ነበሩ:: ሰኔ 30 ቀን 1939 ዓ.ም. በ53 ዓመት ዕድሜ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ሥርዓተ ቀብራቸው ሐምሌ 1 ቀን 1939 ዓ.ም. በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል:: ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ እስከ ሰለተ ዕረፍታቸው ድረስ ከብላታ መርስዔ ኀዘን ጋር በወዳጅነትና በቤተ ሰብነት ኖረዋል::

ዘንድ ከፍተኛ ዝና ያላቸው ትልቅ ሰው ስለሆኑ እርሳቸውን በማየቱና በመተዋወቁ ደስ አለኝ።



24 ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ

## ስለ ሽልማት

በዚህ ዘመን የጥምቀት በዓል ጥር 11 ቅዳሜ ቀን ውሎ ነበር። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱም ለየአድባራቱ ሽልማት ልከው ካህናቱን ደስ አሰኟቸው። ሽልማቱ ካባና አብደላከኒ ቀሚስ ጃኖ ወይም ድርብ (እንደየማዕርጉ) የብር መቋሚያና የብር ጸናጽል ነው። እኔ ትክለኛ ለሆንኩለት ለአቦ ደብርም የዓሥር ሰዎች ሽልማት ተልኮልን ዓሥር ሰዎች ተሸለምን። ከተሸላሚዎቹ መካከል ወጣቶች የነበርነው ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ፣ ገብረ እግዚአብሔር ኤልያስ፣ ኢየሱስ ዓይኔ፣ ወልደ መስቀል፣ እሸቴ ክንፌና እኔ ራሴ ስንሆን የቀሩት አራቱ ሰዎች እነ አለቃ መርዓዊን የመሰሉ ሽማግሌዎች ነበሩ። አባቴም የትምህርቴን ደረጃ ብቻ ሳይሆን ሽልማቴንም ስላዩ ደስ ብሏቸው ወደ አገራቸው ወደ ጅሩ ተመለሱ።

በዚሁ ወራት ትምህርቴ ከሐዋርያ መልእክት ደርሶ ነበርና ከቀድሞው ይልቅ ትምህርቱን ስለተላመድሁት በማጥናት ረገድ ምንም እንኳ ከዕውር ወልደ ጊዮርጊስ ደረጃ ባልደርስ ወደዚያው ለመጠጋት እሞክር ጀመር። አንድ ቀን የዮሐንስን መልእክት በመማር ላይ ሳለሁ አስተማሪዬ ጉባኤውን አንድ ጊዜ ተረጉመውልኝና ከጉባኤው ተመልሼ ቀጸልሁት። ባንድ ጊዜ ስለአጠናሁትም ወደ የኔታ ተመልሼ ሌላ ጉባኤ አነበብሁ። እሳቸውም "ምነው ልጄ የፊተኛውን



አትደግመውም ወይ?" ብለው ቢጠይቁኝ "ስላጠናሁት ይበቃኛል ብዬ ነው" አልኋቸው። የሰጡኝም መልስ "አንተ ብታጠናው እኔ ላላጠናሁትምና እንደገና ድገመው" የሚል ስለሆነ ደገምሁት። ይኸውም እንደ ዕውር ወልደ ጊዮርጊስ በትዕቢት እንዳልጠመድ ሊመክሩኝና ሊያሳስቡኝ ስለፈለጉ ነው። በሁዳዴው ቀለምሲስን[109] ጨረስሁ። በዚህም ጊዜ እኔና ጓደኛዬ ወልደ ጻድቅ ከመቅድመ ወንጌል በስተቀር መጻሕፍተ ሐዲሳትን ስለጨረስን ክላሽ ጀመርን።

## የተስቦ በሽታ በተማሪ ቤቱ ስለመግባቱ

በዚህ ዓመት ፋሲካ ሚያዝያ 27 ቀን ዋለ። ከበዓሉም በኋላ አስተማሪያችን መኖሪያቸውን ወደ ንቡረ እድ አድማሱ ግቢ አዛውረው ያስተምሩን ጀመር። በግንቦት ወር የተስቦ በሽታ በዚያ ሰፈር መግባቱን ሰማንና ሥጋት አደረብን። ቀጥሎም ዕውር ወልደ ጊዮርጊስ በተስቦ በሽታ ታሞ ተኛ። በዚህ ጊዜ የኔታ ጉባኤውን አቁሙና በሽታው እስኪያልፍ ድረስ አትምጡ ብለው መለሱን። እርሳቸው ግን ዕውር ወልደ ጊዮርጊስን በቤታቸው አስተኝተው ያስታምሙት ጀመር። ሕመሙ እየጸናበት ሄዶ ቅዠት መቃዠት ጀመረ። እርሳቸው እንደነገሩን በቅዠቱ ላይ «ምንተ ያሰልጥ ደምየ ለእመ ወረድኩ ውስተ ሙስና፣ መሬትኑ የአምነከ ወይነግር ጽድቀከ»[110] እያለ ይለፈልፍ ነበር። በዚህ አኳኋን ሕመሙ ጸንቶበት አምስት ቀን ያህል እንደታመመ ታላቁ ሰው ወልደ ጊዮርጊስ ሞተ። ዋ፣ የሰው ነገር ያሳዝናል። አስተማሪያችን በርሱ መሞት ከፉኛ አዘኑ። እኛም የትምህርት ጓደኞቹ እንላቀስ ጀመር።

ከዚህ በኋላ ለአለቃ ወልደ አማኑኤል ላክንባቸውና እርሳቸው ከሰፈራቸው ሣጥንና ቀባሪ ሰው ይዘው መጥተው ወደ አዲስ አበባ ተክለ ሃይማኖት ወሰድነው። በዚያም የደብሩ ሹም አለቃ ወልደ ትንሣኤ ካህናቱን ሰብስበው በሚገባ ፍትሐት አስፈቱትና ተቀበረ። አለቃ ወልደ አማኑኤል ባለብዙ ወገን ስለሆኑ ኀዘን አግኝቷቸዋል ማለትን የሰሙ መኳንንትና ካህናት እየመጡ አስቀበሩ። ከመኳንንት ንቡረ እድ አድማሱና ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል እንደ ነበሩ አስታውሳለሁ።

---

[109] ራዕየ ዮሐንስ፣ ከምዕራፍ 1 እስከ 21 ድረስ ያለው።

[110] ትርጉሙ
ወደ ጥፋት ብወርድ ደሜ ምን ግዳጅ ይፈጽማል?
አፈር ያመሰግንሃልን ? እውነትህንስ ይናገራልን? (መዝ. 29 (30)፣9)
ምሥጢሩ
መዝሙረኛው ዳዊት ሞትን በመፍራት ወደ ፈጣሪው «እኔ ብሞትና ወደ መቃብር ብወርድ፣ ደሜም ቢፈስስ ምን ፋይዳ ይፈይዳል? ሥጋዬንም አፈር ቢበላው እኔን ስለ ሰጠኸው ቸር ነህ ብሎ ያመሰግንሃል ወይ?» ብሎ ሞት እንዲቀርለት እንደ ጸለየ ወልደ ጊዮርጊስ የተባለው ታላቅ ሰው ሞቶ በሚያጣጥርበት ጊዜ ሞትን ፈርቶ ይህን የዳዊት ጸሎት በቅዠት መልክ ሲናገር ተደምጧል። ይኸውም ያንገበበበት ሞት እንዲቀርለት ይመስላል። ምንጭ - መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ።

## ወደ ሐረር ስለመውረዴ

የዕውር ወልደ ጊዮርጊስ ሞት ሁላችንንም ስላስደነገጠን በሽታው እኛንም እየጠበቀ የሚያንቀን መስሎን ፈራን። ስለዚህም የትምህርት ጓደኛዬ ወልደ ጻድቅ ወደ እኔ መጥቶ "ወደ ሐረር ብንወርድና ክረምቱን እዚያ ከርመን በመስከረም ብንመለስ ይሻላል።" ብሎ ምክር አቀረበልኝ። ለመሄድ የምንችልበትንም ምክንያት እንዲህ እያለ አደራጀው። "አለቃ ገብረ ክርስቶስ የአባትህ የአለቃ ወልደ ቂርቆስ ደቀ መዝሙር ናቸው። ከዚህም በላይ የአገርህ የጅሩ ሰው ስለሆኑ እኔንና ጓደኛዬን ይዘውን ይውረዱ ብትላቸው እምቢ አይሉህም" አለኝ።

አለቃ ገብረ ክርስቶስ (የቀድሞ ስማቸው ቀኝ ጌታ ባልከው) ባለፈው ዓመት ግንቦት 23 ቀን 1909 ዓ.ም. አደሬ ጢቆ ሥላሴን ተሾመው ሐረር ወርደው እንደነበረና አሁን በቅርቡም ለጉዳያቸው ከሐረር መጥተው አዲስ አበባ በወዳጃቸው በአቶ ሠርፀ መድኅን ቤት ይገኙ እንደ ነበረ እዚህ ላይ መግለጽ ይገባኛል።

ለአለቃ ገብረ ክርስቶስ የምናገረውንም ቃል ሲያስጠናኝ እንዲህ አለኝ። "ተማሪ ቤታችን በተስቦ በሽታ ምክንያት ስለተዘጋ ሥራ ፈትተን ተቀምጠናል፣ ስለዚህ እኔና ጓደኛዬ ክረምቱን ከእርስዎ ዘንድ የአፈ ወርቅ[111] ትርጓሜ ስንማር ለመክረም ፈልገናልና፣ እባክዎ ይዘውን ይውረዱ ብለህ ለምናቸው፣ እንዲህ ያልካቸው እንደሆነ ለአባትህ ወሮታ ሲሉ ይዘውን ይወርዳሉ" ብሎ መከረኝ። እኔም በአሳቡ ተስማማሁብትና በማግሥቱ ሄጄ ከዚህ በላይ በተጻፈው ዓይነት በለስላሳ አነጋገር ነገርኋቸው። እሳቸውም ምንም ሳያመነቱ "ለመሄድ ከፈለጋችሁ ምን ቸገረኝ፤ የፊታችን ቅዳሜ እሄዳለሁና ጧት ላጋር ጣቢያ ጠብቁኝ" ብለው ቀጠሮ ሰጥተውኝ ተመለስሁ።

ከዚህ በኋላ እኔና ጓደኛዬ ወልደ ጻድቅ አስተማሪያችንን የኔታ ወልደ ጊዮርጊስን ተሰናብትንና መጻሕፍታችንን ተሸክመን ሰኔ 1 ቀን ቅዳሜ ጧት ላጋር ጣቢያ ላይ እንጠባበቅ ጀመር። ወዲያው አለቃ ገብረ ክርስቶስ መጥተው የባቡሩን ትኬት በግማሽ ዋጋ አስቈርጠው ሰጡንና አብረን ተሣፍረን ተጓዝን። በማግሥቱ እሑድ ማታ ድሬዳዋ ስንደርስ የድሬዳዋ ሚካኤልን ቤተ ክርስቲያን የተሾሙት አለቃ ዳኜ (የቀድሞ ስማቸው ርእሰ ደብር ዳኜ) በደስታ ተቀብለው አስተናገዱን። ከድሬዳዋም ሰኞ ተነሥተን በዚያ በእንቅልቅል ፀሐይ ረሞጫውን እየረገጥን በእግራችን ተጓዝንና ማታ ሐረማያ ላይ አደርን። ከዚያም ተነሥተን ሰኔ 4 ቀን ማክሰኞ ሐረር ገባን።

---

[111] ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ከ340-400 ዓ.ም. የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ፤ አያሌ ድርሳናትንና ተግሣጾን የጻፈ። ድርሰቶቹ ወደ ግዕዝ ተተርጒመው የሃይማኖት መማርያ ሆነዋል።



ከከተማው ስደርስ አንድ አስደናቂ ነገር ገጠመኝ። በአዲስ አበባ ሳለሁ በሕልም እየተመላለሰ የሚታየኝ አንድ የቤት ሕንፃ በ«ጋ» ፊደል አምሳል ጎባባ ሆኖ የተሠራ ባለበረንዳ ነው። እኔም ምክንያቱ አልገባህ ብሎኝ ችላ ብዬው እኖር ነበር። ነገር ግን ሐረር በደረስሁብት በዚያ ቀን በአደሬ ጢቆ ከተማ ዳር ያንኑ ቤት አገኘሁትና እየገረመኝ ለጥቂት ጊዜ ቆሜ አየሁት። ይኸውም ቤት ልጅ ኢያሱ ቤተ መንግሥት ብለው አሠርተውት የነበረና ሳያስጨርሱት የቀረ መሆኑን ሰዎች ነገሩኝ። ሕልሙ ምንም እንኳ ሌላ ፍሬ ነገር ባይኖረው ቀደም ብዬ ቤቱን ማየቴ ብቻ አስገርሞኛል።

## ሐረር ላይ ሳለሁ

ሰኔ 6 ቀን ኀሙስ የዕርገት በዓል ነበረና አለቃ ገብረ ክርስቶስ ከካህናቱ ጋር ሊያስማምዱን ስለፈለጉ ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስደውን በዓምደ ወርቅ[112] በኩል ከነባሮቹ ለጥቆ አቆሙንና በደብተርነት እናገለግል ጀመር። ከዚያም በኋላ ለእያንዳንዳችን አንድ፣ አንድ፣ ዳውላ ማሽላ የወር ቀለብና ሁለት፣ ሁለት ቁፍነት ስላዘዙልን በአደሬ ጢቆ ሥላሴ ደንበኞች መሆናችን ታውቆ ሁሉም በቶሎ ለመዱን። እኛም የትምህርት ሞያችንን ለማስታወቅ በዜማና በቅኔው ላይ አለን አለን እንል ጀመር። እነርሱም መጽሐፍ ዐዋቂዎች አድርገውናልና አከባበሩን። በዚያ ደብር የነበረው የጣዕመ ዜማ ስልትና የደብተሮች ውብት በእውነት አስደንቆኛል። የአቋቋሙ መሪና አስተማሪ አለቃ ዘውግነህ በጐንደር የስመ ጥሩውን የሣህሉ ወልደ ተክሌንና የሩፋኤሎችን ባህል ተምሮና አጠናቆ የመጣ የሸዋ ሰው ነው። እኔና ጓደኛዬም በጣዕመ ዜማው ስለተደሰትን በሳምንት አንድ ጊዜ ወደ አለቃ ዘውግነህ እየሄድን አቋቋም ስንማር ከርመናል።

ዋናው ትምህርታችን የዮሐንስ አፈ ወርቅ ትርጓሜ ስለሆነ በዚያው ሰሞን አለቃ ገብረ ክርስቶስ ጉባኤ ከፍተው ይተረጕሙልን ጀመር። በጉባኤው ላይ ሦስት ሊቃውንት አለቃ ገብረ ክርስቶስ፣ አለቃ ለማ፣ ልጅ በለው ይገኙ ስለነበሩ ሦስቱም በየተራቸው መጽሐፍ ይተረጕሙ ነበር። መጀመሪያ አለቃ ገብረ ክርስቶስ አፈ ወርቁን ለእኛ ይተረጕማሉ። ከዚያም በኋላ አለቃ ለማ ሐዲሱን፣ ልጅ በለው ቄርሎስን እየተረጐሙ ሦስቱ ሊቃውንት በምሥጢረ መጻሕፍ ሲነጋገሩ ይውሉ ነበር። እኛም አፈ ወርቁን በቶሎ ለመጨረስ ስለፈለግን ከሁለት ላይ ከፍለን ድርሳኑን እኔ፣ ተግሣጹን ጓደኛዬ ወልደ ጻድቅ እያነበብን ሁለቱንም እንቀጽል ጀመር።

በዚህ ጊዜ በመጽሐፍ በኩል ብቻ ችግር አገኘን፣ በዚያ ዘመን አለቃ ገብረ ክርስቶስ የአፈ ወርቁን ንባብና ትርጓሜ እንዲያጽፉ አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ

---

[112] በስተቅድስት በኩል በሁለት በሮች መካከል የቆመ ዓምድ (ምሰሶ)።

ስለአዘዙአቸውና ሥራውን ስለጀመሩ የምንማርበትን መጽሐፍ ቁም ጸሐፊው አለቃ ሐዋዝ ለሥራ መሥሪያ ይወስድብን ነበር። ስለዚህም እኔ ደብተር ገዝሁና እየጻፍሁ (ሌሊት ጭምር በመብራት እየሠራሁ) የአፈ. ወርቁን ድርሳን በ17 ቀን ጽፌ ጨርሼ በእርሱ እያነበብን እንማር ጀመር፡ በዚህ ጽሕፈት ላይ ያደረግሁትን ትጋትና ፍጥነት ሲቃውንቱ ሰምተው አደነቁልኝ። ይኸውም ወደፊት ለሚመጣው ጊዜ እየተጠቀሰ ለሥራ እስከ መመረጥ ሲያደርሰኝ ሊታይ ነው (ገጽ 133)። በነሐሴ መጨረሻ አፈ. ወርቁን አንድ ጊዜ ዘለቅነውና ለክላሽ ተመለስንበት።

ጌታ አለቃ ገብረ መድኅን የሥላሴን በዓል ለማክበር ከአዲስ አበባ መጥተው ሐምሌ 7 ቀን ሰኞ በአደሬ ጢቆ ስለነበሩ በዚህ ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ አየኋቸው። የሥላሴም በዓል የሐረር እንደራሴ ደጃዝማች እምሩ ባለቤትና ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት ደምቆ ተከበረ። በመጨረሻም ታቦት ወጥቶ ዑደት ከታወደ በኋላ ታቦቱ በዐውደ ምሕረቱ ላይ እንደቆመ አንድ የደንብ ጽሑፍ እንደ ዓዋጅ ዓይነት በሕዝቡ ፊት ተነበበ። ጽሑፉም በአለቃ ገብረ መድኅን እጅ ከአዲስ አበባ የተላከ የአደሬ ጢቆ ሥላሴ የአስተዳደር ደንብ ነበር። በደንቡ ላይ የልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪና የሊቀ ጳጳሱ የአቡነ ማቴዎስ ማኅተም ታትሞበታል። ሕዝቡ ንባቡን ካዳመጠ በኋላ ለአደሬ ጢቆ ሥላሴ የተሰጠውን ማዕርግና ክብር እያደነቀ አልጋ ወራሽን አመሰገነ። አደሬ ጢቆ ሥላሴ ከዚያም በፊት በየካቲት 10 ቀን 1910 ዓ.ም. "ዳሩ እሳት መካከሉ ገነት" ተብሎ መስቀል ዞሮበት በገዳምነት የተከለለ መሆኑን ሰምቻለሁ።

## ስለ ሐረር ከተማ

ሐረር በዚያ ዘመን በጣም የደመቀችና ሕይወት ያላት ከተማ ነበረች። ብዙ ሕዝብ ይኖርባታል። ብዙ አዱኛም እንደነበረባት አስታውሳለሁ። ከተማው በሁለት ወንዞች መካከል ይገኛል። ወንዞቹ የከተማውን አካባቢ በአታክልትና በልምላሜ አስጊጠውታል። ጫትና ቡና፣ ብርቱካን፣ ሙዝ የአገሩ ጫካ ናቸው። ስለዚህም ነጋዴው በንግዱ ገበሬው በእርሻው ተደስቶና ክብሮ ይታይ ነበር።

እንደራሴው ደጃዝማች እምሩ[113] የመወደድና የመፈራት ግርማ ሰፍሮባቸዋል። ወምበሩ ፊታውራሪ አረጋይ ቢቾሬ ነገርን የማጣራትና የመፍረድ ሀብት

---

[113] በኋላ ልዑል ራስ። የአጼ ኃይለ ሥላሴ አብሮ አደግ ናቸው። አባታቸው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ዓባይነህ ነበሩ፣ እናታቸው ወይዘሮ መዝለቂያ የራስ መኰንን እኅት የወይዘሮ እኅተ ማርያም ልጅ ስለነበሩ የአጼ ኃይለ ሥላሴ የቅርብ ዘመድም ነበሩ። ከጠላት ወረራ በፊት የልዩ ልዩ ክፍለ ሀገር አስተዳዳሪ ሁነው አገልግለዋል። በጠላት ወረራ ጊዜ በሸሬ ግንባር የጦር አዛዥ ነበሩ። በሰሜን ግንባር ጦሩ ሲፈታ ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ በመዞር ለአንድ ዓመት ያህል የጥቁር አንበሳን ጦር መርተው ጎጀብ ላይ ከተማረኩ በኋላ ወደ ኢጣልያ ተወስደው እስከ 1935 ዓ.ም. ድረስ በእስረኛነት ቈይተዋል። ወደ ሀገር ከተመለሱ በኋላ የሰሜንና የበጌምድር ጠቅላይ ገዢ ሁነው ላጭር ጊዜ ከቈዩ በኋላ በተከታታይ በአሜሪካ እንዲሁም በሀንድ አገር

ግርጌ ማስታወሻው በሚቀጥለው ገጽ ይቀጥላል...



ተሰጥቷቸዋል። የዘብጥያው[114] ሹም አቶ የተሻ ወርቅም ለከተማው ዕድገት የሚጥር ብርቱ ሠራተኛ ነው። ይህን ሁሉ እያየሁ ክረምትን ሐረር ላይ በደስታ አሳለፍሁት።





25 ሐረር ከተማ 1920 ዓ.ም.

---

በአምባሳደርነት አገልግለዋል። በመጨረሻም በሶቪየት ዩኒየን አምባሳደርነት ተሾመው ሳይሄዱ ቀርተዋል። በ1953 ዓ.ም. በነጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትር አድርገናቸዋል ብለው አስታውቀው ነበር። ልዑል ራስ እምሩ በአስተዳዳሪነትና በጦር አዝማችነት እጅግ የተመሰገኑና የተከበሩ ነበሩ። ደርግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ በ1972 ዓ.ም. ሞተው ሥርዓተ ቀብራቸው አዲስ አበባ መንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ በክብር ተፈጽሟል።

[114] ወህኒ ቤት።

# ምዕራፍ 18

## 1911 ዓመተ ምሕረት

በሐረር ሳለሁ፣ ወደ አዲስ አበባ ስለመመለሴ፣ ስለ ልዩ ልዩ ነገር

### በሐረር ሳለሁ

*1911* ዓ.ም. ዘመነ ሉቃስ ረቡዕ ባተ:: በመስከረም ወር እኔና ጓደኛዬ ወልደ ጻድቅ ትምህርታችንን መከለስ ላይ ነን:: የቀድሞ ምክራችን በመስከረም ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ነበር:: አሁን ግን እኔ ለመመለስ ስፈልግ እርሱ መቅረትን ስለመረጠ አሳባችን የተለያየ ሆነ:: ስለዚህም እርሱ የኑሮውን ነገር ሲያደራጅ እኔም የጉዞዬን ነገር አዘጋጅ ጀመር:: ወልደ ጻድቅ በየሳምንቱ እሑድ ወንጌል ወይም ጳውሎስ እየተረጐመ ለሕዝብ ያሰማ ነበርና «ወልደ ጻድቅ ሐዲስ» የሚል የቅጽል ስም ወጣለት:: በሐረር ለመቅረት ያሰበውም በዚህ ዓይነት መንገድ ከሕዝበ ጋር ተስማምቶ ስለነበረ ነው::

እኔ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ያሰብሁት ስለ ሁለት ምክንያት ነበር:: አንደኛው ከአስተማሪዬ ከመምህር ወልደ ጊዮርጊስ መቅድመ ወንጌልን ለመማርና ሐዲስን ለማጠናቀቅ ሲሆን፣ ሁለተኛውም ወደ ቦሩ ሜዳ ለመሄድና ከመምህር አካለ ወልድ አረጋዊ መንፈሳዊን ለመማር ስለተመኘሁ ነበር:: አረጋዊ መንፈሳዊን ለመማር የፈለግሁበትም ምክንያት "ይህ መጽሐፍ የሚማረው ጠፍቶ ሊጠፋ ነው" እየተባለ ይወራ ነበርና ትምህርቱን ለማስቀረት ስል ነው:: በጐንደር ዘመነ መንግሥት ሕዝቅኤልና አቡሻክር[115] የሚማረው ታጥቶ ትርጓሜው ጠፍቶ ቀረ እየተባለ ይነገር ነበረና አሁንም የአረጋዊ መንፈሳዊ ትርጉም ጠፍቶ እንዳይቀር ከልቤ አስቤበት ነበር:: ይህን አሳቤን ለአለቃ ገብረ ክርስቶስ ብገልጥላቸው መልካም አስበሃል ብለው ወደዱልኝ::

በጥቅምት ወር የአፈ ወርቅ ትምህርቴን አቁሜ የመቅድመ ወንጌል ንባብ በደብተር እጽፍ ጀመር:: በዚህም ጊዜ ወልደ ጻድቅ ጋሼ የተባለ የአደሬ ጢቆ ሥላሴ ደብተራ በጽሕፈት ረዳኝ:: ይህ ሰው ዝቋላ ላይ ቅኔ እየተማረ ያደገ የሸዋ ሰው ነው:: ቅኔ በሚገባ ያውቃል፣ ጽሕፈትም ያሳምራል:: ወደ ሚሲዮኖችም እየተዘዋወረ የፈረንጅ ቋንቋ ለምዷል:: ከእኔ ጋር በክረምቱ ውስጥ ተዋውቀን ጓደኝነት ይዘን ነበርና መቅድመ ወንጌል ስጽፍ ባየኝ ጊዜ

[115] የቍጥር መጽሐፍ፤ የመዓልቱን፣ የሌሊቱን፣ የክረምቱን፣ የጾሙን፣ የዘመኑን፣ የበዓሉን አዋዋል የሚወስን::



"ወደፊት ስንለያይ እንድታስታውሰኝ እኔም ልጻፍልህ" ብሎና 12 ገጽ ጻፈልኝ:: ስለዚህም የእጅ ጽሕፈቱ በመጽሐፌ ላይ ሆኖ ወዳጅነቱን ሲያስታውሰኝ ይኖራል::

በሐረር ላይ ከተዋወቅኋቸው ሰዎች አለቃ ክፍሌና አቶ መታፈሪያ ፍሬው፣ ደብተራ ሀብተ ወልድ፣ ደብተራ አክሊለ ደጀን ከትዝታዬ የማይጠፉ ናቸው:: የፊተኞቹ ሦስቱ የላምዋሻ ተወላጆች ዘመዶቼ መሆናቸውን ተረድቻለሁ::

### ወደ አዲስ አበባ ስለመመለሴ

ወደ አዲስ አበባ የመመለሴ ነገር ከተቈረጠ በኋላ፣ አለቃ ገብረ ክርስቶስ ወደ ዕቃ ቤት ወሰዱኝና ዓሥራ አምስት ብር ሰጡኝ:: ይኸውም በደብተርነት የገበርሁበት የቆፍነት አበል መሆኑን አስታወቁኝ:: እንዲሁ ደግሞ አቶ መታፈሪያ ፍሬው ወዳለሁበት ስፍራ መጣና ለስንቅ ይሁንህ ብሎ የአምስት ብር መሐለቅ ሰጠኝ:: ከዚህ በኋላ ወዳጆቼንና ዘመዶቼን ተሰነባብቼ በጥቅምት 26 ቀን እሑድ ከሐረር ተነሣሁና ሐረማያ አደርኩ:: በማግሥቱ ሰኞ ድሬዳዋ ደርሼ ከአለቃ ዳኜ ቤት አደርሁ:: እሳቸውም ለባቡር መሣፈሪያ ብለው አምስት ብር ሰጡኝ:: ከዚህ በኋላ ረቡዕ ተሣፍሬ ኀሙስ አዲስ አበባ ገባሁ::

አዲስ አበባ እንደ ደረስሁ ከየኔታ ወልደ ጊዮርጊስ ዘንድ የመቅድመ ወንጌል ትርጓሜ እማር ጀመር:: ትምህርቱም ከአንድ ወር ተኩል የበለጠ አልወሰደብኝም:: ዳሩ ግን የኅዳር በሽታ[116] የተባለ መቅሠፍት በአገር ላይ ወርዶ ሕዝቡን ይፈጀው ነበርና ትልቅ ሥጋት አደረብኝ:: በሽታውም በየአውራጃውና በየወረዳው መዛመቱን ስለሰማሁ ወደ ቦሩ ሜዳ ለመሄድ ያቀድሁትን ሐሳብ ለሌላ ጊዜ አስተላልፌ የሐዲስ ትምህርቴን እየከለስሁ በአዲስ አበባ ተቀመጥሁ:: በዚህ ዓመት በትምህርት ቤታችን የነበሩት የሐዲስ ደቀ መዛሙርት ስምንት ያህል ነበሩ:: ከደቀ መዛሙርቱ ጥቂቶቹ ቀደምቶች

[116] በ1911 ዓ.ም. የበሽታ መቅሠፍት በኢትዮጵያ ላይ ወርዶ ብዙ ሰው አለቀ:: በሽታው አዲስ አበባ ደርሶ በጣም የታወቀው በኅዳር ወር ስለ ሆነ በሕዝብ ቃል "የኅዳር በሽታ" የሚል ስም ወጣለት:: ፈረንጆች ግን የበሽታውን ስም ግሪፕ ብለውታል:: በአገራችንም አንዳንድ ሰዎች "ቸነፈር" ብለውት ነበር:: በሽታው ቀደም ብሎ አውሮጳ ላይ በዓለም ጦርነት ምክንያት ስለ ተነሣና ብዙ ሕዝብ ስለ ፈጀ ይኸው ወሬ ከመስከረም ጀምሮ ተሰምቶ ነበር:: ወደ አገራችንም በነፋስ ተዛምቶ መጣና ከጥቅምት ጀምሮ ጥቂት በጥቂት በአንዳንድ ሰው ቤት መግባትና መጣል ጀመረ:: በኅዳር ወር ግን አብዛኛውን ሰው ስለ ነደፈው ከተማው ተጨነቀ:: በሽታው እንደ ጣልና እንደ ጉንፋን አድርጎ ይጀምርና በበሽተኛው ላይ ትኩሳት ያወርድበታል:: ከዚያም ሌላ ያስለቅሳል፣ ነስር ያስነስራል፣ ተቅማጥና ውጋት ያስከትላል፣ አንዳንዱንም አእምሮውን ያሳጣዋል:: እንዲህ እያደረገ በሦስት፣ በአራት ቀን ይገድለዋል:: ከአራት ቀን ያለፈ በሽተኛ ግን ከሞት ማዳረሱ (መዳኑ) ነው:: ሆኖም ከግርሻ መጠንቀቅ ነበረበት:: አንዳንድ ስፍራ ቤተሰቡ በሙሉ ይታመም ስለ ነበረ አስታማሚ በማጣት በረሀብና በውሓ ጥም ብዙ ሰው ተጐዳ:: ስለዚህ በአዲስ አበባ ከተማ በየቀኑ ሁለት፣ ሦስት፣ መቶ ከዚህም በላይ ይሞት ጀመር:: በአንድ መቃብርም ሁለቱን ሦስቱን ሬሣ እስከ መቅበር ተደረሰ:: አንዳንዶቹንም ሰዎች ሬሣ ተሸካሚ በመታጣት በየግቢያቸው ውስጥ ቀበሩዋቸው:: ምንጭ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ *የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ* ገጽ 218::

ስንሆን የቀሩት ጀማሪዎች ናቸው። ከጀማሪዎቹም መካከል ጐጃሜ ኃይለ ማርያም ጓደኛዬ ሆኖ ከረመ።

እንዲሁ ደግሞ አባ ኃይለ ኢየሱስ የተባሉ ሽማግሌ በጉባኤው ላይ ነበሩና በዚያው ጊዜ መርሐ ዕውርን[117] ዘለቁልኝ። እኒህ ሰው ከጐጃም የመጡ የሐዲስ ሊቅና መምህር ናቸው። አሁን የመጡትም የትምህርት ፍቅር አስገድዷቸው ሐዲሱን ለመከለስ ብቻ ነበር። በምግብና በመኖሪያ የሚረዷቸው የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ባለቤት ወይዘሮ አልታየ ወርቅ ስለሆኑ፣ ከዚያ እየተነሡ አራት ኪሎ ሜትር ያህል ወደ ተማሪ ቤታችን በየቀኑ ስለሚመላለሱ ትጋታቸውና ብርታታቸው እጅግ ያስደንቀኝ ነበር።

በዚህ ጊዜ ለጀማሪዎቹ ደቀ መዛሙርት እኛ ቀደምቶቹ ጉባኤ እንድናሄድላቸው የኔታ መድበው ስላዘዙን በየክፍላችን እናስቀጽል ጀመር። ለእኔ ከተመደቡት ጀማሪዎቹ የጊዮርጊሱ መሪ ጌታ ይነሡ፣ የገብርኤሎች ደብተራ ሥዩምና ስሙን የዘነጋሁት ጓደኛው የማጥናት ችሎታቸው አስደናቂ እንደ ነበረ አስታውሳለሁ።

## ስለ ልዩ ልዩ ነገር

በዚህ ዘመን 1911 ዓ.ም. ዕድሜዬ 20 ዓመት ስለሞላ ትምህርቴን ሳልተው ለግማሽ ቀን እየሠራሁ ደመወዝ የማገኝበትን መንገድ እፈልግ ጀመር። እንደ አጋጣሚም ገበየሁ መክብብ የተባለ የልጅነት ጓደኛዬ እንዲህ አለኝ። "ባያር የተባለ የፈረንሳይ ኩባንያ ወርቅና ብር ሌላም ማዕድን በኢትዮጵያ ውስጥ በየስፍራው ለመመርመር ፈቃድ አግኝቶ መጥቶ አዲስ አበባ ላይ ይገኛል። ሠራተኛ መሰብሰብና በትምህርት ማሠልጠን ጀምሯል። በትምህርቱም ወራት አምስት ብር ደመወዝ ይሰጣል፣ በፈተና ካለፈውም ወዲያው ይጨምርለታል፣ እኔ ራሴ እዚሁ ገብቻለሁና አንተም ከፈለግህ ልጠይቅልህ" አለኝ።

እኔም ስለ መልካም አሳቡ አመስግንሁትና እባክህ ለጓደኛዬ ለአቶ ዮፍታሔ ንጉሤ ጭምር ጠይቅለት ብዬ ለመንሁትና ተለያየን። ከዚህ በኋላ ገበየሁ ለሁለታችንም ጠይቆ ስፍራ ስለአገኘልን በየካቲት ወር ገብተን ተጻፍንና ትምህርቱን ጀመርን። ተማሪ ቤቱ የተከፈተው መጀመሪያ በቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስ ግቢ በአንድ ቤት ውስጥ ነበር። በኋላ ግን ሊሲያንስ ወደሚባለው

[117] የመርሐ ዕውር ትምህርት በኢትዮጵያ ሊቃውንት ዘንድ እራሱን የቻለ የቍጥር ትምህርት (የዘመን አቈጣጠር ስልት) ነው። በ17ኛው ምዕት አጼ ሱስንዮስ የካቶሊክን ትምህርት ከተቀበሉ በኋላ መርሐ ዕውር መጽሐፍ እንዲጠፋ አዝዞ ነበር። ዓቃቤ ሰዓት አቦም የሚባል ሊቅ መጽሐፉን ይዞ በረሃ በመሄድ እዚያ ትምህርቱን እያስላሰለ ጊዜው እስኪያልፍ ድረስ ቈይቷል። አጼ ፋሲለደስ ከነገሡ በኋላ የእስክንድርያ ሃይማኖት ሲመለስ ከበረሃ ወጥቶ የመርሐ ዕውርን ትምህርት አስፋፍቶታል። ምንጭ - ሥርግው ሀብለ ሥላሴ፣ የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት፣



ወደ ካቶሊኮች ተማሪ ቤት ተዛወረ። ትምህርቱ በሳምንት ሦስት ቀን ብቻ ሲሆን የትምህርቱ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ10 እስከ 12 ሰዓት ብቻ ነበር። የትምህርቱ ዓይነት የማዕድኖችን ስም የሚዘረዝርና ጠባያቸውን የሚያስረዳ ከፈረንሳይ ወደ አማርኛ የተተረጐመ ቃል ነው። «ኮንግሎሜራ» የሚለውን ቃል የቀልድ ጥቅስ አድርገነው ነበር።

ለትምህርቱ ሥራ ዲባቸው የተባለ ፈረንሳዊኛ የሚያውቅ ኢትዮጵያዊ ተቀጠረና ትምህርቱን በጥቁር ሳንቃ ላይ እየጻፈ ያስገለብጠን ጀመር። እኛም ከዚያ ላይ እየቀዳን በቃል ማጥናት ነበረብን። እንግዲህ የቃል ጥናቱ ለሌሎች ምንም እንኳን ቢከብድ እኛ ግን በግዕዝ ትምህርት ተለማምደነዋልና አልተቸገርንበትም። በወሩ መጨረሻ ፈተና ሆኖ አስተማሪው ሲጠይቀን ሁሉንም በቃላችን አነበብንለት። በዚህ ጊዜ አስተማሪው ዲባቸው ከፍተኛ ቍጥር ስለሰጠን ፈረንጁም ቀለባችንን ሰባት፣ ሰባት ብር ቈረጠልን። በዚህ ዓይነት ደሞዝ እየተቀበልን ስንማር ሦስት ወር ከቈየን በኋላ ኩባንያው በግንቦት መጨረሻ ሥራውን አቆመብንና ትምህርቱም ደመወዙም ቀረ። ሥራው የቆመበትን ምክንያት በትክክል አላውቀውም። ሆኖም ኩባንያው ፈቃድ ያገኘው ከልዑል አልጋ ወራሽ ብቻ ስለነበረና ንግሥት ዘውዲቱና ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ በፈቃዱ ስላልተስማሙበት ነው እየተባለ ሲወራ ሰምቻለሁ።

ከዚህ በኋላ አቶ ዮፍታሔ በሊጋባ ክፍል ተጠያይቆ የገንዘብ አስገቢነት ሥራ ለማግኘት የክፍሉን ሹም አቶ መልአኩ ወንድም የተባለውን ደጅ ይጠና ጀመር። እኔ ግን ምንም ለማግኘት ስላቃተኝ የሐዲስ ትምህርቴን እየቀጠልሁ ተቀመጥሁ።

በዚህ ጊዜ በተማሪ ቤታችን የሆነውንም ልጽፈው እወዳለሁ። በገጽ 126 ስማቸውን የጠቀስሁት ሽማግሌው አባ ኃይለ ኢየሱስ ጳውሎስ እያነበቡ ሲቀጽሉ ከርመው ነበር። በሐምሌ ወር ከዕብራውያን መልእክት ደርሰው ነበርና አንድ ቀን «ሃይማኖትሰ ጥይቅት ይእቲ ለዘይሴፈዋ . . .» የሚለውን ጉባኤ አንብበው ካስተረጐሙ በኋላ፣ «ምንተ እንከ እብል እስመ ኀፀር ዕለትየ ከመ እዜንክሙ በእንተ እለ ጌዴዎን፣ ወባርቅ፣ ወዮፍታሄ . . .»[118]

[118] ትርጉሙ
ሃይማኖትስ ተስፋ ለሚያደርጋት የተረዳች ናት . . . (ዕብ. 11፥ 1)
እንግዲህ ምን እላለሁ? የእነ ጌዴዎንን፣ የእነ ባርቅንና የእነ ዮፍታሔን ፣ . . . ነገር እነግራችሁ ዘንድ ቀን ያጥረኛልና። (ዕብ. 11፥ 31-32)
ምሥጢሩ
ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቱን ለጻፈላቸው ዕብራውያን (እስራኤላውያን) ለእምነት ጽናት ምሳሌ የሚሆኑ ሰዎችን በዝርዝር መናገር ጀምሮ ሳለ ሁሉንም ለማከተት ጊዜ ስለሚያጥረው ስድስቱን ያህል ጠቅሶ ሌሎቹን ትቷል ። አባ ኃይለ ኢየሱስ ወደ ዕብራውያን የተጻፈውን መልእክት እያጠኑ ሳሉ ምዕራፍ 11 ቍጥር 32 ላይ «ቀን ያጥረኛል» ከሚለው ሲደርሱ ታመው በመሞታቸው ቅዱስ ጳውሎስ «የሃይማኖት

ዝርዝር ማስታወሻው በሚቀጥለው ገጽ ይቀጥላል...

የሚለውን አርእስት ሰጥተው ወደ ቤታቸው ሄዱ። (ዕብ. 11:32)። በማግሥቱ ሆድ ዝማ (ተቅማጥ) አሟቸው ኖሮ ወደ ጉባኤው ሳይመጡ ቀሩ። በተከታዮቹም ሁለት ቀኖች እንዲሁ ስለቀሩ፣ የኔታ ሰው ልከው ቢያስጠይቁ ሆድ ዝማው በብርቱ ያመማቸው መሆኑን ሰሙና ሄደው ጐበኟቸው። በአራተኛውም ቀን፣ ሐምሌ 27 ቀን አባ ኃይለ ኢየሱስ ሞቱ የሚል ወሬ መጣልንና ሁላችንም ሄደን በተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አስቀበርናቸው። የኔታ በዚህ ቀን ለዕውር ወልደ ጊዮርጊስ ካደረጉለት ያላነሰ ኀዘን አደረጉላቸው። እኛም ከላይ የጠቀስሁትን የአርእስቱን ቃል እያስታወስንና እየተደነቅን አዘንላቸው። የተደነቅንበትም ምክንያት እላይ እንደጻፍሁት የቃሉ ትርጉም «ቀን አጥሮብኛልና እንግዲህ ምን እላለሁ» የሚል ስለሆነና ቃሉና ሞታቸው ስለተጋጠመ ነበር።

---

ጀግኖችን ሁሉ ለመጻፍ ቀን ያጥረኛል» ካለው ጋር ተነጻጽሮአል። ምንጭ - መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ።

# ምዕራፍ 19

## 1912 ዓመተ ምሕረት

በትምህርት ቤቴ ሳለሁ፣ ስለ መምህር አካለ ወልድ ሞት፣ ስለ መጻሕፍት ትርጓሜ ድርጅት፣ ስለሥራ ስለመጠራቴና ስለመግባቴ፣ ስለ ልዩ ልዩ ነገር

### በትምህርት ቤቴ ሳለሁ

1912 ዓ.ም. ዘመነ ዮሐንስ ዓርብ ባተ። በዚህም ዓመት የትምህርት ቤት ኑሮዬንና ትምህርቴን እንደቀጠልሁ ነኝ። አስተማሪዬ የኔታ ወልደ ጊዮርጊስ ጥበብን ለመቅሰም የማይበዝኑ ትጉህ ሰው ስለሆኑ፣ የ64 ዓመት ዕድሜ በነበሩበት በዚያ ጊዜ ከአቶ ዮሐንስ ወልደ ማርያም እንግሊዝኛ ለማጥናት ሲመላለሱ ያስከትሉኝ ነበር። አቶ ዮሐንስ ወልደ ማርያም በስዊድን ሚሲዮን የሚያስተምሩ የሸዋ (የቱጉለት) ሰው ናቸው። የኔታ ፊደሉን አጥንተው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የዮሐንስን ወንጌል በእንግሊዝኛ እያነበቡ ቋንቋ ሲለማመዱበት አየሁና "ይህ ትምህርት ለምን ይረባል" ብዬ ብጠይቃቸው "ብዙ ጥበብ የተጻፈበት ቋንቋ ስለሆነ ለብዙ ነገር ይጠቅማል፤ በመንፈሳዊ በኩል ብዙ መጻሕፍት ተጽፈውበታል" ብለው መለሱልኝ። እኔ ግን ከግዕዝ ትምህርት በቀር ሌላ ጠቃሚ ትምህርት ይገኛል የሚል ሐሳብ አልነበረኝምና ከየኔታ የሰማሁት ቃል አስገርሞኝ ፊደሉን ተመለከትሁት። ቀጥሎም ገና ጀማሪዎች የነበሩትን የአቶ ዮሐንስን ልጆች እንግዳንና ገብረ እግዚአብሔርን እየጠየቅሁ ፊደሉን አጠናሁት። ይሁን እንጂ የአረጋዊ መንፈሳዊ ትምህርት ገና ከአሳቤ ስላልተለየ እንደ ትምህርት ልቈጥረው አልፈለግሁም ነበር።

### ስለ መምህር አካለ ወልድ ሞት

የአራቱ ጉባኤያት[119] አስተማሪ መምህር አካለ ወልድ ኅዳር 9 ቀን 1912 ዓ.ም. ረቡዕ በሩ ሜዳ ላይ ዐረፉ። እርሳቸው የወሎ ሐዋርያ ሆነው አርባ አንድ ዓመት የኖሩ መምህር ናቸው። ሞታቸው አዲስ አበባ ላይ በተሰማ ጊዜ ኀዘን ተደረገላቸው። በዚያም ሰሞን እሑድ ቀን በመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የሬሣ ምሳሌ ቃሬዛ ተደርጎ ልዑል አልጋ ወራሽና አቡነ ማቴዎስ ባሉበት መኳንንትና ሊቃውንት በተሰበሰቡበት የጕዞ ፍትሐት[120] ውሎ ተዋለላቸው። ለነዚህ ዋና ሆነው እንግዶችን የተቀበሉ የወንድማቸው የአለቃ እስጢፋኖስ

---

[119] መጻሕፍተ ብሉያት፣ ሐዲሳት፣ ሊቃውንትና መነኮሳት።

[120] አስከሬን ከቤት ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚሄድበት ወቅት በመንገድ ላይ እያረፈ ለሟቹ የሚጸለይ ጸሎት። ይህ ጸሎት በአንድ ቦታ ከሚደረግ ፍትሐት የላቀና የሚደረገውም ለተከበሩ ሰዎች ነው።

ልጅ መልአከ ፀሐይ ኤስድሮስ (የቀድሞ ስማቸው መልአከ ፀሐይ አፈ ወርቅ) ነበሩ። በዚህ ቀን የክስተት አርያም[121] ድርሰት ተደርሶ ነበርና ብዙ ቅኔ ሲወርድ ዋለ።

ከዚህም በኋላ በእንጦጦ ማርያምና በትልልቆቹ አድባራት ሰዓተ ሌሊት ተቆመላቸው። አርባቸው በታኅሣሥ 18 ቀን ሆኖ ነበርና በጾሙ ምክንያት ወደፊት ተላልፎ መልአከ ፀሐይ ኤስድሮስ የአዲስ አበባን አድባራት ጠርተው በጥር 2 ቀን ከፍ ያለ ተዝካር አበሉ።

ከአሁን በፊት እንደጻፍሁት ወደ ቦሩ ሜዳ ለመሄድና ከመምህር አካለ ወልድ "አረጋዊ መንፈሳዊ"ን ለመማር በብርቱ ተመኝቼ ነበር (ገጽ 124-127)። አሁን ግን እርሳቸው ስለሞቱ ምኞቴ የቀረ ነገር ሆኗል። ሆኖም እግዚአብሔር በጥበቡ ያደራጀልኝ ሌላ ነገር ወደፊት ሲያጋጥመኝ ነው (ገጽ 132)።

## ስለ መጻሕፍት ትርጓሜ ድርጅት

ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ለማጻፍና ለማሳተም ስላሰቡ በ1910 ዓ.ም. በታኅሣሥ ወር የትርጓሜ ማሰናጃ ድርጅት አቋቁመው ነበር። የሥራው መሪ አለቃ ገብረ መድኅን ሆነው በትልቁ ቤተ መንግሥት ግቢ በተሰጣቸው በማረፊያ ቤታቸው ሥራው ተጀመረ። ከአዲስ አበባ ግራ ጌታ ወልደየስና አለቃ ገብረ አብ፣ አለቃ ጠብቄ ተጠርተው ፍትሐ ነገሥቱን በንባብና በትርጓሜ ወዲያው ያጽፉ ጀመር። ለሥራው ተስማሚ የሆኑ ቁም ጸሐፊዎችም ከየስፍራው ተመርጠው ተቀጠሩላቸው።

ከአዲስ አበባ ውጭ ለሆኑትም ሊቃውንት ሥራውን በየሞያቸው እየመደቡ በልዩ ልዩ ጊዜያት ላኩላቸው። ለምሳሌ የአፈ ወርቁን ንባብና ትርጓሜ የሐረሩ አለቃ ገብረ ክርስቶስ እንዲተረጉሙትና እንዲያጽፉት ታዘዙ። መጽሐፈ ስሎሞን ለአለቃ ክፍሌ ማረፊያ ተሰጠ። ማር ይስሐቅና[122] ፊልክስዮስ ሌላም መጽሐፍ በደብረ ሊባኖስና በሌላ ስፍራ እንዲዘጋጅ ተደረገ።

አረጋዊ መንፈሳዊን መምህር አካለ ወልድ እንዲተረጉሙትና እንዲያጽፉት ልዑል አልጋ ወራሽ ከዚህ በታች ያለውን ደብዳቤ ልከውላቸው ነበር።

> የኢትዮጵያ መንግሥት
> አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ

[121] ሰማይ መከፈት፣ የዜማ ስም። በታላቅ በዓል ቀን እንዲሁም ታላላቅ ሰዎች ሲሞቱ የሚዘመር ነው።

[122] በማር ይስሐቅ (Issac of Neneveh, Nestorian Bishop) ዕለተ ዕረፍቱ (700 ዓ.ም. እንደ ፈረንጅ አቈጣጠር) የተደረሰ፣ ከሦስቱ መጽሐፈ መነኮሳት አንዱ። ሌሎቹ ሁለት መጻሕፍት አረጋዊ መንፈሳዊና ፊሊክስዩስ ናቸው።



> ይድረስ ከመምህር አካለ ወልድ እንዴት ሰንብተዋል፣ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ። አሁን ዛሬ በድካምዎ ላይ ይህን ማዘዝ አይገባም ነበር። ነገር ግን ምንም ባልረሳዎ ለዘወትር ለሃይማኖት አባትነትዎ መታሰቢያ የሚሆነኝን አረጋዊና መንፈሳዊ መጽሐፍ ንባቡን ከነትርጓሜው አስጽፈው ይላኩልኝ። ጸሐፊውንና ብራናውን ከቢትወደድ ወሌ ዘንድ እንዲሰጥዎ ልኬባቸዋለሁ። ያጻጻፉም ዓይነት ንባብ ንባቡ በቀይ፣ ትርጓሜ ትርጓሜው በጥቁር እየሆነ እንዲጻፍ።
>
> ግንቦት 15 ቀን 1911 ዓ.ም. አዲስ አበባ።

መምህር አካለ ወልድ በዚህ ትእዛዝ መሠረት አረጋዊ መንፈሳዊን ማጻፍ ጀምረው ሳለ በኅዳር 9 ቀን 1912 ዓ.ም. ስለሞቱ ሥራው በጅምር ቀርቶ ነበር። የአርባ ተዝካራቸው ከወጣ በኋላም ቤተሰቦቻቸው ጅምሩን መጽሐፍ ይዘው መጥተው በጥር ወር 1912 ዓ.ም. ለልዑል አልጋ ወራሽ አስረከቡ። ልዑል አልጋ ወራሽም ጅምሩን ማን ሊፈጽመው እንደሚችል አለቃ ገብረ መድኅንን ቢጠይቁ ለዚህ ሥራ ችሎታ ያላቸው የመምህር አካለ ወልድ ደቀ መዝሙር መምህር ደስታ[123] ናቸው፣ አሁን ያሉትም መርጦ ላይ ነው ብለው መለሱላቸው።

በኋላ ጊዜ እንደሰማሁት የልዑል አልጋ ወራሽ ትእዛዝ በስልክ ወደ መርጦ ከተማ ተላልፎ መምህር ደስታ ተጠሩ። አዲስ አበባም ሲደርሱ ከሥዕል ቤት በስተምሥራቅ የሚገኝ አንድ ትልቅ ማረፊያ ቤት ተሰጣቸውና ከነደቀ መዛሙርታቸው ተቀምጠው ያስተምሩ ጀመር። ከልዑል አልጋ ወራሽ ፊት በቀረቡ ጊዜም "አሁን የጠራንዎት አባትዎ መምህር አካለ ወልድ የጀመሩትን የአረጋዊ መንፈሳዊ ትርጓሜ እርስዎ እንዲጨርሱት በማለት ነው" አሏቸውና ጅምሩን አቅርበው አሳዩዋቸው።

መምህር ደስታ ቅንና የዋህ፣ እውነት ተናጋሪ ስለሆኑ እንዲህ ሲሉ መለሱ። "ትርጓሜውን መተርጐምና ማስተማር እችላለሁ፣ ነገር ግን እየተረጐምሁ እጽፋለሁ ያልሁ እንደሆነ ያስቸግረኛልና እኔ እየተረጐምሁለት ተምሮ የሚጽፍ ደቀ መዝሙር ቢሰጠኝ እወዳለሁ" ብለው አሳባቸውን ገልጸው አስታወቁ።

ልዑል አልጋ ወራሽ መምህር ደስታን አነጋግረው ከአሰናበቱ በኋላ ለዚህ ሥራ የሚሆን ሰው ይፈልጉ ብለው አለቃ ገብረ መድኅንን አዘዟቸው። እሳቸውም በማፈላለግ ሳሉ አለቃ ገብረ ክርስቶስ ከሐረር ወደ አዲስ አበባ መጥተው ነበርና ይህንኑ አንሥተው ያጫውቷቸዋል። አለቃ ገብረ ክርስቶስም ለዚህ ሥራ የሚሆን መርስዔ ኀዘን ነው ካሉ በኋላ የሚከተለውን ጨማምረው ያነግሩዋቸዋል።

"ይህ ልጅ የአለቃ ወልደ ቂርቆስ ልጅ ነው። ሐዲስ ከመምህር ወልደ ጊዮርጊስ ተምሯል። ባለፈው ዓመት ከእኔ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ሲቀጽል ከርሞ ነበር።

[123] በኋላ አቡነ አብርሃም።

በኋላ ግን ወደ ቦሩ ሜዳ ሄጄ ከመምህር አካለ ወልድ መጽሐፈ መነኮሳትን እማራለሁ ብሎ ነግሮኝ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ። አሳቡም የአረጋዊ መንፈሳዊ ትርጓሜ ጠፍቶ እንዳይቀር ለመማርና ትምህርቱን ለኋላ ልጅ ለማስቀረት ነው። በጽሕፈትም ረገድ ፈጣን ነው። እኔ ዘንድ በነበረበት ጊዜ የአፈ ወርቁን ድርሳን በጥቂት ቀን ውስጥ ጽፎ ይቀጽልበት ነበር። እንግዲህ ወደ ሩቅ ስፍራ ሄዶ ሊማር የፈለገውን ትምህርት አሁን በቅርብ ካገኘው ደስ ሳይለው አይቀርምና እርሱን ቢያሠሩት ይሻል ይመስለኛል" ይሏቸዋል።

አለቃ ገብረ መድኅን ከዚህ በፊት ስለኔ የሚያውቁት ነገር አልነበረምና ያለበትን ስፍራ አስጠይቀህ አስታውቀኝ ይሏቸዋል። አለቃ ገብረ ክርስቶስም መኖሪያዬን አጠያይቀው በአስተማሪዬ በመምህር ወልደ ጊዮርጊስ ዘንድ መሆኑን ስለተረዱት ይህንኑ ነግረዋቸዋል።

## ስለሥራ ስለመጠራቴና ስለመግባቴ

አለቃ ገብረ መድኅን ከልዑል አልጋ ወራሽ ዘንድ ቀርበው ለአረጋዊ መንፈሳዊ ሥራ አንድ ደቀ መዝሙር ተገኝቷል ብለው አስታወቁ። ልዑል አልጋ ወራሽም፣ "ከልካዮች ይጥሩና ያምጡት" ብለው ስላዘዙ አድራሻዬ የተነገራቸው ሁለት ከልካዮች በየካቲት 6 ቀን ቅዳሜ ጧት ከየኔታ ወልደ ጊዮርጊስ ቤት ደርሰው "መርስዔ ኀዘን የሚባል ማነው?" ብለው ጠየቁ። የኔታም "ለምን ትፈልጉታላችሁ" ቢሏቸው "ምክንያቱን እኛ አናውቅም ጠርታችሁ አምጡት የሚል ትእዛዝ ብቻ ተቀብለናል" ብለው መለሱላቸው። በዚህ ጊዜ እኔና ጓደኞቼ የኔታም መሥጋታችን አልቀረም ነበር። የሆነ ሆኖ የከልካዮቹን ትእዛዝ መቀበል ግዴታ ስለሆነ ይዘውኝ ወደ ግቢ ወሰዱኝና ከአንድ አለቃቸው ፊት አቀረቡኝ። እርሱም ወደ አለቃ ገብረ መድኅን ውሰዱት ስላላቸው ከእርሳቸው ማረፊያ ቤት አድርሰውኝ ተመለሱ።

በዚያ ሰዓት አለቃ ገብረ መድኅን በማረፊያ ቤታቸው ከአለቃ ገብረ ክርስቶስና ከሌሎች ሰዎች ጋር ንግግር ይዘው ነበር። ጥቂት እንደጠበቅሁ ተጠርቼ ገባሁና እጅ ነሥቼ ቆምሁ። የሰላምታ ቃል ከተናገሩኝ በኋላም "ያስጠራሁህ አልጋ ወራሽ ለሥራ ስለፈለጉህ ነው። አሁን ወስጄ አገናኝሃለሁና ሥራውን እርሳቸው ይነግሩሃል" አሉኝ። እኔም የምናገረውን አጥቼ ዝም ስላቸው ጊዜ ግራ እንደገባኝ ተሰማቸውና "አይዞህ አትደንግጥ የምትሠራው ከእኔ ጋር ነው" አሉኝ።

ከዚህ በኋላ ወደ ግቢ ገብተው አስጠሩኝና ከልዑል አልጋ ወራሽ ፊት አቀረቡኝ። ወደ መሬት አጎንብሼ እጅ ከነሣሁ በኋላ ቀጥሎ ያለው ቃል ከልዑልነታቸው ተነገረኝ።

"አሁን ያስጠራንህ አረጋዊ መንፈሳዊን ከመምህር ደስታ እየተማርህ ንባቡንና ትርጓሜውን እንድትጽፍልን ነው። አንተም ይህን ትምህርት ፈልገኸው እንደ



ነበረ ሰምተናልና ደኅና አጋጣሚ ሆኖልሃል፣ የድካምህን ዋጋ እናስቀርብህም፣ ባልደረባህም አለቃ ገብረ መድኅን ናቸው" አሉኝና መሬት ስሜ ተመለስሁ።

ከግቢው እንደወጣሁ አለቃ ገብረ መድኅን "ነገ ና" ብለው ቀጠሮ ሰጥተውኝ ወደ ትምህርት ቤቱ ተመለስሁ። እዚያም ስደርስ የሆነውን ነገር ሁሉ ለየኔታና ለጓደኞቼ ነገርኋቸውና ደስ አላቸው።

በማግሥቱ የካቲት 7 ቀን (እርሱም የሁዳዴ ቅበላ እሑድ ነበር) መጻሕፍቱን ይዤ ወደ አለቃ ገብረ መድኅን ዘንድ ሄድሁ። እሳቸውም መጀመሪያ ከአባ ወልደ ማርያም[124] ጋር አስተዋወቁኝ። ቀጥሎም ነባሮች ሆነው ከቈዩት ደቀ መዛሙርት ከክንፈ ርግብና ከወልደ ኪዳን ጋር አገባጠሙኝና ወደ ማረፊያ ክፍል እንዲወስዱኝ አዘዟቸው። ድርጎ ታዘዘልኝ፣ የመኝታ ቤትም ተሰጠኝ፣ እንዲሁ ደግሞ የምማርበት መጽሐፍ አንድ ትልቅ አረጋዊ መንፈሳዊ ተሰጠኝ። እንግዲህ አዲሱ የኑሮዬ ደረጃ በዚህ ቀን ተጀመረ።

የካቲት 8 ቀን ሰኞ በኣተ ጾም[125] ሆነ (ሁዳዴ ገባ)። ከጧቱ ሦስት ሰዓት ሲሆን አለቃ ገብረ መድኅን ወደ መምህር ደስታ ጉባኤ ወስደው አስተዋወቁኝና አረጋዊ መንፈሳዊ ጀመርሁ። ጉባኤ የተዘረጋበት ስፍራ ከሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት በደቡብ በኩል በሚገኘው ቤት በበረንዳ ላይ ነው። የቤቱ አንድ ክፍል የአጼ ምኒልክ ዐፅም በሣጥን ሆኖ የተቀመጠበት ሲሆን ሌላውም ክፍል ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ማረፊያ ሆኖ የተዘጋጀና ጸሎት የሚያደርሱበት፣ ቅዳሴ የሚያስቀድሱበት ስፍራ ነው። ሊቃውንቱ መጻሕፍቱን የሚተረጕሙበት ስፍራ በዚያው አጠገብ ከበረንዳው ስለሆነ ግርማዊት ንግሥት ትርጕሙን ለማዳመጥ በሚፈልጉበት ጊዜ መስኮቱ ይከፈትላቸው ነበር።

ጉባኤው በመደበ የመምህር ደስታ ነበርና ሐዲስና ሊቅ፣[126] መጽሐፈ መነኮሳት ሲተረጕሙበት ይውላሉ። ጧት ቀደም ብለው ገብተው ለደቀ መዛሙርታቸው ለአባ ሰይፉና ለአባ ገብረ መስቀል ሐዲስ ያሄዱላቸዋል። ለሌሎችም ሰዎች ከመጽሐፈ ሊቃውንት እነ ዮሐንስ አፈ ወርቅን ያሄዱላቸዋል። ከዚህ በኋላ እኔ አረጋዊ መንፈሳዊ እያነበብሁ ይተረጕሙልኛል። በዚህ ጊዜ አለቃ ገብረ መድኅን በጉባኤው ላይ ይገኛሉ። የእኔ ጉባኤ ሲያበቃ ትምህርቴን ለመቀጸል እመለሳለሁ። ጌታ አለቃ ገብረ መድኅን ግን በጉባኤው ላይ ይቈዩና ሃይማኖተ አበው[127] ይተረጕማሉ። ደቀ

[124] አባ ወልደ ማርያም የልዑል አልጋ ወራሽ አበ ንስሐ (ንስሐ አባት) ናቸው። (መ.ኅ.ወ.ቂ.)

[125] ጾም ገባ (ግዕዝ)።

[126] በሊቃውንት የተደረሱ ብሉያትንና ሐዲሳትን የሚያብራሩ መጻሕፍት ለምሳሌ፤ ቄርሎስ፣ አፈ ወርቅ፣ ሃይማኖተ አበው።

[127] ከዐረቢኛ የተተረጐመ፣ ከሐዋርያት ጀምሮ በየጊዜው የተነሡት ታላላቅ አበው ያዘጋጇቸውን ትምህርት ጠቀስ ጽሑፎችን የያዘ መጽሐፍ።

መዛሙርታቸው የእንጦጦዎቹ ደብተራ ኃይለ ሚካኤልና ደብተራ ገብረ መድኅን ናቸው።

በጉባኤው ሌሎች ሊቃውንትም ይገኙበት ስለነበረ ስለ ምሥጢር መጻሕፍት[128] በሊቃውንቱ መካከል በሚደረገው የሐሳብ መለዋወጥ ጉባኤው ደምቆ ይውላል። የግርማዊት ንግሥት አበ ንስሐ[129] መልአከ ገነት ተድላና የልዑል አልጋ ወራሽ አበ ንስሐ አባ ወልደ ማርያም አልፎ አልፎ በጉባኤው ላይ ይገኙ ነበር።

ከሌሎች ሊቃውንት መካከል በጉባኤው አዘውትረው የሚገኙት አለቃ ይግዛውና አባ ገብረ መድኅን ምንጊዜም ከትዝታዬ የማይለዩ ናቸው። አለቃ ይግዛው አገራቸው ጎጃም ደብረ ወርቅ ሆኖ የቅኔና የመጻሕፍት ሊቃውንት መምህር ናቸው። ከንግግር ተውህቦ[130] ጋር ትርጓሜ ያጠናቀቁ በምሥጢር የተራቀቁ ስለሆኑ፣ ሁሉም በፍቅርና በአክብሮት ይመለከቷቸዋል።

አባ ገብረ መድኅንም አገራቸው በጌምድር ሆኖ መጽሐፈ መነኰሳትን ጠንቅቀው የተማሩና እጅግ ግብረ ገብ የሆኑ የማኅበረ ሥላሴ መነኩሴ ናቸው። ልብሳቸው ከተሰፋ ጀንዲ[131] የተበጀ አንድ ዳባ[132] ብቻ ነበር እንጂ ከወደ ውስጥ አንዳች ልብስ አልነበራቸውም። ወደ አዲስ አበባ የመጡትም የገዳሙን የውሐ ቢርካ (ኩሬ) እና ቤተ ክርስቲያን ለማሠራት ከመንግሥት እርዳታን ለመጠየቅ ነበረ። መንግሥትም ሥራውን ለግሪኩ ለሙሴ አትናቴዎስ በኮንትራት ሰጥቶ እንዳሠራላቸውና ጥያቄያቸውን ፈጽሞ ደስ እንዳሰኛቸው አስታውሳለሁ። አባ ገብረ መድኅን ለገዳማቸው የቁን ያህል የደከሙ መሆናቸውን ስለማውቅ ትጋታቸውን ሁልጊዜ አደንቅ ነበር።

አስተማሪዬ መምህር ደስታ የአረጋዊ መንፈሳዊን ጉባኤ በቀን ሁለት ጊዜ ስለሚያሄዱልኝ በትጋት አጠና ጀመር። በመጀመሪያው ጉባኤ ያሄድሁትን ብቻዬን ስቀጽል እቈይና ለሁለተኛ ጊዜ ያሄድሁትን ግን አለቃ ገብረ መድኅን ባሉበት ላይ አጠናለሁ። ለቀጸላው ከእሳቸው የማገኘው እርዳታ እጅግ ከፍ ያለ ነው። ትርጓሜውን ስለመጻፍ ሲመክሩኝም መጀመሪያ መጽሐፉን አንድ ጊዜ ተምረህ ዝለቀውና ጽሕፈቱን ኋላ በክሳሽ ላይ አድርገው ስላሉኝ ምክራቸውን ተከተልሁት። ይሁን እንጂ የደቀ መዝሙር ልማድ ነውና ምልክት የሚባለውን ማስታወሻ ባጭር ባጭሩ ከመጻፍ አልተገታሁም ነበር።

---

[128] ቁርሎስ፣ አፈ ወርቅ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ዓሥራ አራቱ ቅዳሴ።


[129] ንስሐ አባት።

[130] ስጦታ።

[131] የተለፋ፣ የለሰለሰ ቆዳ።

[132] ከቆዳ የተሠራ ልብስ።






1 በ1922 ዓ.ም. የታተመው አረጋዊ መንፈሳዊ መጽሐፍ

መጽሐፉን ተምሬ በሐምሌ ወር አንድ ጊዜ ዘለቅሁትና ለክላሽ ተመለስሁበት። ትርጓሜው የሐዲስን ያህል ክብደት ስለሌለው እምብዛም አልተቸገርሁበትም። ሆኖም አርእስተ አእምሮ የሚባለው ድርሳን (በተለይም «ልቡ ለባሕታዊ ገነተ ተድላ ውእቱ») የሚለው ክፍል ጠንካራ ነበረ።

ወደ ሌላው ታሪክ ከማለፌ በፊት ስለ አረጋዊ መንፈሳዊ መጽሐፍና ስለ ደራሲው አንዳንድ መግለጫ ለመስጠት እፈልጋለሁ። ይህ መጽሐፍ በ36 ድርሳናትና በ48 መልእክታት የተከፈለ ነው። ወደ መጨረሻውም «አርእስተ አእምሮ» የተባለ ሦስት ድርሳንና አንድ መልእክተ አረጋዊ አንድ ስእለተ እንሁ ይገኙበታል።

የመጽሐፉ ደራሲ ከሰው ርቆ በበረሃ የሚኖር መነኵሴ ነው። በዚያው ሳለ ከመንፈስ ቅዱስ የተገለጸለትን ምሥጢር እየጻፈ በደብረ ኮኖብዮስ አበ ምኔት[133] ሆኖ ለሚኖር ወንድሙ ለዮሐንስ ይልክለት ነበርና ወንድሙ ሰብስቦ መጽሐፍ አድርጎታል። አረጋዊ ለወንድሙ ሲጽፍ ስለ ትሕትና "ከበረሃ እሪያ[134] የተላከ መልእክት" እያለ ይጽፍለት ነበር። ወንድሙ ግን "የበረሃ እሪያ ሊሉት አይገባም አረጋዊ መንፈሳዊ ነው እንጂ" እያለ መልስ ይሰጠው ነበርና ከዚህ የተነሣ ደራሲውም ድርሰቱም «አረጋዊ መንፈሳዊ» የሚባል ሆኗል።

አረጋዊ በምንኵስና የማዕርግ ተራ ከእንጦንስ[135] ተጀምሮ ሲቈጠር በአራተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። ይኸውም እንደሚከተለው ነው። እንጦንስ ምንኵስናን ለመጀመሪያ ጊዜ መሠረተ። መቃርስ ከእንጦንስ የምንኵስናን ማዕርግ ተቀበለ። ጳኵሚስ ከመቃርስ የምንኵስናን ማዕርግ ተቀበለ። ቴዎድሮስ ሮማዊ ከጳኵሚስ የምንኵስናን ማዕርግ ተቀበለ። አረጋዊ ከቴዎድሮስ ሮማዊ የምንኵስናን ማዕርግ ተቀበለ።

ስለ መጽሐፉ አመጣጥ በትምህርቱ ላይ የተነገረኝን በማስታወስ ጥቂት ቃል እናገራለሁ። ይህ መጽሐፍ ወደ አገራችን መጥቶ ከዐረቢኛ ወደ ግዕዝ የተመለሰው[136] በአጼ ልብነ ድንግል[137] ዘመን ነው። መላሾቹ እጨጌ እንባቆምና ሚካኤል ግብጻዊ ይባላሉ። ንባቡ በእጅ ጽሕፈት እየተባዛ በየስፍራው ስለደረሰ ድምሆይ የተባለ አንድ የምሥሐለ ማርያም ደብተራ አረጋዊ መንፈሳዊ መጽሐፍ ነበረው። በአጼ ገላውዴዎስ ዘመን ጊዮርጊስ ሶርያዊ የተባለ ሊቅ

[133] የገዳም አስተዳዳሪ፣ አለቃ።

[134] ከርከሮ፣ የአሳማ ዓይነት።

[135] እንጦንስ በላዕላይ ግብጽ የነበረ ቅዱስ ነው። የነበረበትም ዘመን በግምት ከ240 እስከ 248 ዓ.ም. እንደሆነ ይነገራል። (መ.ኅ.ወ.ቂ.)

[136] የተተረጐመው።

[137] የአጼ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ከነሐሴ ወር 1500 ዓ.ም. አንሥቶ እስከ መስከረም 5 ቀን 1533 ዓ.ም. ድረስ ነው። (መ.ኅ.ወ.ቂ.)



ሰው ለንግድ ወይም አገር ለማየት ወደ አገራችን መጥቶ ነበርና ድምሆይ ወደ እርሱ ሄዶ ሲጫወት ሳለ የአረጋዊ መንፈሳዊ መጽሐፍ ስላለኝ ትርጓሜውን ታውቅ እንደሆነ እባክህ ተርጕምልኝ ብሎ ለመነው። ጊዮርጊስ ሶርያዊም እሺ ብሎ ባለሐተታ ትርጓሜ አስተምሮት ወዳገሩ ተመልሷል። ድምሆይ መምህሩን እስከ ሐማሴን ድረስ ተከትሎ ትምህርቱን ስላጠናቀቀ የትጋቱ ጽናት ይተረክለታል።

የትርጓሜው ትምህርት ከማን ወደ ማን እንደ ተላለፈና አሁን ከመምህር ደስታ እንዴት እንደ ደረሰ በትምህርቱ ላይ ከአስተማሪዬ የሰማሁትን ለአንባቢ ለመግለጽ ያህል ቀጥሎ ያለውን ቃል እጨምራለሁ።

> ጊዮርጊስ ሶርያዊ ለድምሆይ ዘምሥሐለ ማርያም አስተማረ
> ድምሆይ ዘምሥሐለ ማርያም ለጥበበ ክርስቶስ አስተማረ
> ጥበበ ክርስቶስ ለሐዋርያነ ክርስቶስ አስተማረ
> ሐዋርያነ ክርስቶስ ለሊቀ ካህናት ወልደ ዮና አስተማረ
> ሊቀ ካህናት ወልደ ዮና ለእጨጌ በትረ ጊዮርጊስ አስተማረ
> እጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ለዓቃቤ ሰዓት አብራንዮስ አስተማሩ[138]
> ዓቃቤ ሰዓት አብራንዮስ ለመንፈቆ ወልደ ሃይማኖት አስተማሩ
> መንፈቆ ወልደ ሃይማኖት ለመምህር ሙሴ አስተማሩ
> መምህር ሙሴ ለመምህር ሐሊብ አስተማሩ
> መምህር ሐሊብ ለመምህር ሀብቱ አስተማሩ
> መምህር ሀብቱ ለመምህር አካለ ወልድ አስተማሩ
> መምህር አካለ ወልድ ለመምህር ደስታ አስተማሩ

እስከዚህ ጊዜ ድረስ የትርጓሜው ትምህርት የተላለፈው በቃል በማጥናት ብቻ ነበር። አሁን ግን በልዑል አልጋ ወራሽ ትጋትና ትምህርቱን በጽሑፍ ጭምር ለማስተላለፍ ስለታሰበ የሥራው ዕድል ለአስተማሪዬ ለመምህር ደስታ ደረሳቸውና ይኸው ተጀምሯል። እንግዲህ ፍጻሜውን እግዚአብሔር እንዲያበጀውና ለአስተማሪዬ መታሰቢያ እንዲሆን እመኛለሁ።

## ስለ ልዩ ልዩ ነገር

በዚያ ወራት እኔ ለትምህርትና ለሥራ ከመትጋት በቀር ሌላ ሐሳብ አልነበረኝምና በጌታ በአለቃ ገብረ መድኅን ፊት መወደድንና ሞገስን በቶሎ አገኘሁ። ቀድሞ የተማርሁት የሐዲስ ትምህርቴ እንዳይገድፈኝ ለቅጸላ እንደሚመች አድርጌ ለሰባት ዕለታት ደልድዬው ስለነበረ በመዓልትም ሆነ በሌሊት በቅጸላ እዳስሰው ነበር። ይህንኑ ጌታ ሰምተው ኖሮ አንድ ቀን

[138] የቀድሞዎቹን አንተ የትርቦቹን አንቱ ማለት የተለመደ ነው። ነገሥታትን በተመለከተ ከአጼ ናዖድ በፊት የነበሩት አንተ በኋላ ያሉት አንቱ የማለት ልምድ እንዳለ የዚህ ታሪክ ጸሐፊ የነገሩኝን አስታውሳለሁ።

ጠሩኝና ከማቴዎስ ወንጌል «ወተወሊዶ እግዚእ ኢየሱስ»[139] የሚለውን ጉባኤ በፊታቸው እንዳሂድ አዘውኝ ተረጐምሁት። ከዚያም በኋላ የሐዲስ ደቀ መዛሙርታቸውን ጠርተው "እንግዲህ እኔ በሌለሁ ጊዜ መርስዔ ኀዘን ያስቀጽላችሁ" ብለው አገጣጠሙኝና ከዚያ ቀን ጀምሮ አስቀጽላቸው ጀመር። እነርሱም አባ ዓይኑ ኩሉና የአስበ ተፈሪው መምሬ ማፈኛ፣ አያ ወልደ ኪዳንና የጋስጫ መምህር አባ ወልደ አረጋይ ናቸው። ከዚህም የተነሣ በዚህ ስፍራ ያሉት ሰዎች በአክብሮት ይመለከቱኝ ጀመር።

በዚህ ዓመት ፋሲካ ሚያዝያ 3 ቀን ውሎ ነበር። በዚህ ዕለት ጌታ አለቃ ገብረ መድኅን ከግቢ መብሩቅ እጀ ጠባብና ሱሪ ባለ ጥበብ ኩታ አስመጥተው "ከልዑል የተሰጠህ ነው" ብለው ስለሸለሙኝ ደስ አለኝ።

እንዲሁ ደግሞ በልዑል አልጋ ወራሽ ፊት ዘወትር ማታ ማታ በሚደረገው የማስታኰት[140] ጸሎት ላይ እኔና ቄም ጸሐፊው ተክለ ጊዮርጊስ ናቄ እንድንገኝ ስላስፈቀዱልን በጸሎት ሰዓት ወደ ግቢ እንገባ ጀመር። ማስታኰቻው ስፍራ በእንቍላል ሰገነት አጠገብ በሚገኘው በእልፍኙ ምድር ቤት ውስጥ ነው። በጸሎቱ ላይ ከአለቃ ገብረ መድኅንና ከአባ ወልደ ማርያም ሌላ ደጃዝማች ብሩና ደጃዝማች ኃይሉ ሥላሴ ዓባይነህ አዘውትረው ስለሚገኙ ከልዑልነታቸው ጋር ሰባት ሰዎች ብቻ ሆነን እናስታኩታለን። አንዳንድ ጊዜም ደጃዝማች ጌታቸው በማስታኰቱ ላይ ይገኙ ነበር። እኔ ከመግባቴ በፊት ውዳሴ ማርያም የሚያድሉት ጌታ አለቃ ገብረ መድኅን ነበሩ። አሁን ግን እኔን ከልዑል ጋር በጣም ለማለማመድና ለማቀራረብ ስላሰቡ ውዳሴ ማርያም እያደልሁ የጸሎቱ ተካፋይ እንድሆን አደረጉኝ።

ደግሞ በዚህ በፋሲካው ሰሞን ካሁን በፊት ተሰርቆብኝ የነበረው መጽሐፌ ከእጄ ስለገባ ደስ ብሎኝ ሰነበተ። ይኸውም በተማሪ ቤት ሳለሁ የትርጓሜ ምልክት በእጄ የጻፍሁበት መጽሐፈ ሐዲሳት ነው። ይህን መጽሐፍ ባለፈው በታኅሣሥ ወር ሌባ ከልብሶችና ከሌላም ዕቃ ጋር ሰርቆ ስለወሰደብኝ መቼም አይገኝ ብዬ ተስፋ ቈርጬ ነበር። ነገር ግን ሌባው ልብሶቹን ሸጦ መጽሐፉን ብቻ ከአንድ የመሸታ ቤት አስቀምጦት ኖሮ ስሜን በመጽሐፉ ላይ ያየ ሰው ስለነገረኝ መጽሐፉን በዳኛ አስያዝሁና ከባሻ ወልዴ ችሎት እንዲቀርብ አደረግሁ። ባሻ ወልዴ ምክንያት እየፈጠረ መጽሐፉን የማይሰጠኝ ሲሆን ለአለቃ ገብረ መድኅን ነገርኋቸውና አቤቱታዬን ለልዑል አልጋ ወራሽ አቀረቡልኝ። ልዑልም "በመጽሐፉ ላይ ስሙና የእጅ ጽሕፈቱ ከተገኘ በቶሎ አስረክቡት" ብለው የበላዩን ሹም አዛዥ ወሰኔን ስላዘዙልኝ ወዲያው ዕለቱን

[139] ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶ።

[140] ከቀኑ 11 ሰዓት እስከ ምሽቱ 1 ሰዓት ተከቱል የሚደረስ የሁልቀን ጸሎት።



አስረከበውኝ ተመለስሁ። ይህ መጽሐፍ ዛሬም ከእኔ ጋር ስለሚገኝ የድሮ ድካሜን ያስታውሰኛል።

ስለ አለቃ ገብረ መድኅን እኔ የማውቀውን ከብዙ በጥቂቱ ለመጻፍ እነሆ እጀምራለሁ። አገራቸው ትግሬ ውስጥ ሽሬ ነው። በወጣትነታቸው አድዋ ከአለቃ ተክለ ሃይማኖት ቅኔ ተምረው ከተቀኙ በኋላ በ13 ዓመት ዕድሜያቸው ለዜማና ለመጽሐፍ ትምህርት ወደ በጌምድርና ወደ ጐጃም ሄደው ቈይተዋል። ከዚያም በኋላ ወደ ሸዋ ተላልፈው መጻሕፍትን እየተማሩ ብዙ ጊዜ ኖረዋል። አብዛኛው ትምህርታቸውና እድገታቸው ሸዋ ላይ ስለሆነ የቀድሞዎቹን የሸዋን ሊቃውንት ታሪክ ከአንደበታቸው አይለዩትም። በዜማና በቅኔ፣ በመጻሕፍት ትርጓሜ በጣም የተመሰገኑ ሊቅ ናቸው።

መጻሕፍተ ሐዲሳትን ከአለቃ ወልደ አማኑኤል፣ መጻሕፍተ ሊቃውንትን ከአለቃ ወልደ ሥላሴ ማንመልሶህ ተምረውና ለመምህርነት ተመርጠው ጉባኤ አድርገው ያስተምሩታል። መጻሕፍተ ብሉያትንም ከደብረ ብርሃኑ መምህር ከአለቃ ሥነ ጊዮርጊስ ተምረዋል።

አለቃ ገብረ መድኅን በ1892 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ የተሾሙት ደብረ ብርሃን ሥላሴን ሲሆን ከሦስት ዓመት በኋላ አራዳ ጊዮርጊስንና እንኮበር ሚካኤልን ሦስት፣ ሦስት ዓመት ተሾመውበታል። ከዚያም በኋላ በ1900 ዓ.ም. በነሐሴ ወር ኢየሩሳሌምን ለመሳለም ሄደው ነበርና ከመንፈቅ በኋላ ተመልሰው ሐረር ላይ ሳሉ በ1902 ዓ.ም. ከደጃዝማች ተፈሪ መኰንን ጋር ስለተዋወቁ በከበሬታ ተቀበሏቸውና አዲስ ለተከሉት ለአደሬ ጢቆ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አለቃ አድርገው ሾሟቸው። አለቃ ገብረ መድኅን ይህን ደብር በሚገባ አቋቁመው የሊቃውንት ስፍራ አደረጉት። ከሰገሌ ጦርነት በኋላም ሹመቱን በፈቃዳቸው ትተው ለአለቃ ገብረ ክርስቶስ አስጧቸውና እርሳቸው እነሆ ልዑል አልጋ ወራሽን በምክር እየረዱና እያገለገሉ ተቀምጠዋል። የቤተ መንግሥቱን ሥርዓት የተከታተሉ ሥልጡን ሰው ስለሆኑ በአልጋ ወራሽ ዘንድ ባለሟልነትንና መታመንን አግኝተዋል።

ስለ ጠባያቸውም ጥቂት ቃል እናገራለሁ። አለቃ ገብረ መድኅን አንደበታቸው የተቆጠበ ንግግራቸው የታረመ ነው። ምን ጊዜም ለቁም ነገር ሥራ የታጠቁ ናቸው። ለተዋሕዶ እምነት ተቆርቋሪና ተከራካሪ ናቸው። ትሕርምትን[141] ስለሚወዱ ለሥጋዊ ምቾት አይጨነቁም። ልብሳቸው ሁልጊዜ ንጹሕ ነው። ዝቅዝቅ ጋቢ[142] መልበስን ያዘወትራሉ። አለባበሳቸው መስቀለኛ ሆኖ በማናቸውም ጊዜ አንድ ዓይነት ነው። ማለት በቤት ውስጥ ወይም ከቤት ውጭ ቢሆን፣ ወደ ቤተ መንግሥት ወይም ወደ ቤተ ክርስቲያን ቢገቡ

[141] ጾም።

[142] ጋቢው ጥለቱ ወደ ላይ ሆኖ ሲለበስ። በተለምዶ በኀዘን ጊዜ ነው እንደዚህ የሚለበሰው።

አለባበሳቸው አይለወጥም ማለት ነው። ነጠላ ጫማ ማድረግና በእግር መሄድን ይወዳሉ። ለጸሎት ወይም ለሌላ ምክንያት በቆሙ ጊዜ ቀጥ ብሎ ከመቆም በስተቀር ድጋፍ ወይም ጥጋት አይፈልጉም። ለወደዱት ሰው ሁለመናቸው የተከፈተ ነው። በተቃዋሚነት የሚገጥማቸውንም በዚያው ዓይነት ለመመከትና ለመመለስ ስንፍና የለባቸውም።

ከፍቅረ ንዋይ[143] የራቁ ናቸው። ለምሳሌ የሐረር ንብረታቸውን የሚያስተዳድረውና እንደ ልጅ አድርገው የሚወዱት ደብተራ የማነ ከሐረር ገንዘብ በላከላቸው ጊዜ ወዲያው ለደቀ መዛሙርትና ለችግረኞች በታትነው ያድራሉ እንጂ ነገ የሚል ሐሳብ አልነበራቸውም። ስለ እሳቸው ከዚህም የበለጠ ለመናገር ስችል እዚሁ ላይ አቁሜ ሌላውን ታሪክ እቀጥላለሁ።

በዚህ ዓመት በክረምቱ ውስጥ አስተማሪዬ መምህር ደስታ ፍርኩታ ኪዳነ ምሕረትን ተሾሙ። ይህ ገዳም በመንዝ ውስጥ የሚገኝ ትልቅ ገዳም ከመሆኑም በላይ አጼ ምኒልክ ለመምህር አካለ ወልድ ሰጥተዋቸው ይኖር የነበረ ነው።

በፍልሰታ ሰሞን መምህር ደስታ በጉባኤያቸው ስፍራ ሆነው ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም ለንግሥት ሲያሰሙ አለቃ ገብረ መድኅንም እንዲሁ በቤተ ክርስቲያኑ ቅድስት ውስጥ ለልዑል አልጋ ወራሽ ውዳሴ ማርያም ያሰሙ ነበር። አንባቢውም እኔ ራሴ ነበርሁ።

ሱባዔው ከማለቁ በፊት ጌታ አለቃ ገብረ መድኅን እንደ ጉንፋን አድርጎ ሕመም ጀመራቸው። ሱባዔውን ላለማቋረጥ ቢታገሡትም እየጸናባቸው ስለሄደ በማረፊያ ቤታቸው ተኝተው ታመሙ። ዋና አስታማሚያቸው አባቴ ወልደ ማርያም ሲሆኑ በተጨማሪ እኔና ክንፈ ርግብ ለአስታማሚነት ስለተመረጥን ከአጠገባቸው ሳንለይ አስታመምናቸው። የሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት ቀሳውስት እየተመላለሱ ሥጋ ወደሙ አቀበሏቸው። ልዑል አልጋ ወራሽም ማታ ማታ እየመጡ ይጠይቋቸው ነበር። ወደ ሆስፒታል እንዲሄዱ ቢጠይቋቸው እምቢ ስላሉ የአልጋ ወራሽ ባለሟል ልጅ ደስታ ዳምጠው ሐኪሙን እያመላለሱ ሲያሳክሟቸው ሰነበቱ። 15 ቀን ያህል በጽኑ ከታመሙ በኋላ በጳጉሜ ውስጥ ተሸሏቸው ከሞት ተረፉ።

ስለ ሕመማቸው ደቀ መዛሙርታቸውና ወዳጆቻቸው አዝነው ነበር። ከሐረርም ወዳጆቻቸው ደብተራ የማነና መሪ ጌታ ዘውድነህ፣ አለቃ ገብረ ክርስቶስና አለቃ ለማ፣ ሌሎችም ሰዎች ደንግጠው መጥተው ጠየቋቸው። ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱም መልእክ ገነት ተድላንና ወይዘሮ አጥቁለሽን እየላኩ በየጊዜው አስጠይቀዋቸዋል።

---

[143] የሀብት፣ የገንዘብ ፍቅር።

# ምዕራፍ 20

## 1913 ዓመተ ምሕረት

**የትርጓሜ ረቂቅ በመሥራት ላይ ሳለሁ፣ ስለ ወንጌል ትርጓሜ፣ ስለ የውጭ አገር ትምህርት**

### የትርጓሜ ረቂቅ በመሥራት ላይ ሳለሁ

1913 ዓ.ም. ዘመነ ማቴዎስ ቅዳሜ ባተ። ባለፈው ክረምት ክለሳ የጀመርሁትን የአረጋዊ መጽሐፍ ትምህርቴን እንደቀጠልሁ ነኝ። ትርጓሜውን በእርሳስ እየጻፍሁ ረቂቅ አወጣ ስለነበረ ረቂቁን እየተቀበለ በቀለምና በብራና ላይ የሚጽፍ አንድ ቁም ጸሐፊ ታዘዘና ባለፈው በሐምሌ ወር ሥራውን ጀመረ። እርሱም ቀኝ ጌታ ወልደ ተክሌ የተባለ የአዲስ አበባ ገብርኤል ካህን ነው። ይህ ሰው በቁም ጸሐፊነት የተመሰገነና የትርጓሜ ልምድ ያለው ብልህ ሰው ነው።

የትርጓሜውን ረቂቅ በጻፍሁ ጊዜ የሥራዬ አቅድ እንደሚከተለው ነበር። አንዱን ጉባኤ መጀመሪያ ከአስተማሪዬ ከመምህር ደስታ አስተረጉምና ብቻዬን ከቀጸልሁት በኋላ ወዲያው በእርሳስና በወረቀት የትርጓሜውን ረቂቅ አወጣለሁ። ቀጥሎም ያንኑ ጉባኤ እንደገና አስተርጓሚ ጌታ አለቃ ገብረ መድኅን ባሉበት እቀጽልና በፊት ያረቀቅሁትን እየመረመርሁ አስተካክዬ ንባቡንም በቦታው አስገብቼ የመጨረሻውን ረቂቅ እጽፋለሁ። ከዚህ በኋላ ይህን የጻፍሁትን ለአስተማሪዬ ለመምህር ደስታ አነብላቸውና እሳቸው "መልካም ነው፣ ልክ ነው" ሲሉኝ ለቁም ጸሐፊው እያስተላለፍሁለት ንባቡን በቀይ ትርጉሙን በጥቁር ቀለም እያስማማ ይጽፈዋል። አስተማሪዬ ያረሙት ቃል ሲኖርም አርሜ እሰጠዋለሁ። ይሁን እንጂ የእኔ ረቂቅ በአስተማሪዬ ዘንድ ሁልጊዜ ተቀባይነትን ያገኝ እንደ ነበረ አስታውሳለሁ።

ትርጓሜው በዚህ አኳኋን ተሠርቶና ተገልብጦ በየካቲት ወር 1913 ዓ.ም. ሥራው አለቀና ጌታ አለቃ ገብረ መድኅን ለልዑል አልጋ ወራሽ አቀረቡላቸው። ስለ አረጋዊ ትርጓሜ የምናገረውን እነሆ ከዚህ ላይ አቆማለሁ። ቢሆንም በዚህ ሥራ ምክንያት አማርኛን ለመጠንቀቅ ዕድል አግኝቼ እንደነበረ ለመግለጽ ያህል ጥቂት ቃል እጨምራለሁ።

ጌታ አለቃ ገብረ መድኅን መልክዐ ፊደላትን[144] እና የቃላትን ጸያፎች[145] ጠንቅቆ በማወቅ የተራቀቁ ስለሆኑ እኔ በዘልማድ የጻፍሁትን ቃል ወይም የቃል አገባብ እያረሙ ያስረዱኝ ነበር። ለምሳሌ «ድርሳን ሠለስቱ» የሚለውን እኔ ራሴ በራሴ ልማድ ሰወስተኛው ድርሳን ይህ ነው ብዬ ጽፌው ነበር። እሳቸው ግን ሰወስተኛው በማለት ፈንታ ሦስተኛው ብሎ መጻፍ እንደሚገባ ነገሩኝና አስተካከልሁት። በዚህ ዓይነት ከእሳቸው ያገኘሁት የንግግር ሥርዓትና ጥንቃቄ ሁሉ ከአምስት ዓመት በኋላ የአማርኛ አስተማሪ በሆንሁበት ሰዓት ስለጠቀመኝ ሳመሰግናቸው እኖራለሁ።

## ስለ ወንጌል ትርጓሜ

እላይ በገለጽሁት በትርጉም ሥራ ላይ በነበርሁበት ጊዜ የአርባዕቱ ወንጌላትን ትርጓሜ እንድመረምርና እንዳርም አለቃ ገብረ መድኅን አዘውኝ በተጨማሪ ሠራሁ። ትርጓሜው ከሌላ ስፍራ ተጽፎና ተጠርዞ የመጣ ነው። አሁን የእኔ ሥራ የጎደለውን መሙላትና የተሳሳተውን ማቃናት ብቻ ስለሆነ እዚያው እመጽሐፉ ላይ አርሜ ጨረስሁና አቀረብሁላቸው። እሳቸውም በእርማቱ ስለተስማሙበት ለቁም ጸሐፊው ለተክለ ጊዮርጊስ ናቁ ሰጡትና በቀለምና በብራና አከናውኖ ጻፈው። መቅድመ ወንጌል የሚባለው መጽሐፍ ግን ከዚያ በፊት ትርጓሜውን የጻፈው አልነበረምና እኔ ተርጉሜ የጻፍሁትን ለአለቃ ገብረ መድኅን አቅርቤላቸው ከወንጌሉ ጋር አያያዙት። ይኸውም ከአንድ ዓመት በኋላ በማተሚያ ቤት ታትሞ በወጣው ላይ የሚገኘው ነው።

በሥራ ላይ ከነበሩትም ሰዎች የአንዳንዶቹን ስምና ሥራቸውን በሚከተለው እጠቅሳለሁ። የጐንደሩ የአቋቋም መምህር አለቃ እልፍነህ ለልዑል አልጋ ወራሽ ጸሎት ማድረሻ የሚሆን ወንጌል በጉልህ ፊደል ይጽፉ ነበር። እንዲሁም የሐዲሱ መምህር አለቃ ለማ ከሐረር መጥተው የጳውሎስን ትርጓሜ መጻፍ ጀመሩ። የዋድላው አባ ኪዳነ ማርያምም የሰባቱን ኪዳናት ትርጓሜ አስጽፈዋል። በተጨማሪም ግፅው[146] የተባለ ለቤተ ክርስቲያን የሚያገለግል መጽሐፍ ጽፈው አዘጋጅተው ለአባቴ ወልደ ማርያም አበርክተዋል።

በቁም ጽሕፈት ሥራ ላይ የነበሩት ወልደ ጊዮርጊስ ደለለኝና ደብተራ ስመኝ፣ ደብተራ ተክለ ጊዮርጊስ ናቁ፣ መንግሥቱ፣ ወርቁ፣ ተረፈ ወርቁና መርስዔ ኀዘን ወርቁ የተባሉት ደቀ መዛሙርት ሥራቸውን እንደቀጠሉ ነበር።

[144] የፊደላትን ገጽታና አቀማመጥ።

[145] የሰዋስውን ሕግጋት ያልተከተሉ የአጠቃቀም ግድፈቶች።

[146] በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የየዕለቱን ምንባብ በዝርዝር የያዘ ማውጫ መጽሐፍ።



ስለ አባ ኪዳነ ማርያም ትንሽ መግለጫ መስጠት የተገባ ነው። እኚህ መነኩሴ ቀድሞ ኢየሩሳሌም ነበሩ። በኋላም ወደ አገራቸው ወደ ዋድላ ተመልሰው ጉባኤ ዘርግተው ሐዲስና ፍትሐ ነገሥት መጽሐፈ ቅዳሴ ሲያስተምሩ ቈይተው ነበር። ባለፈው ዓመት ግን ሃይማኖተ አበውን ከአለቃ ገብረ መድኅን ለማድረስ መጥተው ከእኛ ጋር ተቀመጡ። ሰባቱን ኪዳናት አስቀጽለውኝ በጽሑፍ የቀረጽነውና ለአባቴ ወልደ ማርያም የአበረከትናቸው በዚሁ ጊዜ ነበር[147]።

አባ ኪዳነ ማርያም የንግግር ተሰጥዎ ያላቸው ሰባኪ ስለሆኑ በሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት በቅዳሴ ላይ እየሰበኩ ለካህናቱና ለሕዝቡ ልዩ ልዩ ሥርዓትን አስለመዱ። ይኸውም የሚከተለው ነው።

አንደኛ፣ ፍትሐት ዘወልድና በእንተ ቅድሳት፣ ጸሎተ ንስሐም በሚደገምበት ጊዜ ግንባርን ወደ መሬት ደፍቶ መንበርከክ እንደሚገባ በቅዳሴው ላይ ተጽፎ የቈየ ሥርዓት ሲሆን በከተማችን ተዘንግቶ ይኖር ነበር። አባ ኪዳነ ማርያም ግን ይህን ሥርዓት ለማስለመድ እየሰበኩና ምሳሌነታቸውን እያሳዩ ሁሉም እንዲበረከክ አደረጉት።

ሁለተኛ፣ በቅዳሴ ላይ የሚነበበውን ጳውሎስና ሐዋርያ፣ ግብረ ሐዋርያ፣ ወንጌል፣ በግዕዝ ብቻ እንጂ በአማርኛ ማንበብ ገና አልተጀመረም ነበር። እሳቸው ግን ከግዕዝ ቀጥሎ በአማርኛም እንዲነበብ ማድረግን በብዙ ድካም አስለመዱ። በዚህ ጊዜ ከካህናት አንዳንዶቹ በአማርኛ ማንበብ የፕሮቴስታንት ባህል ነው እያሉ መንቀፍ ጀምረው ነበር። ሆኖም ውሎ አድሮ ስለተለመደ በሁሉም ዘንድ የሚደረግ ሆኗል።

ሦስተኛ፣ ዲያቆን የበዓሉን ምስባክ በግዕዝ ከሰበከ በኋላ በአማርኛ እየተረጐመ ለሕዝብ ያሰማ ነበር። ይህን ሥርዓት ብቻ ሌሎች ሳይከተሉላቸው ቀርተዋል።

አራተኛ፣ በቅዳሴ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ከቆሙት ካህናትና መኳንንት አብዛኞቹ በቃልም በመጽሐፍም የግል ጸሎት ሲጸልዩ ይታዩ ነበር፣ አባ ኪዳነ ማርያም ግን ተሰጥዎ ከመቀበል ወይም ቅዳሴውን ከማዳመጥ በስተቀር በቅዳሴ ላይ የግል ጸሎት አይገባም ብለው በስብከታቸው ተከላከሉ።

ያህን በመሰለ ስብከታቸውና በትምህርታቸው ምክንያት አባ ኪዳነ ማርያም በንግሥትም በአልጋ ወራሽም ዘንድ የታወቁና የተከበሩ ሆኑ። ለአለቃ ገብረ መድኅንም ከደቀ መዝሙርነታቸው በላይ የቅርብ ወዳጅ ሆኑ።

[147] መርስዔ ኀዘን ሰባቱ ኪዳናትን ከአባ ኪዳነ ማርያም ተምረውት፣ ትርጓሜውንም አዘጋጅተውት፣ መጽሐፉ በ1917 ዓ.ም. ታትሞ ወጥቷል። በቀድሞው ልማድ መሠረት የማንም ሊቅ ስም በመጽሐፍ ላይ አይጻፍም ነበር፣ ስለዚህም ስማቸው በመጽሐፉ ላይ አልተጠቀሰም።

አባ ኪዳነ ማርያም በአበው መጽሐፍ ከታዘዘው ውጭ በልማድ ገብቶ የቈየውን አሮጌውን የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ለማሻሻልና በመጽሐፍ የታዘዘውን ለመተካት በእውነት ይደክሙ ነበር። ደብተሮች በክብሮ የሚያደምቁትንም ሽብሽባ ከቁም ነገር ስለማይመለከቱት አንዳንድ ሰው የፕሮቴስታንት ባህል ይዘዋል እያለ ያማቸው ነበር። እሳቸው ግን አልነበሩም። አባ ኪዳነ ማርያም በድንገት ፈንጣጣ አሟቸው ሐምሌ 15 ቀን 1913 ዓ.ም. ዐረፉና በደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ተቀበሩ።

## ስለ የውጭ አገር ትምህርት

የፈረንጅ ቋንቋን የተማረ ሰው ለሥራ ሲፈለግና ሲከበር ስለታየ የቋንቋ ትምህርት በዚያ ዘመን ተፈላጊ ሆነ። ልዑል አልጋ ወራሽም ሦስት አሽከሮቻቸውን ለትምህርት ወደ ውጭ አገር ለመላክ ስለፈለጉ ሦስት ሰዎች በጥር 11 ቀን ረቡዕ ከግራዝማች በዳሶ ጋር በባቡር ተሣፍረው ወደ ጅቡቲ ተጓዙና እዚያ ሲደርሱ ጕዞአቸውን በመርከብ ወደ ህንድ ቀጠሉ። እነርሱም በሻህ ውረድ፣ መልአኩ በያን፣ ወርቁ ጉበና[148] የተባሉ ናቸው። እነዚህ ልጆች ቦምቤይ ከተማ ላይ ጥቂት ወራት በትምህርት ከቈዩ በኋላ አገሩ ስላልተስማማቸው ወደ አሜሪካ እንዲዛወሩና እንዲማሩ ተደረገ።

መልአኩ በያን የአልጋ ወራሽ የመኝታ ቤት አሽከር ከመሆኑም በላይ በትርጕም ክፍል ላለነው ሠራተኞችም ለቀለባችንና ለድርጎአችን ባልደረባ ነበረና እስከ ላጋር ወርደን ሸኘነው። እርሱም አደን ከተማ ሲደርስ የሁላችንንም ስም በአንድ ወረቀት ጽፎ ሰላምታ ስለላከልን ስናመሰግነው ሰነበትን።

በዚያው ሰሞን እኔ ወደ አቶ ኀሩይ ወልደ ሥላሴ ሄድሁና እንደነ መልአኩ በያን ለትምህርት እንድሄድ እባክዎ ለአልጋ ወራሽ ይንገሩልኝ ብዬ ለመንኋቸው። ምኞቴም የሕክምና ትምህርት መሆኑን ብገልጥላቸው "ካሁን በፊት እስከ ስንት ክፍል ተምረሃል፣ ዕድሜህስ ምን ያህል ይሆናል" ብለው ጠየቁኝ። እኔም "በፈረንጅ ትምህርት በኩል ከፊደል በቀር ሌላ አልተማርሁም፣ ነገር ግን እስካሁን በግዕዝ ትምህርት ላይ ነኝ፣ ትምህርቴ ዜማና ቅኔ፣ መጻሕፍተ ሐዲሳት ነው፣ ዕድሜዬም 21 ዓመት ያህል ነው" ብላቸው በዚህ ዓይነት ደረጃ እውጭ አገር ስለማይቀበሉህ ልነግርልህ አልችልም አሉኝና

[148] እነዚህ ሦስት ወጣቶች በመጀመሪያ ወደ ህንድ ሄደው ስላልተስማማቸው ወደ አሜሪካ ተዛወሩ። አሜሪካ እንደደረሱም ከአሜሪካው ፕሬዚዳንት ከሃርዲንግ ጋር ለመገናኘት ዕድል አግኝተው ነበር። በሻህ ውረድ ትምህርቱን ጨርሶ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ አገሩን በታላቅ ትንነትና ችሎታ አገልግሏል። በ1929 ዓ.ም. ግራዚያኒን ለመግደል ሙከራ በተደረገ ጊዜ ተይዞ ተገድሏል። መልአኩ በያን በሕክምና ትምህርት ከሃዋርድ ዩኒቨርሲቲ ተመርቆ ኢጣልያ ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ ለኢትዮጵያ እርዳታ ለማሰባሰብ (በተለይ ከጥቁር አሜሪካኖች) በጣም የጣረ ነው። ከነፃነት መመለስ በፊት ሞቷል።



አገሬ እያጉረመረምሁ ተመለስሁ። ለሌላ የተደረገውን ለኔም አድርጉ ማለትን እንደማልችል ገና አላወቅሁም ነበርና ተሞኝቻለሁ።

አርአያ ሥላሴ ወርቃ የተባለ የአባቴ ወዳጅ የሆነ ሰው ከሦስት ዓመት በፊት ለጠበል ወደ ደብረ ሊባኖስ ሄዶ ይኖር ነበር። በዚህ ሰሞን ግን ወደ አዲስ አበባ መመለሱን ስለሰማሁ ከአቶ ኀሩይ ቤት እንደተመለስሁ ወደርሱ ሄጄ ጠየቅሁትና የሆነውን ሁሉ አጫወትሁት። እርሱም "አንተ ከበረታህ እዚህም አገር ተምረህ ወዳሰብከው ስፍራ ትደርሳለህ" ብሎ በምክር ስላበረታታኝ አሳቤ ወደ ቋንቋ ትምህርት አዘነበለ። አቶ አርአያ[149] ከዚያም በኋላ በየጊዜው ለማዋየው ነገር ከልብ ይመክረኝ የነበረውን አልዘነጋውም።

በሚያዝያ ወር ልዑል አልጋ ወራሽ ወደ ደሴ ሲዘምቱ ጌታ አለቃ ገብረ መድኅንና አባቴ ወልደ ማርያም አብረው ሄዱ፣ እኔ ግን እስከ በረህ ድረስ ከሸኘሁ በኋላ የዳዊት ትርጓሜ እንድገለብጥ አዘውኝ ከመንገድ ተመልሼ ነበርና አንድ ቀን ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ሄጄ ለትምህርት ጥያቄ አቀረብሁ። ዲሬክተሩ ሙሴ ሐና ባለ ማኅተም የሆነ የተያዥ ወረቀት ማምጣት አለብህ ስላለኝ የግራዝማች ሥዩምን ባለ ማኅተም ደብዳቤ አቀረብሁለትና በእንግሊዝኛ ክፍል ትምህርት ጀመርሁ። አስተማሪው ሙሴ በዳዊ ይባላል። ተማሪዎቹም ከሐያ የማይበልጡ ናቸው። በአካባቢዬ ከነበሩት ተማሪዎች አበበ በንቲንና ካሣዬ ተጫኔን፣ ኃይለ ጊዮርጊስን፣ ይልማ ዴሬሳን፣ ተምሣሥንና ገብረ መድኅን ዐወቀን አስታውሳለሁ።

ቀን በትምህርት ላይ እየዋልሁ ከትምህርት ምላሽ የትርጓሜ ጽሕፈት ሥራዬን እሠራ ጀመር። ተማሪ ቤቱ በሐምሌ ላይ በተዘጋ ጊዜ ፕራይመርስ የተባሉትን ሦስት ትንንሽ መጻሕፍት ጨርሼ ነበር።

ልዑል አልጋ ወራሽ ከደሴ ተመልሰው ኀሙስ 12 ቀን አዲስ አበባ በገቡ ጊዜ አለቃ ገብረ መድኅንም አብረው ስለመጡ ሥራዬን ብቻ ጠንክሬ እሠራ ጀመር። የቋንቋ ትምህርት መጀመሬንም እንዳይሰሙብኝ ለማድረግ ተጣጣርሁ። ዳሩ ግን ተደብቆ የሚቀር ነገር ስለሌለ ወሬውን ሰምተው

[149] አቶ አርአያ ሥላሴ ወረታ በ1875 ዓ.ም. ሰኔ 15 ቀን ተወለዱ። የዜማ፣ የቅኔና የሐዲስ ሊቅ ነበሩ። በኢጣልያኖች ወረራ ጊዜ ወደ ባሌ የጦር ግንባር ዘምተዋል። ከዚያም ከነደጃች በየነ መርድ ጋር በአርበኝነት ዓሥር ወር ያህል ቈይተዋል። በ1929 ዓ.ም. በየካቲት ወር የእነደጃች በየነ ጦር ድል ሲሆን አቶ አርአያ ተማርከው ደናኔ በተባለ ስፍራ ሁለት ዓመት ታሰሩ። ጠላት ከወጣ በኋላ በ1933 ዓ.ም. በግንቦት ወር በትምህርት ሚኒስቴር የአማርኛ ቅኔ ምክትል ዲሬክተር ተብለው ተሾመው ይሠሩ ጀመር። በ1938 ዓ.ም. መጽሐፍ ቅዱስን የሚመረምርና አማርኛውን የሚያቃና አንድ ኮሚቴ በብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ሰብሳቢነት በቤተ መንግሥቱ ግቢ ውስጥ በንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ በተቋቋመ ጊዜ አቶ አርአያ ለዚህ ሥራ ተመርጠው የኮሚቴው አባል ሆነው ይሠሩ ጀመር። አብዛኛው አገልግሎታቸው በሐዲስ ኪዳን ክፍል ከቄስ ማቴው ጋር ነበር። ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስ በ1954 ዓ.ም. ታትሞ የወጣው ነው። አቶ አርአያ ሥላሴ በ1963 ዓ.ም. ነሐሴ 12 ቀን በ88 ዓመት ከ2 ወር ዕድሜያቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ምንጭ - የብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ያልታተመ ጽሑፍ።


ጠሩኝና እያዘኑ ክፉኛ ገሠጹኝ:: ዳግመኛ ወደዚያ ስፍራ እንዳትመለስ ብለውም አስጠነቀቁኝ:: እንግዲህ የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት እስከ ተከፈተ ድረስ የቋንቋ ትምህርቴን አቋርጬ ተቀመጥሁ:: ጌታ አለቃ ገብረ መድኅን ደህን ማድረጋቸው በእርሳቸው አስተያየት እኔን ለመጥቀም እንጂ ለክፋት እንዳላደረጉት ሕሊናዬ ስላወቀ አላዘንሁባቸውም::

በዚህ ዓመት ውስጥ በቀበና አቦ ቦታዬ ላይ አንድ የግድግዳ ቤት አሠራሁና ዜማ አስተማሪው ደብተራ ወልደየስ ከነተማሪዎቹ እንዲቀመጥበት አደረግሁ:: ይህ ቤት በዓለም ውስጥ የመጀመሪያው ንብረቴ መሆኑ ነው:: መኖሪያዬ እንደቀድሞው በግቢ ውስጥ ከአለቃ ገብረ መድኅን ጋር ስለሆነ የኑሮ ችግር አልገጠመኝም:: አልፎ አልፎ የሚታዘዝልኝ የገንዘብ ዳረጎትም[150] ለፍላጎቴ በቂ ነበር::

በዚህ ወራት ከአለቃ ታዬ ጋር ስለተዋወቅሁና ስለተለማመድሁ የታሪክ ጽሑፍ ለመመልከት ዕድል አገኘሁ:: እኒህ ሰው በጽሕፈት ሚኒስቴር[151] ውስጥ የመንግሥት ሠራተኛ ሆነው ታሪክ የሚጽፉ ናቸው:: ቢሮአቸውና የእኔ መኖሪያ ቤት የተያያዘ ስለሆነ ከሥራ ፋታ ባገኘሁ ቍጥር ወደሳቸው ብቅ ለማለት ይቀናኝ ነበር:: ጠባያቸው ለስላሳና ትሁት ስለሆነ ለታሪክ ጥናት ፍላጎትና ምኞት ያለውን ሰው ሲያናግሩት ቢውሉ ደስ ይላቸው ነበር:: ስለዚህ በአማርኛ የጻፉትን የታሪክ ደብተር እየሰጡኝ እመለከተው ጀመር::

አለቃ ታዬ በግዕዝ ትምህርት የተመሰገኑና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ የነበሩ የበጌምድር ሰው ናቸው:: ከአድዋ ዘመቻ በፊት ወደ ሐማሴን ሄደው ነበርና ምንኩሉ በተባለ ስፍራ ያለው የሚሲዮን ማኅበር የግዕዙን ሰዋስው በ1889 ዓ.ም. አሳተመላቸው:: ከዚያም በኋላ በሚሲዮን አማካይነት በዳግማዊ ምኒልክ ፈቃድ በ1894 ዓ.ም. ወደ አውሮጳ ሄደው ጀርመንኛና ፈረንሳዊኛ ዐውቀው ወደ አገራቸው ተመለሱ:: ይሁን እንጂ በደብረ ታቦር ሳሉ "ጻድቃን አያማልዱም" በሚል ክርክር ከካህናት ጋር ስለተጋጩ ብዙ ጭቅጭቅ አገኛቸው:: በመጨረሻም በዚሁ በክርክሩም ምክንያት ወደ አዲስ አበባ ተላለፉና ከአቡነ ማቴዎስ ፊት ቀርበው ነገሩ ከታየ በኋላ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተለይተው የሚሲዮን ማኅበር ቤተ ሰብ ሆነው ተቀመጡ::

በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያን ታሪክ እንዲጽፉ ስለተጠየቁ በጽሕፈት ሚኒስቴር ውስጥ የመንግሥት ሠራተኛ ሆነው ከዛሬ ዓሥር ዓመት በፊት ጀምሮ በዚህ ሥራ ላይ ናቸው[152]::



26 አለቃ ታዬ

[150] ለተሰጠው አገልግሎት የሚሰጥ አበል::

[151] የጽሕፈት ሚኒስቴር በጸሐፌ ትእዛዝ የሚመራ ነው:: ጸሐፌ ትእዛዝ ማለት ቀጥታ ትርጓሜው "ትእዛዝን የሚጽፍ" ማለት ሲሆን ደንበኛ ሥራው የንጉሡን ማኅተም መያዝና መጠበቅ፣ ማተም፣ ትእዛዙን ማስተላለፍ ነው:: አጼ ምኒልክ በ1900 ዓ.ም. የሚኒስትርነት ሹመት በኢትዮጵያ እንዲቋቋም አደረጉ:: ይህም ሥራ ለኢትዮጵያ የመጀመሪያ ጊዜ ስለነበረ ማቋቋሙ ቀላል ነገር አልነበረም:: በዚህም ጊዜ ለጸሐፌ ትእዛዙ በሚኒስትሮች ሥራ ውስጥ ደንበኛ ስፍራ የማይገኝለት መሆኑን አማካሪዎቻቸው ቢነግሩዋቸው አጼ ምኒልክ ምንም እንኳን በአውሮጳ ለዚህ አኳኋን የሚስማማ ሥርዓት ባይኖር ጸሐፌ ትእዛዙ ሚኒስትር እንዲሆን እፈልጋለሁና ስፍራ ይደረግለት ብለው አዘዙ:: ከዚህም በኋላ በአማርኛ የጽሕፈት ሚኒስትር ተብሎ ተሰየመና ጸሐፌ ትእዛዙ ከሚኒስትሮቹ መካከል አንደኛው ሆኑ:: በፈረንሳዊኛ የተረጐሙ ሰዎችም ለጊዜው እንደመሰላቸው የብርዕ ሚኒስትር ስላሉት በውጭ አገር ሰዎች አነጋገር ያው ቃል ተለምዶ ቀረ:: መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ስለ ጸሐፌ ትእዛዝ ሹመት አመጣጥ ያልታተመ ጽሑፍ::

[152] አለቃ ታዬ በዚህ ዓመት በነሐሴ 17 ቀን በሕመም ምክንያት በ64 ዓመት ዕድሜያቸው አዲስ አበባ ላይ ሞቱ:: የተወለዱት በ1853 ዓ.ም. ኅዳር 21 ቀን መሆኑን ሰምቻለሁ:: እኒህ ሰው ቀድሞ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ የነበሩና እጅግ የተማሩ ናቸው::

ጊዜ ሞታቸው በቀረበ ጊዜ አዲስ አበባ ሥላሴ ቅበሩኝ ብለው ተናገሩ ይባላል:: ምናልባት ያደጉበት የልጅነት ቤተ ክርስቲያናቸው ትዝ ብሏቸው ይሆናል ብዬ አስባለሁ::

ከሞቱ በኋላ ቤተሰቦቻቸውና ወዳጆቻቸው ወደ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ካህናቱን ፍትሐት ፍቱልን ቢሏቸው አንፈታም አሏቸው:: ቀባሪዎችም መቃብር ለመቆፈር ቢጀምሩ ካህናቱ በደወል ተሰበሰቡና ይህ ጸረ ማርያም በቤተ ክርስቲያናችን አይቀበርብንም ሲሉ አምባጓሮ አንሥተው ከለከሉ:: አምባጓሮው ስለ በረታ ነገሩ እስከ ንግሥት ዘውዲቱ ደርሶ ነበርና "እርሱ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መቀበርን ፈቅዶ ከተናዘዘ የቀድሞ ሃይማኖቱን መፈለጉ ነውና ቢቀበር ምን ቸገራችሁ" ብለው የምክር ቃል ላኩባቸው:: ካህናቱ ግን ከቶ አይደረግም ብለው በእምቢታቸው ስለ ጠነከሩ የአለቃ ታዬ ሬሣ ወደ ጉለሌ ተወስዶ በፕሮቴስታንቶች የመቃብር ስፍራ ተቀበረ:: ምንጭ - መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ *የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ* ገጽ 271-272::

# ምዕራፍ 21

## 1914 ዓመተ ምሕረት

**የአባቴን ሞት ስለመስማቴ፣ ለአርባ ተዝካር ወደ ጅሩ ስለመሄዴ፣ ስመንፈቅ ተዝካር ወደ ጅሩ ስለመመለሴ፣ ስለ ልዩ ልዩ ነገር**

### የአባቴን ሞት ስለመስማቴ

1914 ዓ.ም. ዘመነ ማቴዎስ እሑድ ባተ:: ባለፈው ዓመት የጀመርሁትን የዳዊት ትርጓሜ ጽሕፈት በዚህ በመስከረም ወር ስለጨረስሁ የሐዋርያ ትርጓሜ ከአለቃ ዘአማኑኤል ጋር ሆኜ እንዳወጣ ታዘዝሁና ሥራውን ጀመርሁ::

አባቴም "በቶሎ ና" ብለው በዘመዳችን በመምሬ ጸጋዬ በኩል መልእክት ስለላኩብኝ ፈቃድ ተቀበልሁና ወደ ጅሩ ለመሄድ እሰናዳ ጀመር፣ ዳሩ ግን ጥቅምት 10 ቀን 1914 ዓ.ም. ኀሙስ ሞተው ኖሮ መርዶው በዚያው ሰሞን መጥቶ ተነገረኝና በኀዘን ላይ ተቀመጥሁ:: መርዶው የተነገረኝ በቀበና አቦ ቤቴ ላይ ነው:: በእንጦጦ ማርያምና በራጉኤል በሴላም ስፍራ ያሉት ጓደኞቻቸው እየመጡ አላቀሱኝ:: በተለይ የዜና ማርቆሱ መምህር ወልደ ሚካኤል፣ መምህር ደስታ፣ አለቃ ገብረ መድኅን፣ አባ ወልደ ማርያም፣ መልአከ ገነት ተድላ፣ ንቡረ እድ አድማሱ፣ ግራዝማች ሥዩም ወልደ ያሬድ፣ አለቃ ወልደ ትንሣኤ መጥተው ከልቅሶዬ መድረሳቸው ትዝ ይለኛል:: የቤተልሔሙ የዜማ ምስክር ሊቀ ካህናት መርሻም በዚህ ዘመን አዲስ አበባ ላይ ነበሩና ወደ እኔ መጥተው "ጓደኛዬ አብሮ አደጌ" እያሉ እያለቀሱ ኀዘናቸውን ገለጹልኝ::


እኔም የአባቴ መልእክት ደርሶኝ ሳልሄድና ሳላያቸው በመቅረቴ እየተጸጸትሁ ኀዘን በረከተብኝ:: የአባቴ ልጅ እኅቴ ፈትለ ወርቅ ከባልዋ ከመምሬ ንጉሤ ጋር ሐረርጌ ላይ ደሩ በተባለው ስፍራ ነበረችና መርዶው እንዲደርሳት ጌታ አለቃ ገብረ መድኅን የስልክ ቃል አስተላለፉላት:: አባቴ አለቃ ወልደ ቂርቆስ በዚህ በሞቱበት ዘመን የሰድሳ ስድስት ዓመት ዕድሜ ነበሩ::

### ለአርባ ተዝካር ወደ ጅሩ ስለመሄዴ

ከዚህ በኋላ ወደ ጅሩ ለመሄድ ጥቅምት 24 ቀን ከአዲስ አበባ ተነሣሁ:: እኔን ተከትለው የሄዱት የእንጦጦ ማርያም ርእሰ ደብር ራስ ወርቅና የራጉኤል መሪ ጌታ አፈ ወርቅ እንዲሁም ሀብተ ማርያምና ተማሪው ወልደ ማርያም ናቸው:: ጅሩ ደርሼ ከዘመዶቼ ጋር በአባቴ ቤት ተላቀቅስንና መቃብራቸው ወዳለበት ወደ ደብረ ብሥራት ዜና ማርቆስ ሄደን እንደገና አልቅሰን



ተመለስን:: ከዚያም በኋላ ተከታዮቼ ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ እኔ ተዝካር ለማውጣት ጅሩ ላይ ቀረሁ::



የተላከ፡ ከመምሕር፡ ወልደ፡ ሚካኤል፡
ይድረስ፡ ከመጋቢ፡ ይብረሁ፡ ከፍ፡ ወልዱ፡ ዓፄቁ፡
እንደምን፡ ሰነበታችኋል፡ እኔ፡ እግዚአብሔር፡ ይመ
ስገን፡ ደህና፡ ነኝ፡ የመሪጌታ፡ ወልዴ፡ ቂርቆስን፡
ዝምዴና፡ እናንተ፡ ታውቁታላችሁ፡ ይኸውና፡ ልጁ፡
መርሐ፡ ጌዜን፡ መጥቷልና፡ ንገዱን፡ አቁርጋቸ
ሁ፡ ተቀበሉት፡ እኛ፡ የቷያ፡ እንግዳ፡ ቅጥሬው፡ እኛ
ውን፡ ለዜና፡ ማርቆስ፡ ቤተ፡ ለ፡ ይጋዳላችኋልና፡
ጥቅምት፡ ፳፫ ቀን፡ ... ዓመተ፡ ምሕረት፡

2 ከመምህር ወልደ ሚካኤል ለዜና ማርቆስ ካህናት የተላከ መልእክት

የአባቴ ተዝካር ኅዳር 15 ቀን ሰኞ በጾመ ስብከት ውስጥ ስለሆነ የጾም ድግስ ተደገሰና የሦስት መቅደስ ካህናት ወደ ቤት ጠርተን አበላን:: እነርሱም የዲላሞ ጊዮርጊስና የጅሑር መድኃኔ ዓለም፣ የሠርፀ ክርስቶስ ማርያም ካህናት ናቸው::

አክስቴ እመዬት በሰሙ (ስመ ጥምቀቷ ወለተ ጊዮርጊስ) ምንም እንኳ ወደ 80 ዓመት የተቃረበ ዕድሜ ቢኖራት እንደምንም በርትታ በተዝካሩ ላይ ዋለች:: የፈትለ ወርቅ እናት አመለ ወርቅ አባዬና የአምሳለ ወርቅ እናት ደስታ ተካልኝ ለተዝካሩ ድግስ ከፍ ያለ ትጋትና ድካም አደረጉ:: የእናቴ ልጅ እኅቴ መሻገሪያና ባለቤትዋ አቶ ባንትረሴም በብዙ ወገን ረዱኝ:: ከጎረቤቶችም አቶ ሞገድ፣ አቶ ዘረፋ፣ አቶ ጣሴ፣ አቶ መርሻ፣ አቶ ምንዳና ሌሎችም በተዝካሩ ሥራ ያደረጉልኝን እርዳታ በምስጋና አስታውሳለሁ::

በአርባው ተዝካር ማግሥት ቄሱ መምሬ መኩሪያ ኑዛዜያቸውን አቅርበ አፈሰሱ:: የኑዛዜው ቃል መጻሕፍትንና እልቅናን ከቦሎ ዋሻ የደብተርነት መሬት ጋር ለእኔ አድርጎ የቀረውን ሁለት መሬት ለሁለቱ እኅቶቼ ፈትለ ወርቅና አምሳለ ወርቅ እንዲካፈሉ የሚወስን ነው:: አክስቴን እመዬት በስሙንም እኔ እንድጦራትና እንድጠብቃት ብለው ሰጥተውኛል::



መሪጌታ ወልደ ቂርቆስ ሲናዘዙ

የቦሱ ዋሻን ምድር መጻሕፍቶቼን እስከ አትሮንሱ:: አምሳ ብር:: 1 ጻኖ:: በቅሱ እስከ ሥርዓቷ:: ሳም:: ለመርስዔ ኃዘን::

የጉራችን መሬት የነዋሪን መሬት ለፈትለ ወርቅ:: አምሳስ ወርቅን ወንድሞቿ ይዳሯት ይኳሏት:: እድል ፈንታዬን ጽዋ ተርታዬን ያለች እንደሆን በ1 ቁና እህል አግጻለሁ::

ከተዳረች ከተኳለች በኋላ ከፈትለ ወርቅ ጋራ ተካፍለው ይብሉ::

ፈትለ ወርቅ ዘር ብታጣ:: ለመርስዔ ኃዘን ትስጥ:: መርስዔ ኃዘን ዘር ቢያጣ ለፈትለ ወርቅ ይስጥ ከዚህ የወጣ ርጉም ይሁን የይሁዳ በረከት ይድረሰው::

አናዛዡ ቄስ መምሬ መኩሬ

አማኞች:: አቶ ጣሴ አቶ ዘወልዴ አቶ አሰበ አቶ ዳጨ አቶ መርሻ አቶ ወልድዬ

እርጥብ አማኞች አቶ ገብረ መድኅን አቶ ፍቅሬ አቶ ዳጨ አቶ ባንጃው ዳኛው አቶ ምናዩ

3 የአለቃ ወልደ ቂርቆስ ኑዛዜ



እንግዲህ ፍሪዳ[153] ታርዶ የሚደገሰው ትልቁ የተዝካር ድግስ መንፈቃቸው በሚውልበት በፋሲካው ሰሞን እንዲሆን በምክር ተወሰነ:: ከዚህም በኋላ ቤቱን ከነዕቃው ለእኅቴ ለፈትለ ወርቅ እናት ለእመት አመለ ወርቅ ሰጠሁና በታኅሣሥ ወደ አዲስ አበባ ተመልሼ ሥራዬን ቀጠልሁ::

## ለመንፈቅ ተዝካር ወደ ጅሩ ስለመመለሴ

ለተዝካር ማውጫ ልዑል አልጋ ወራሽ እንዲረዱኝ ስለለመንሁ አምሳ ብር ተሰጠኝ:: ደግሞም ላምዋሻ ላይ ካለው የመንግሥት ጕተራ አራት ዳውላ ጌሾና አራት ዳውላ በርበሬ ስለታዘዘልኝ ማዘዣውን ከእርሻ ሚኒስትሩ ከአዛዥ ደገፌ ተቀብዬ በሁዳዴ ውስጥ (በሰሙነ ገብር ኄር) ወደ ጅሩ ወረድሁ:: በዚህም ጊዜ እኅቴ ፈትለ ወርቅ ከባልዋ ከመምሬ ንጉሤ ጋር ከሐረርጌ (ከደኑ) መጥታ አገኘኋት::

ጅሩ ስደርስ ጌሾና በርበሬውን ፍሪዳውንና ሌላውን ዕቃ በማቅረብ ብዙ ድካም ደረሰብኝ:: በዚህ ዘመን ፋሲካ ሚያዝያ 8 ቀን ስለዋለ የአባቴ ተዝካር ሚያዝያ 12 ቀን የአዳም ኀሙስ[154] ዕለት ነበረ:: ድግሱ ተሰናዳና የአባቴን ፍትሐት ሲፈቱ የቈዩትን የሰባት መቅደስ ካህናት ጠርተን አበላን:: መቅደሶቹም ዲላሞ ጊዮርጊስ፣ ጅሑር መድኃኔ ዓለም፣ ሠርፀ ክርስቶስ ማርያም፣ እምቧጮ መኀደላዊት፣ ሽማ ገብርኤል፣ በጣሶ ማርያም፣ ላምዋሻ አቦ የተባሉ ናቸው:: ድግሱ በማግሥቱና በሣልስቱ ቀጥሎ ዋለ:: በማግሥቱ ለካህናት የአጣኝ[155] ሲሆን በሣልስቱ ለአገር ሰዎች ለመሀይምናን[156] ነበር::

ከዚህ በኋላ የእኅቴ ባል መምሬ ንጉሤ እኔን ለመክሰስና በሙግት ለማሰናከል አቅዶ ተነሣና እኅቴን አስጨነቃት:: ሊከሰኝ የፈለገው በቤት ብዙ ገንዘብ ነበረና አላፊ ሆነህ አስረክበኝ በማለትና ኑዛዜውንም በመንቀፍ ጭምር ነበረ:: እኔም ስለ ገንዘብ ነገር ሁሉንም በመዝገብ ጽፌዋለሁና ሒሳቡን ባቀርብለት ፍላጎቱ ሙግት ብቻ ሆነ:: ይህ ሰው በተፈጥሮው ሙግት ፈላጊ ሲሆን ዘመዶቹም በጥብቅና ሥራ የሚኖሩ ነበሩ::

ከዚህ በኋላ እኅቴ ፈትለ ወርቅ "እኔ ወንድሜን አልከስም ኑዛዜውም ትክክል ነው" ብላ በሐሳብ ስለተለየችና እምቢ ስላለችው ተቈጣባትና "ንዝ እመጣለሁ" በሚል ምክንያት በማግሥቱ ወደ ሐረር ተመለሰ:: እኔም ቤቱን ከነዕቃው

[153] የእርድ ከብት፣ ሠንጋ::

[154] ከፋሲካ በኋላ የመጀመሪያው ኀሙስ::

[155] አገልግሎት ሰጭ ካህን::

[156] ካህናት ያልሆኑ::

ለእኅቴ ሰጥቼ ከመሬቴ የማገኘውን ሰብል ለአክስቴ ለእመዬት በሰሙ መጦሪያ እንዲሆን ወስኜ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ እሰናዳ ጀመር።

## ስለ ልዩ ልዩ ነገር

በዚሁ ጊዜ የአባቴ ጓደኛ አቶ ወርቄ ሽብሬ ወደኔ ቀርበው "አባትህ በሕይወቱ ሳለ ለልጁ ለመርስዔ ኀዘን ከጨዋ ቤት ሚስት ፈልግለት ስላለኝ ከትልቅ ሰው ጋር ተነጋግሬአለሁ፣ አባትህም ተስማምቶበት ወገኖቿን እሺ አሰኝቼ ነበር። ልጅቷም የእኅቴ ልጅ ናት። አሁንሳ የአንተ ሐሳብ እንዴት ነው?" ብለው ጠየቁኝ። የልጅቷን ስምና የወላጆችዋንም ስም ዘርዝረው አስረዱኝና የልጅቱ አባት መንዝ የግድም ሰው ሲሆን እናትዋ ግን የጅሩ ተወላጅ ናት አሉኝ። እኔም ነገሩን ካዳመጥሁ በኋላ አንዳች ጥናትና ምርመራ ሳላደርግ "አባቴ የፈቀዱት ነገር ከሆነ እሺ እፈጽማለሁ" አልኋቸው። አቶ ወርቄም "እንግዲያስ አባትዋ አቶ ፈቅይበሉ በሐምሌ ወር አዲስ አበባ ላይ ይገኛልና ቃል ማሰሪያው እዚያው ይደረጋል። የነገር አባትህም እኔ ራሴ ነኝ" ካሉኝ በኋላ ከሐምሌ በፊት አዲስ አበባ ላይ እንደሚገኙ አስታውቀውኝ ተለያየን። እኔም ወደ አዲስ አበባ ተመልሼ ሥራዬን እቀጥል ጀመር።

በዚያ ዘመን ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ በሕግ ለሚያገቡ ሰዎች የልብስ ስጦታ እንደሚያደርጉ ሰምቼ ነበርና እኔም እንደ ሌላው ሁሉ የልመና ወረቀት ጽፌ በመልእክ ገነት ተድላ በኩል ባቀርብ ሙሉ የሙሽራ ልብስ ታዘዘልኝ። ልብሱን ከግምጃ ቤት ተቀበልሁና ሌላውን ነገር ሳሰናዳ ሳለሁ ጓደኛዬ አቶ ዮፍታሔ ንጉሤ ሊጠይቀኝ መጣ። በጨዋታም መካከል የጋብቻውን ነገር አነሣሁና ከባላገር ሚስት ለማግባት ተነጋግሬ ስለመምጣቴ ነገሩን በዝርዝር ብገልጽለት እንዲህ አለኝ። "የባላገር ልጅ ለማግባት ማሰብህ የተሳሳትህ ይመስለኛል፣ አንተ ያደግኸው በከተማ ነው፣ በጠባይ እንዴት ልትግባቡ ነው፣ የባላገሩንስ እንግዳ እንዴት ልትችለው ነው፣ እንደ እኔ ቢሆን ንብረትህን ለማቋቋም ደጋፊ ሊሆንልህ ከሚችል ከከተማ ሰው ጋር መጋባት በተሻለህ ነበር" አለኝ። እኔም ነገሩ ስለገባኝ ሐሳቡን በቶሎ ተቀበልሁና "የነገር አባት ለሚሆነኝ ለአባቴ ወዳጅ እሺ ያልሁትን ቃል እንዴት አድርጌ እለውጠዋለሁ" ብለው "ለዚህ አታስብ እኔ አንድ ፈሊጥ አበጃለሁና ሰውየው ሲመጡ ብቻ አስተዋውቀኝ፣ ፈሊጡንም በፍጻሜው ጊዜ እንጂ አሁን አልነግርህም፣ አሁን ብነግርህ ነገሩ ያስቅሃልና እንዳታበላሸው ስለፈራሁ ነው" አለኝ።

ከዚህ በኋላ በሰኔ ወር አቶ ወርቄ ሽብሬ ስለመጡ ይህንኑ ለዚያው ለጓደኛዬ ነገርሁት፣ እርሱም ፈሊጡን በሆዱ አስቀመጠና ለመስተንግዶ የሚሆን እንጀራና ጠላ አስይዘህ ወደ ሰውየው ዘንድ አብረን እንሂድ አለኝ። እኔም ጠላና እንጀራ አስገዝቼ አሽከሜ አብረን ሄድን። እዚያ ስንደርስ ጓደኛዬ መሆኑን ነግሬ አስተዋወቅሁትና ከእሳቸው ጋር ጨዋታ ጀመረ። ጥቂት እንደ ቈየ "ለእርስዎ ብቻ የማጫውትዎ ጉዳይ ነበረኝ" ቢላቸው ፈቀዱለትና እኔ ከቤት ወጥቼ እደጅ ተቀመጥሁ።



እንግዲህ ጓደኛዬ የነገራቸው ቃል (በኋላ እንደገለጸልኝ) "መርስዔ ኀዘን ጓደኛዬ ነው። እርስዎ የአባቱ ወዳጅ በመሆንዎ ከትልቅ ሰው ቤት ስለገቡለትና ጥሩ ቆንጆ ሚስት ስለአገኙለት ደስ የተሰኘ መሆኑን ነግሮኛል። እኔም ጓደኛው ስለሆንሁና ስለማስብለት ወደ ዐዋቂዎች[157] ቤት ሄጄ ስለ ጋብቻ ጠየቅሁለት። ነገር ግን ያገኘሁት መልስ ደስ አያሰኝም። ነገሩ በእኔና በእርስዎ መካከል ይቅርና የሚያስደነግጥ ነው። ሙሽራይቱ ከጋብቻው በኋላ በአንድ ወር ውስጥ ትሞታለች ብሎ ነግሮኛል። ይህን ነገር ለመርስዔ ኀዘን አልነገርሁትም። ምክንያቱም አሳቡ ተነሣሥቷልና መቼም እሺ አይለኝም በማለት ነው። አሁንም የምነግርዎት ምናልባት እሺ ቢልዎት በርትተው ጋብቻውን እንዲያስቀሩ ነው" የሚል ነው።

አቶ ወርቄ ይህን ሲሰሙ ደነገጡና "ይህማ በጣም የሚያሳስበኝ ነገር ነው። እርሱም ወንድሜ ነው። ልጅቱም እኅቴ ናት። ጆሮዬ እየሰማ መቼ ይደረጋል። ጋብቻው በግድ እንዲቀር አደርጋለሁ" አሉት። እኔም ተጠርቼ ገባሁና "እባክህን ይህ ጋብቻ ይቅርብህ፣ ድሮም የጀመርሁት እኔው ነበርሁ፣ አሁን ግን በሕልሜ የማየው ሁሉ መልካም አይደለምና ይቅርብን፣ ይቅርብን" እያሉ እየተከዙ ይለምኑኝ ጀመር። እኔም "ሕልም ምን ቁም ነገር አለው" እያልሁና እየተግደረደርሁ "አይቀርም" አልኋቸው። እሳቸው ግን ተነሥተው ቆመው "ልጄ ልጄ እባክህን እሺ በለኝ" እያሉ ልመና ስላበዙብኝ "እሺ ይቅር መቼስ ምን አደርጋለሁ ፈቃድዎን መፈጸም ይገባኛል" አልኋቸውና ተሰነባብተን ወጣን። ጓደኛዬም እላይ የተጻፈውን ቃል እየነገረኝና ልባችን በሳቅ እየፈረሰ ወደ ቤታችን ተመለስን።

እንግዲህ የባላገር ጋብቻ ተሠረዘና የከተማ ጋብቻ እየፈለግን ተቀመጥን። ይህንንም ወደፊት ከስፍራው ስንደርስ እተርከዋለሁ።

የትርጕም ሥራ ከያዝሁ እነሆ ሁለት ዓመት አድርጌአለሁ። ነገር ግን በሥራዬ የማገኘው አበል በዳረጎት ዓይነት ስለሆነ ለለቶችና የወር ቀለብ እንዲቈረጥልኝ ለአለቃ ገብረ መድኅን አመልክቼ ሥራዬን ቀጠልሁ። ነገር ግን መልሱን በቶሎ ስላልሰጡኝ ተበሳጨሁና ሌላ ሥራ አጠያይቅ ጀመር። ከጥቂት ቀን በኋላም የእንግሊዝ ቆንስል ሙሴ ዛፊሮ ጸሐፊ ይፈልጋል ማለትን ስለሰማሁ ባለፈው ዓመት የተዋወቅኋቸውና የተለማመድኋቸው አለቃ ታዬ እንዲጠይቁልኝ ለመንኋቸው። እሳቸውም የአደራ ወረቀት ጽፈው ሰጡኝና ወስጄ ብሰጠው ጥቂት ካነጋገረኝ በኋላ "ሥራው በረና ላይ ነው እንጂ እዚህ አይደለም፣ እዚያ መሄድን ትፈቅዳለህ ወይ?" አለኝ። እኔም "እስቲ አስቤ ላስታውቅም" ብዬ ተመለስሁ። የአገሩንም ርቀት ስለጠላሁ ዝም ብዬ ያንኑ ሥራዬን እቀጥል ጀመር።

---

[157] ዐዋቂ ወይም መጽሐፍ ገላጭ የሚባለው ጋብቻ ይሠምር እንደሆን ለማወቅ የሚመለከታቸው መጻሕፍት ሐሳበ ጋብቻና ሐሳበ ኮከብ ይባላሉ።

ስለ ወር ቀለብ ለአለቃ ገብረ መድኅን ያቀረብሁትም ጥያቄ በአጋጣሚ በዚሁ ጊዜ ፍጻሜ አግኝቶ ኖሮ በወር ዓሥር፣ ዓሥር ብር እንድቀበል ታዘዘልኝ። ማዘዣውንም ዋናው የጽሕፈት ሹም ግራዝማች ኃይሌ ወልደ ሩፋኤ በነሐሴ 27 ቀን 1914 ዓ.ም. ጽፈው ለግምጃ ቤቱ ሹም ለአቶ ደስታ (የንዳው) አስተላለፉልኝና ቋሚ የወር ቀለብ እቀበል ጀመር።

# ምዕራፍ 22

## 1915 ዓመተ ምሕረት

በአዲሱ ዓመትና በአቦ በዓል ላይ፣ ወደ ጅሩ ስለመሄዴ፣ በተላላፊ በሽታ ስለመታመሜ፣ ስለ ልዩ ልዩ ነገር፣ ሚስት ስለማግባቴ

### በአዲሱ ዓመትና በአቦ በዓል ላይ

1915 ዓ.ም. ዘመነ ሉቃስ ሰኞ ባተ። ዘመን የተለወጠበትን በዓል በቀበና አቦ ማኅሌት ቆሜ አከበርሁ። በቅዳሴ ጊዜ የደብሩ ሹም አለቃ ኃይለ ሥላሴ የበዓል ቅኔ እንድቀኝ ጋበዙኝና ወዲያው በዘረፋ[158] እጣነ ሞገር ተቀኘሁ። ክብር ይእቲውን[159] ስለማስታውሰው በሚከተለው ጽፌዋለሁ።

ትግበር ምድር ዘትፈቅድ፣[160]
በመጽሐፈ ልባ ተግሣጽ፣
ተውህባ መባሕት እምነ ዘስቀሎ በዕፅ፣
እንዘ ታወጽኦሙ ላዕለ፣
ለዘእግረ መስቀል አብያጽ፣
ለሄሮድያዳ አብአታ አኮኑ፣
በዘአቤሮን እንቀጽ።

የሚል ነው። ቅኔው በዘረፋ የቀረበ በመሆኑ አለቃውና አቶ ዮፍታሔ አድናቆታቸውን ገለጹልኝ።

---

[158] ስለ አንድ ድርጊት ወይም ታሪክ ለብዙ ጊዜ ባለማሰብ ወይም ባለማሰላሰል በፍጥነት የግዕዝ ቅኔ መቀኘት።

[159] ክብር ይእቲ በዕለቱ ቅኔ እንዲሰጥ የተፈቀደለት ሰው ካህናቱ ድርጎት ከመውረዳቸው በፊት ብቻውን እያዜመ የሚያቀርበው የዜማ ክፍል ነው።

[160] ትርጉሙ
ምድር በልቧ መጽሐፍ/ተግሣጽ፣
የምትወድደውን ታደርግ ዘንድ፣
በእንጨት ላይ ከተሰቀለው መብት ተሰጣት፣
ከመስቀል እግር በታች ያሉትን ወንድሞች፣
ወደላይ ስታወጣቸው፣
ሄሮድያዳን በአቤሮን በር አግብታለችና።
ምሥጢሩ
ከበላይ አዛዥ በደብዳቤ ሙሉ ሥልጣን የተሰጠው ሰው የገባውን ለማስወጣት፣ የወጣውንም ለማስገባት ይችል ይሆናል ። እንደዚሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በተሰቀለበት ዕለት መቃብሮች ተከፍተው ብዙዎች ቅዱሳን መነሣታቸው፣ ከዚያም በፊት በብሉይ ኪዳን ዘመን እነ አቤሮንን፣ (ዘኁል. 16፣ 31-32) በሐዲስ ኪዳንም የመጥምቁ ዮሐንስን አንገት ያስቈረጠች ሄሮድያዳ የተባለችውን ሴት ምድር አፍዋን ከፍታ ማስመጥዋ (የማቴዎስ ወንጌል ትርጓሜ 14፣ 1-12) በቅኔው ተመሥጥሯል። ምንጭ - መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ።

ጥቅምት 5 እሑድ የአቦ በዓል ስለሆነ ማኅሌተ ጽጌው ከመቼውም ይልቅ ደምቆ አደረ። ከማታው በ3 ሰዓት ደወል ተደውሎ በየወረቡ እየታወደ በማኅሌቱ አደርንበት። የተክለ ሃይማኖቱ አባ ወልደ ተክሌና የሥዕል ቤቱ ደብተራ ሀብተ ጊዮርጊስ በአቋቋሙና በወረቡ ሲፈራረቁበት አደሩ። በዚያ ሌሊት የነበረው የማኅሌት ጣዕም እጅግ ውብ ነበረ። ከማኅሌተ ጽጌ በኋላ የዕለቱ መዝሙር «ኪነ ጥበቡ መንክር ወዕፁብ . . .» ተመረገደና መመለሻው «ጸገዩ ቀንሞስ ምስለ ናርዶስ» ተወርቦ ቤተ ክርስቲያኑን ስንዞር የነበረው ውብት ትዝ ይለኛል[161]።

የዕለቱ እስመ ለዓለም፤ ናሁ ሠናይ፤ ወናሁ አዳም፤[162] የሚለው አርባዕት በዘይበል ነበርና እሸቴ ክንፌና ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ከእርሱ ላይ በመግሠሥ[163] አዲስ የበዓል ወረብ አዘጋጅተው በጥሩ ዜማ አቀረቡ። ቃሉም ይህ ነው።

«ኪያሁ ፍርህዎ ወሰብሕዎ ወተማኅፀኑ ኀቤሁ ለኃይለ ሥላሴ ወራሴ መንግሥት። ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም በዝመክን ለዘቀደሳ ለአስካለ ማርያም ንግሥት ዓለም»።[164]

---

[161] ትርጉሙ
የእግዚአብሐር የጥበቡ ሥራ ድንቅ ዕፁብ ነው . . .
ቀንሞስና ናርዶስ የተባሉ የሽቱ ተክሎች አበቡ።
ምሥጢሩ
ድርሰቱ የቅዱስ ያሬድ ነው። በጥቅምት ወር ካሉ እሑዶች በአንዱ የቅዱሳን በዓል ሲተባበር ይዘመራል። የመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር የመዝሙሩ መጀመሪያ ሲሆን ሁለተኛው ዐረፍተ ነገር የመዝሙሩ መጨረሻ ነው። ምድርን በአበባ፣ ሰማይን በከዋክብት ያስጌጠ የእግዚአብሔር ጥበብ ዕፁብ ድንቅ መሆኑን፣ ቀንሞስና ናርዶስ የተሰኙት ተክሎች በሚያብቡበት ጊዜ እጅግ ደስ እንደሚያሰኙ ቅዱሳን ከእግዚአብሔር የተቀበሉት ክብር እጅግ ብዙና አስደሳች መሆኑን የሚገልጽ መዝሙር ነው። ምንጭ - መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ።

[162] ድርሰቱ የቅዱስ ያሬድ ሲሆን የቅዱሳን በዓል በጽጌ (አበባ) ወራት ከመስከረም 26 እስከ ኅዳር 5 ቀን ባሉት እሑዶች ሲውል ይዘመራል። የሱፍ አበባና በተክል ቦታ ውስጥ ያለ የሮማን ተክል እጅግ ያማሩና ደስ የሚያሰኙ እንደሆኑ የቅዱሳን ክብራቸው በቤተ ክርስቲያን ያማረና የተወደደ መሆኑን የሚያመለክት ምሳሌያዊ መዝሙር ነው። ምንጭ - መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ።

[163] ግሥ መግሠሥ ማለት ከመደበኛው ዘርዕ በመነሣት ከወቅታዊው ሁኔታ ጋር አስማምቶ መዝሙር መዘመር ወይም ቅኔ መቀኘት ማለት ነው። ይህም ለጊዜው የሚያገለግል እንጂ ሁልጊዜ ሲዘመርና ሲቃኝ የሚኖር አይደለም ። ምንጭ - መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ።

[164] ትርጉሙ
ወራሴ መንግሥት (ልጅ ኢያሱ ወራሽ) ኃይለ ሥላሴን ፍሩት፤ አክብሩት፤ ወደ እርሱም ይግባኝ በሉ፤ እግዚአብሔር የቀደሳትን የዓለም (የኢትዮጵያ) ንግሥት አስካለ ማርያምን ፍሩአት፤ አክብሩአት፤ ወደ እርስዋም ይግባኝ በሉ። ይህም በዚህ ቦታ እነሆ መልካም ነው፤ እነሆም ያማረ ነው ።
ምሥጢሩ
ፍጡራኑን እንደ ፈጣሪ አድርጋችሁ ፍሩ፣ አክብሩ ማለት ሳይሆን በቅዱስ መጽሐፍ «መፈራት ለሚገባው መፈራትን፣ ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ።» (ሮሜ 13፣ 7) በተባለው መሠረት ለባለሥልጣን ተገቢውን ክብር ለመስጠት ነው። የዚህም ተገቢነት

ግርጌ ማስታወሻው በሚቀጥለው ገጽ ይቀጥላል...



ባት ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱና ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ፣ አቡነ ማቴዎስም ወደ ቤተ ክርስቲያኑ መጥተው አስቀደሱ። ከቅዳሴ በኋላ ታቦት ወጥቶ ሲታወድ[165] እላይ የጠቀስሁት ወረብ ተወርቦ ተሸበሸበበትና የበዓሉ ፍጻሜ ሆነ።

በዚህ ቀን የመንግሥት ነጋሪት መቺዎች ነጋሪት ጭነው መጥተው በአቦ ማርገጃ ላይ እየጎሰሙ በዓሉን አደመቁት። የዚህ ዓይነት ሥርዓት ለትልልቅ ደብር ወትሮም የነበረ ነው። ለቀበና አቦ ግን የመጀመሪያ ጊዜው ነበር።

## ወደ ጅሩ ስለመሄዴ

የአባቴን የዓመት ቍርባን ለማስቈረብ ጥቅምት 7 ቀን ወደ ጅሩ ተጓዝሁ። እግር መንገዴንም ልዑል አልጋ ወራሽ ስለ ስእለት ለአቦ ሰጥተውት የነበረውን አንድ ጋሻ መሬት ኘአ ላይ እንድረከብ ማኅበሩና አለቃው ስለለመኑኝ የቤተ ርስቱን ሹም የአቶ ይነሡ ውድነህን ማኅተም ይዤ ሄድሁና ለኘአ ወረዳ ሹም አቀረብሁለት። እርሱም መሬቱን በፈረስ ዞሮ አሳየኝና ተመርቼ ጉዞዬን ወደ ጅሩ ቀጠልሁ።

ጥቅምት 9 ኀሙስ የአባቴን የሙት ዓመት ቍርባን አስቈረብሁ። የእኅቴ ባል መምሬ ንጉሤ ዘሊባኖስ ከሐረር ተመልሶ ስላገኘሁት እንደገና ጭቅጭቅ ይፈጥርብኝ ይሆን ብዬ ሠግቼ ነበር። ነገር ግን ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን ጭቅጭቅ አላነሣብኝም። ከዚህ በኋላ ወደ እምቢሮ ወርጄ አክስቴን እመዬት በሰሙን ጐበኘሁና በጥቅምት መጨረሻ ወደ አዲስ አበባ ተመለስሁ።

በዚህ ጊዜ የእኅቴን የወይዘሮ መሸገሪያን ልጅ እርገጤን አስከትዬ ለትምህርት ወደ አዲስ አበባ አመጣሁት። ከተማሪ ቤት አስገብቼው ሲማር ሳለ ከሁለት ሳምንት በኋላ በተላላፊ በሽታ ስለታመመ እጅግ ተጨነቅሁ። ወዲያው እናቱ ከጅሩ ተጠርታ መጣችና አስታማው ሲድን ወደ ጅሩ ተመለሰ። በትምህርት እንዲጠቀም አስቤለት የነበረውም በዚህ ምክንያት ተደናቅፎ ቀረበት።

## በተላላፊ በሽታ ስለመታመሜ

የእኅቴ ልጅ እርገጤ ታሞ ወዳገሩ ከተመለሰ በኋላ እኔም በታኅሣሥ ወር በዚያው ዓይነት ሕመም ታመምሁ። በትልቁ ግቢ ውስጥ ባለው በመኖሪያ ቤቴ ሦስት ቀን ያህል ከተኛሁ በኋላ ጓደኞቼ እነ ክንፈ ርግብ ወደ ቀበና አቦ ወስደው በቤቴ አስተኙኝ። ምክንያቱም ሠራተኛ ሲታመም በግቢ ውስጥ

---

በሮሜ 13፣ 1-7፤ በ2ጴጥ. 2፣ 13-14 ተጽፎአል። ምንጭ - መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ።

[165] ሲዞር፤ ከግዕዙ ቃል ዖደ (ዞረ)፣ ዑደት (ዙረት)።

እንዲተኛ የማይፈቀድ በመሆኑ ነበር። በቤቴ የተቀመጠው አስተማሪው ደብተራ ወልደየስ ከጓዳ አንዱን ክፍል ለቀቀልኝና ተኝቼ ታመምሁበት። በማስታመምም ደከመልኝ። እንዲሁም ደግሞ የጓደኛዬ የደምሴ ወልደ ገብርኤል እናት እመዬት በለጥሻቸውና ወንድሙ አፈ ወርቅ አዳፍሬ ምግብ እያሰናዱና እያመላለሱ በብዙ ረዱኝ። ጎረቤቶቼ የሆኑት ጓደኞቼ ዘኢየሱስና ዮፍታሔ፣ ገብረ እግዚአብሔር ኤልያስ በችግሩ ሁሉ እንዳልተለዩኝ አስታውሳለሁ።

ስምንት ቀን ከተኛሁ በኋላ በሽታው እየጸና ስለሄደ በታኅሣሥ 28 ቀን ቅዳሜ የአቦ ቀሳውስት ሥጋ ወደሙ አምጥተው አቊርበውኝ ተመለሱ። ከቊርባኑ ከእኩል ሰዓት በኋላ ነስር ነሰረኝና ብዙ ደም ፈሰሰብኝ። ነስሩ ሲጀምረኝ ዐውቅ ነበር። በኋላ ግን አንዳች ነገር እስከ አለማወቅ ደርሼ በጠና ታመምሁ። ሰዎች በኋላ ጊዜ እንደነገሩኝ ነስሩ በርትቶብኝ እንደነበርና ደሙን በትንሽ ቆሬ እየተቀበሉ ሦስት ጊዜ ማፍሰሳቸውን አጫወቱኝ። ሰውነቴም ይንቀጠቀጥ እንደነበረ ነገሩኝ። ስለዚህም ደብተራ ወልደየስ ተስፋ ቈርጦ እስከ መደንገጥ ደረሰ። ዳሩ ግን ይህ ነስር ለኔ የመዳን ምክንያት ሲሆንልኝ ነው። ሲነስረኝ ውሎ ወደ ማታ ዓይኔ ተገለጠና ሰውን ማወቅ ጀመርሁ። ደግሞም ሰውነቴን ሁሉ ቀለለኝና ቁጭ ብዬ እነጋገር ጀመር። ቀጥሎም ከቀን በቀን በሽታው እየተወኝ ሄደና ድኜ በጥር 5 ቀን ቤተ ክርስቲያን ለመሳለም ቻልሁ።

ከዚህ በኋላ የግቢ መኖሪያዬን ትቼ በቀበና አቦ ለመኖር ስለመረጥሁ አንድ ሰቀላ ቤት በግድግዳና በቆርቆሮ ክዳን አሠራሁና መኖሪያዬን ከዚያ አደረግሁ። ጓደኞቼ ዘኢየሱስና ዮፍታሔ፣ ገብረ እግዚአብሔር ኤልያስ ቀደም ብለው ቤት ሠርተው ነበርና ጉርብትናቸው እጅግ ጠቀመኝ። እናቴ ወይዘሮ የሸዋ ወርቅም መታመሜን ሰምታ ኖሮ ከጅሩ መጥታ አዲሱን ቤት በማሟሟቅ እየረዳችኝ ሦስት ወር ተቀምጣ ተመለሰች። እኔም ገረድ ቀጥሬ ተቀመጥሁ።

## ስለ መጽሐፈ ሲራክ ትርጓሜ

ብሉይ የሚያስተምሩት የቀበና አቦ ሹም አለቃ ኃይለ ሥላሴ የመጽሐፈ ሲራክ ትርጓሜ እንዲያወጡ ስለታዘዙ እኔም ለሥራው ታዝዤሁና አብረን እንሠራ ጀመር። ንባቡንና ትርጓሜውን ለማዘጋጀትና ለመጻፍ የወሰደብን ጊዜ ከአንድ ዓመት ያልበለጠ መሆኑን አስታውሳለሁ። መጽሐፉን ባስረከብን ጊዜም ከልዑል አልጋ ወራሽ የተደረገልንን ሽልማት ወደፊት እጽፋለሁ።

## ስለ ልዩ ልዩ ነገር

በዚህ ዓመት ሚስት ለማግባትና ንብረት ለመያዝ ስላስፈለገኝ የቅርብ ወዳጆቼንና ዘመዶቼን ሚስት ፈልጉልኝ እያልሁ አሳሰብኳቸው። እነርሱም በየበኩላቸው ባቀረቡልኝ ዝርዝር ውስጥ የሰንበቴ ማኅበር ማኅበርተኛዬን ስም ተጠቅሶ ስላገኘሁት ምርጫዬ የእርሳቸውን ልጅ ለማግባት ሆነና፣ የልጅቷን



ዕድሜ ሳላውቅ ወይም ሳልጠይቅ በትልቅ ሰው በኩል የጋብቻ ጥያቄ አቀረብሁላቸው። ሰውየውና እኔ ጥንቱንም እንተዋወቃለንና የተገኘው መልስ "ጋብቻውን ለመቀበል ፈቃዴ ነው፣ ነገር ግን ልጅቱ ገና የስባት ዓመት ዕድሜ ናትና ለጋብቻ ስላልደረሰች ወደፊት እስከ ስንት ዓመት ሊጠብቅ ይችላል" የሚል ነበር። እኔም ይህን በሰማሁ ጊዜ ሕፃንነቷን ያላወቅሁ መሆኔን አስረድቼ በወዳጅነት መንፈስ ጥያቄውን ሠረዝሁና ሌላ እፈልግ ጀመር። ከሰውዬው ጋር የነበረኝም ፍቅር ምንም ሳይቀንስ ጸንቶ የሚኖር ሆኗል።

በዚህ ዓመት ፋሲካ በመጋቢት 30 ቀን ውሎ ነበር። ከዚያም በኋላ በሚያዝያ ወር አንድ የቀበና አቦ ዲያቆን ራሱን በዛፍ ላይ ሰቅሎ ስለሞተ የመንደሩ ወሬ ሆኖ ሰነበተ። በዚሁ ጊዜ የሰማሁትንም አስደናቂ ነገር ሳልገልጸው አላልፍም።

ይህ ልጅ በሊቀ ድቁና የሚያገለግል የይፋት ሰው ነው። ስሙም ኪዳነ ማርያም ይባላል። ትሁትና ሰው አክባሪ ስለሆነ በጠባዩ መንፈሳዊ ነው። በዚያም ዘመን ሚስት አጭቶ ነበርና ሚያዝያ 28 ቀን በሠርግ ለማግባት ይሰናዳ ጀመር። ለሠርጉ አንድ ሳምንት ሲቀረው ጋብቻው የሚሠምር መሆን አለመሆኑን ለማስጠየቅ ወዳጆቹን ወደ ዐዋቂ ስለላካቸው ከአለቃ ኤልያስ ዘንድ ሄደው ጠየቁለት። አለቃ ኤልያስ ሥራቸው ሰዓሊነት ሆኖ ሳለ ጋብቻም ያውቃሉ የሚባሉ የጉጃም ሊቅ ናቸው።

አለቃ ኤልያስ የጋብቻውን ቀን ቀጠሮ በመጽሐፋቸው መረመሩና የወጣው አንቀጽ «መርዓዊሃ ይሰቀል» (ሙሽራው ይሰቀላል) የሚል መሆኑን ነገሯቸው። መልእክተኞቹም ደነገጡና "እንዲህ ከሆነ ጋብቻው ይቅርብህ ብለን ገልጠን እንንገረው፣ ሠርጉም በሚመጣው እሑድ ነው" ቢሏቸው ቀጥሎ ያለውን ምክር ሰጧቸው። "ሠርጉ ተደግሶ ያለቀ ነገር ከሆነ ይህን ወሬ ነግራችሁ አታስደንግጡት፣ ይህ አንቀጽ ለሌሎችም እየወጣ በትንንሽ ምክንያት ሲተላለፍላቸው አይቻለሁ፣ ለምሳሌ ካሁን በፊት እኔ ራሴ ሚስት ለማግባት ፈልጌ መጽሐፉን ስመለከት ይኸው አንቀጽ ቢወጣልኝ ሴቲቱን ስለወደድሁ ዝም ብዬ አገባኋት፣ ከዚያም በኋላ የቀድሞ ባልዋ ከሰሰኝና በሰንሰለት ተቆራኝቶኝ[166] በአፈ ንጉሥ ነሲቡ ችሎት ላይ እጄን ሲያንጠለጥለው ስለሰነበተ በዚህ ተላልፎልኛል፣ አሁንም በአንድ ትንሽ ምክንያት ይተላለፍለት ይሆናልና አታስደንግጡት፣ ሆኖም በጸሎትና በምጽዋት የጎዘን ነገር ይጨምርበት" ብለው መክረው መለሷቸው።

መልእክተኞቹም ተመለሱና ሌላውን አስቀርተው ስለ ጸሎትና ስለ ምጽዋት የተነገረውን ምክር ብቻ ለኪዳነ ማርያም አስረዱት። እርሱም ለቤተ

[166] ከዳኛ ዘንድ እስኪደርስ ወይም እስኪፈረድ ድረስ ተከሳሹ ከከሳሹ ጋር እግሩ ወይም እጁ እንዲጣመር ተደርጎ ሲታሰር።

እግዚአብሔር ገንዘብ ሰጠና ጸሎተ እጣን[167] እየተደገመ እንዲታጠንለት አድርጎ በጸሎት ሰነበተ።

ከዚህ በኋላ ሚያዚያ 28 ቀን እሑድ ማታ ኪዳነ ማርያም ጓደኞቹን አስከትሎ ወደ ሴቲቱ ቤት ሄዶ እንደ አገር ልማድ ተሠርጎ አደረ። በማግሥቱ ሰኞ ሚስቱን ተቀብሎ በሠራተኞች ታጅቦ ወደ ቀበና አቦ መጣና በራሱ ቤት የሠርጉን በዓል አክብሮ ዋለ። ማታ በጨለማ ከሚዜዎቹ ጋር ከቤት ወጣና በስተጓሮ ከአጥር ውጭ ባለው ስፍራ ቊጥቋጦ ከለላ አድርጎ ዓይነ ምድር ተቀመጠ። ሙዜዎቹም እንደርሱ ወገባቸውን ለመሞከር[168] ፈንጠር እያሉ ተቀመጡ። ስፍራው የአጋም ቊጥቋጦና የወይራ ዛፍ የሞላበት ጫካ ቢጤ ነው።

ኪዳነ ማርያም በዚህ ጊዜ ከተቀመጠበት ተነሥቶ ወደ ጫካው ገባና ከወይራ ዛፍ ላይ ወጥቶ እንደ ባላ በሆነ በዛፉ ቅርንጫፍ ላይ አንገቱን ቀርቅሮ ተሰቀለ። ሙዜዎቹ ሥራቸውን ጨርሰው ይጠብቁት ነበርና ስለዘገየባቸው "ምነው ቀረህ" ብለው ድምፅ ቢያሰሙት የማይመልስላቸው ሆነ። ወደ ስፍራውም ሄደው ቢያዩ ስለጠፋባቸው ስሙን እየጠሩ በየጫካው ይፈልጉት ጀመር። ሊያገኙት አለመቻላቸውን ከተረዱ በኋላ የሙሽራውን መጥፋት ለቤተሰብና ለጎረቤት ተናገሩና ሁሉም በመብራት በየጫካው ይፈልጉ ጀመር። ነገር ግን አልተገኘም። በዚህ ጊዜ የነበረውም ወሬ የመንፈሳዊነት ባሕርይ ስላለው ምናልባት መንኖ ይሆናል የሚል ነበር።

ሌሊቱ በዚህ አኳኋን አልፎ ከነጋ በኋላ በጫካው ውስጥ በአንድ ዛፍ ላይ ነጭ ልብስ ተንጠልጥሎ ስለታየ ወደዚያ ቀርበው ቢያዩት ኪዳነ ማርያም መሆኑ ታወቀ። ከዚያ በኋላ ሬሣውን ከዛፉ አውርደው ወደ ቤት አስገቡትና ልቅሶ ሆነ። ቀጥሎም ቀሳውስት ተጠርተው ፍትሐት ሲፈቱ ዋሉና ዕለቱን ተቀበረ።

እዚህ ላይ አስደናቂ ነገር አድርጌ በትዝታዬ ያቄየሁትና ለአንባቢ ልገልጸው የፈለግሁት ከአለቃ ኤልያስ የተነገረውን ቃል ነው። ሙሽራው ይሰቀላል ያለው የአንቀጹ ቃል በቀጥታ በመፈጸሙ ሁላችንንም ሲያስደንቀን ሰንብቶ ነበር።

## ሚስት ስለማግባቴ

ሚስት ፈልጉልኝ እያልሁ ከነገርኋቸው ዘመዶቼ ውስጥ መምሬ ራስ ወርቅ ወልደ መስቀል የተባሉት የቅርብ ዘመዴ አንድ ቀን መጡና ለትዳር ተስማሚ የምትሆን ሚስት አድአ ላይ አገኘሁልህ ካሉኝ በኋላ ስለ ቤተሰቦቿና ስለ

[167] ቁስ ዕጣን ሲያጥን የሚጸልየው ጸሎት።

[168] ዓይነ ምድር መቀመጥ፣ መጸዳዳት።



ሁናቴዋ በዝርዝር ያስረዱኝ ጀመር። የልጅቷ አያት ደብተራ ወልደየስና አጎትዋ ቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ አቢብ የራጉኤል ተክለኞች መሆናቸውን ነገሩኝ። እንዲሁም አባትዋ የመራቤቴ፣ እናትዋ የመንዝ ተወላጆች መሆናቸውንና ስምዋ እታገኘሁ ባዩ መሆኑን ገለጹልኝ። እኔም ነገሩን መርምሬ ከተረዳሁ በኋላ ስለተስማማሁበት ሽማግሌዎች ልኬ የጋብቻውን ጥያቄ ለወላጆችዋ እንዲያቀርቡ አደረግሁ። በተለይም አለቃ ዳኜ በዚህ ጉዳይ ተግተው እንደሠሩልኝ አስታውሳለሁ።

ወላጆችዋም አባቴን ያውቃሉና ጥያቄውን በደስታ ስለተቀበሉት ሠርጉ አዲስ አበባ ላይ በአጎትዋ በቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስ ቤት ሆኖ በእግዚአብሔር ፈቃድ ነሐሴ 27 ቀን 1915 ዓ.ም. እሑድ የጋብቻችን ሥርዓት ተፈጸመ። በዚህ ጊዜ የእኔ ዕድሜ 24 ዓመት ከ5 ወር ሲሆን የሚስቴም ዕድሜ 16 ዓመት ከ4 ወር ነበረ።

# ምዕራፍ 23

## 1916 ዓመተ ምሕረት

**ስለ መጽሐፈ ሲራክ ትርጓሜ፣ ስለ አሰቦት ገዳም፣ ወደ ጅሩ ስለመሄዴ**

### ስለ መጽሐፈ ሲራክ ትርጓሜ

*1916 ዓ.ም. ዘመነ ዮሐንስ ረቡዕ ባተ። ባለፈው ዓመት ተጀምሮ የነበረው መጽሐፈ ሲራክ (ገጽ 158) ንባቡና ትርጓሜው ተጽፎ ስለተፈጸመ፣ አለቃ ኃይለ ሥላሴና እኔ ጥቅምት 5 ቀን መጽሐፉን ለልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ አስረከብን። እሳቸውም በሥራው ስለተደሰቱ ከግምጃ ቤታቸው ሽልማት አዘውልን ሁለታችንም ተሸለምን። ለአለቃ ኃይለ ሥላሴ የተሰጣቸው ሽልማት ካባና ድርብ አብደላከኒ ቀሚስ ሲሆን ለእኔ የተሰጠኝ ግን ካባና ጃኖ አብደላከኒ ቀሚስ ነበር።*

*ሽልማቱን ለበስንና እንደጊዜው ልማድ በዘመዶቻችንና በወዳጆቻችን ታጅበን፣ እምቢልተኞችና ጥሩምባ ነጋሪዎች በፊት በፊታችን እየነፉልን ወደ ቀበና ቤታችን ተጓዝን።*


*የመጽሐፈ ሲራክ ንባብና ትርጓሜ በ1917 ዓ.ም. በልዑል አልጋ ወራሽ ማተሚያ ቤት ታትሞ ወጣ። ይሁን እንጂ የኛ የአዘጋጅዎቹ ስም በመጽሐፉ ላይ አልተገለጸም። ምክንያቱም አሠሪውና አሳታሚው መንግሥት በሆነበት መጽሐፍ ላይ የአዘጋጅዎችን ስም አለማሳወቅ የዘመኑ ፈሊጥ ስለነበረ ነው። ስለዚህም በዚያ ዘመን የተጻፉትና የታተሙት ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በማን እንደተዘጋጁ መግለጫ የላቸውምና የሥራው አላፊነት ለአሳታሚው ብቻ ሆኖ ይገኛል።*

### ስለ አሰቦት ገዳም

*የሥራ አለቃዬ ጌታ አለቃ ገብረ መድኅን ካለፈው ዓመት ጀምሮ የአሰቦትን ገዳም ለማቅናት መመላለስ ስለጀመሩ ሥራዬን የምሠራው በቤቴ ነበር። አሰቦት ከግራኝ ወረራ በፊት ደብረ ወገግ የተባለ የአባ ሳሙኤል ገዳም የነበረበት ስፍራ ነው። ከገዳሙ ስም የተነሣ ሳሙኤል ዘወገግ ተብለው ተጠርተውበታል። ገዳሙ በግራኝ ወረራ ጠፍቶ ሲኖር አሁን በአለቃ ገብረ መድኅን አሳሳቢነት ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኩንን እንደገና አቋቋሙትና በ1911 ዓ.ም. የሥላሴን ታቦት ተከሉበት። ጌታ አለቃ ገብረ መድኅንም የገዳሙ ጠባቂ ሆነው ወደዚያው መመላለስ ሲጀምሩ እኔ ከአባ ወልደ ማርያም ጋር ሆኜ የትርጓሜ ጽሕፈት ሥራዬን እንድቀጥል ስላዘዙኝ*



*በአዲስ አበባ ቀረሁ። ሆኖም አልፎ አልፎ እየመጡ ሥራዬን ይመለከቱት ነበር። በዚህ ዓመት የጀመርሁትም ሥራ ከአለቃ ኃይለ ሥላሴ ጋራ የደቂቀ ነቢያትን ትርጓሜ ከነንባቡ ማዘጋጀት ነበር።*



27 የአሰቦት ደብረ ወገግ ገዳም

### ወደ ጅሩ ስለመሄዴ

*በዚህ ዓመት በየካቲት ወር ከዓቢይ ጾም በፊት ወደ ጅሩ ወረድሁና ዘመዶቼንና ንብረቴን ጐበኘሁ። አክስቴ እመዬት በሰሙና ባለቤቷ መምሬ ወሰን መሪ ሁለቱም እርጅና ተጭኗቸውና ተዳክመው አገኘኋቸውና አዘንሁ። እርስዋ በዕድሜ ከ81 ዓመት በላይ ስትሆን መምሬ ወሰን መሪም 97 ዓመት ያደረጉ ናቸው። ወዲያው እንደ ደረስሁ ከአዲስ አበባ ያመጣሁላቸውን ልብስ አለበስኋቸው። ቀጥሎም የፍየል ሙክት ገዝቼ አቀረብሁና ሥጋ በልተው ደስ እንዲላቸው ስለአደረግሁ በተደረገው ሁሉ እያመሰገኑ መረቁኝ። በመጨረሻም ለኑሮአቸውና ለምግባቸው የሚያስፈልጋቸውን አደራጀሁና በእነርሱ ዘንድ ተቀምጣ ለምትጦራቸው ዘመዳችን ለእሸቴ አደራ ብዬ ሰጥቼ ተሰናበትኋቸውና ወደ አዲስ አበባ ተመለስሁ።*

# ምዕራፍ 24

1917 ዓመተ ምሕረት

ከሥራ ወደ ሥራ ስለመዛወሬ፣ ስለ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ፣ ስለ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት መከፈት፣ ስለ ልዩ ልዩ ነገር

## ከሥራ ወደ ሥራ ስለመዛወሬ

1917 ዓ.ም. ዘመነ ማቴዎስ ኀሙስ ባተ። ባለፈው ዓመት ከአለቃ ኃይለ ሥላሴ ጋር የጀመርነውን የደቂቀ ነቢያት ትርጓሜ ከነንባቡ በዚህ ዓመት መጀመሪያ ላይ ጨረስንና ለልዑል አልጋ ወራሽ አስረከብነ። ከዚህም በኋላ በጥቅምት ወር ባለቤቴ ወይዘሮ እታገኘሁ ባዬ በደኅና ተገላግላ ወንድ ልጅ አገኘን። ሆኖም ከሦስት ሳምንቶች በኋላ ሕፃኑ ትክትክ[169] በሚባል በሽታ ስለታመመ ሥጋትና ኀዘን ደረሰብን። በሽታውም ስለጠነከረበት ሳይጠመቅ እንዳይሞት ተባለና ከክርስትናው ቀን በፊት አስጠምቀነው ገብረ መድኅን የሚል ስመ ጥምቀት ተሰጠው። ጥቂት ቀን ቈይቶም ሞተና በቀበና አቦ ተቀበረ።

በኅዳር መጨረሻ ወደ ጅሩ ሄጄ ዘመዶቼን ጐብኝቼ ተመለስሁ። ከዚያም እንደመጣሁ በታኅሣሥ ወር የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ዋና ጸሐፊ ሆኜ ወደ ማተሚያ ቤት ተዛወርሁ። እንዲሁ ደግሞ ከአራት ወር በኋላ የግዕዝና የአማርኛ አስተማሪ ሆኜ በሚያዝያ ወር ወደ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተዛወርሁ።

## ስለ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ

ልዑል አልጋ ወራሽ በግቢያቸው ውስጥ ላቆሙት የመጻሕፍት ማተሚያ ቤት ዲሬክተር ያደረጉት አቶ ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ሥራውን ለማስፋፋት እጅግ ይተጋ ነበር። በዚህም ዘመን ማተሚያ ቤቱ አንድ የሳምንት ጋዜጣ እያተመ ቢያወጣ ለኢትዮጵያ ጠቃሚ መሆኑን በመግለጽ ለልዑል አልጋ ወራሽ ሐሳብ አቅርቦ እያስታወሰ ቈይቶ ነበርና ስለ ፈቀዱለት ሥራውን ለመጀመር ይሰናዳ ጀመር። በዚሁም ጊዜ ለጋዜጣው ጽሕፈት የአማርኛ ችሎታ ያለው አንድ ሰው ይታዘዝልኝ ብሎ ልዑል አልጋ ወራሽን ስለ ለመነ እኔን የእልፍኝ አሽከሩ ልጅ በልሁ ደገፋ ፈልጎ አስጠርቶ የጋዜጣ ሥራ ጸሐፊ እንድትሆን ከልዑልነታቸው ታዘሃል ብሎ አስታወቀኝ። ቀጥሎም ወደ አቶ ገብረ ክርስቶስ ወስዶ አገጣጠመኝና ሥራውን ተረክቤ እሠራ

169 የሕፃን ጉንፋን፣ ሳል።



ጀመር። የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ በዓመት አምስት ብር ሲሆን፤ ለውጭ አገር ግን በዓመት ሰባት ብር ሆኖ ተወሰነ።




4 የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ የመጀመሪያው እትም

ከዚህ በኋላ የጋዜጣው ስም ምን ተብሎ እንደሚሰየምና በምን ቀን መውጣት እንደሚገባው የሥራውንም አጀማመር በማጥናትና ሐሳብ በማቅረብ ሦስት ሳምንት ያህል አለፈ። በመጨረሻም ልዑል አልጋ ወራሽ ጋዜጣውን «ብርሃንና

ሰላም» ብለው ሰየሙትና የመጀመሪያው ጋዜጣ ታኅሣሥ 23 ቀን 1917 ዓ.ም. ኀሙስ በ4 ገጾች ታትሞ ወጣ:: ከዚያም ቀጥሎ በየሳምንቱ ኀሙስ፣ ኀሙስ የሚታተም ሆነ::

በመጀመሪያው ቊጥር ጋዜጣ ዲሬክተሩ አቶ ገብረ ክርስቶስ ስለ ብርሃንና ስለ ሰላም ሐተታ በመስጠት የጻፈ ሲሆን እኔም ዋና ጸሐፊውም በበኩሌ ወደ ጅሩ ሄጄ ሳለ ስለአየሁት አዝመራ ሐተታ በመስጠት ጽፌ አቀረብሁ:: እርእስቱ «ስለ ዘንድሮ አዝመራ ከሀገር ውስጥ የመጣልን ወሬ» የሚል ሆኖ ጅሩ የሚባለው «አገር ነጭ ስንዴና ጥቁር ስንዴ፣ ባቄላና ተልባ፣ ሽንብራና ጓያ ይበቅልበታል» እያለ የሚቀጥል ነበር::

ስለ ዘንድሮ አዝመራ ከሀገር ውስጥ የመጣልን ወሬ ።

ጅሩ በሚባል አገር ነጭ ስንዴና ጥቁር ስንዴ ባቄላና ተልባ አተርና ሽንብራ ጓያ ይበቅልበታል ጥቁር ጤፍም አልፎ አልፎ ጥቂት ጥቂት ይገኛል ። ነገር ግን የጅሩ ዋና አዝመራው ስንዴ ነው ። በሁሉም ዘመን እጅግ አድርጎ አምሮበታል ያበቃቀሉንም ነገር ሲያዩት ያስገርማል ፤ ያገሩ መሬት መረሬ ስለሆነ ስንዴው በነሐሴ ይዘራል ። በኅዳርና በታሕሣሥ ዝርዝር ይሆናል ፤ በዚህም ጊዜ ከከፍተኛ ቦታ ላይ ሆኖ የጅሩን ሜዳ ሳያት ሰው ከልምላሜዋ ማማር የተነሣ ልክ በባሕር መሃከል ያለ ይመስለዋል ። ነገር ግን ወደ እርሻው ውስጥ ገብቶ ያዩት እንደሆነ መረሬው አፉን ለቆ ክንድ ክንድ ያህል ተሰ-ንጥቆ ይገኛል ። ወይ ግሩም ከእንደዚህ ያለ ንቃቃት መሬት ላይ ያንን ያህል ልምላሜ መገኘቱ እግዚአብሔርን ያስመሰግናል ያገሩም መሬት ውድ ስለ ሆነ በመላው ጅሩ ከእርሻ በቀር አጻሬ መሬት በብዙ አይገኝም ።

ዳሩ ግን አንዳንድ ዘመን ብርድ የሚባል በሽታ አለበት በታሕሣሥና በጥር እየተነሣ እህሉን ሁሉ ያጠፋዋል ። ይኸን ካለፈ በኋላ ግን ምንም ጥፋት የለበትም ፤ እንዲህ አድርጎ በየክቲትና በመጋቢት መከሩን ይሰበስባል ፤ ዛሬም በዚህ ወራት ባንድ ብር አንዳንድ ዳውላ ይሸመታል ። በጅሩ ዙሪ ያሉትም የቄላ አገሮች ማሽላ ዘንጋዳ ጤፍ ኑግ ሰሊጥ ሱፍ ሙዝና ሎሚ ጥጥ ያበቅላሉ ። በዚያም አገር የሚኖሩ ሰዎች ሞረት ከጥጹ ፤ ደብብ ከጸጋ እንወለዳለን እያሉ የሚመኩ ጥንተ ክርስ ቲያን ናቸው ። ነገር ግን ዝንጀሮ የሚባል ዋና ባላንጣ ስለ ወደቀባቸው ከወፊት እስከ ማታ ድረስ እሱን ሲጠብቁ ፍጹም ዕረፍት አያገኙም ።

5 ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ታኅሣሥ 23 ቀን 1917 ዓ.ም.


በዚያ ጊዜ ጋዜጣውን ለሕዝብ ለማስታወቅና ለማስለመድ ብዙ ድካም ነበረ:: የዲሬክተሩም ትጋት በተለይ የሚደነቅ ነበር::

የራስ ሥዩም ባለቤት ወይዘሮ ተዋበች ሚካኤል (የንጉሥ ሚካኤል ልጅ) ጥር 12 ቀን አዲስ አበባ ላይ ስለሞቱ ሬሣቸው ወደ ደብረ ሊባኖስ ተወስዶ በእየታቸው በወይዘሮ ባፌና መቃብር ቤት ተቀበረ:: ኀዘንተኞቹ ከተመለሱ



በኋላ ጃንሜዳ ላይ ድንኳን ተተክሎ ጥር 16 ቀን ውሎ ሆነና የልቅሶው ሥነ ሥርዓት ከፍ ባለ ሁናቴ ተፈጸመ:: የሥርዓቱ ዝርዝር ጥር 21 ቀን ታትሞ ወጥቶ ነበርና ጋዜጣው ለመኳንንትና ለኀዘንተኞቹ በነፃ ታድሎ ብዙዎች ስለ አነበቡት የጋዜጣው ዝና በሁሉም ዘንድ የታወቀ ሆነ:: ከዚህ በኋላ የጋዜጣው አንባቢና የማኅበረተኞቹ ቊጥር እያደገ ይሄድ ጀመር::

## ስለ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት መከፈት



28 ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት አስተማሪዎችና ተማሪዎች (ቀስቱ መርስዔ ኀዘንን ያመለክታል)

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከጃንሜዳ በስተ ሰሜን በኩል በሚገኘና የወይራ ዛፍ በሞላበት በአንድ ቦታ ላይ ዘመናዊ ትምህርት ቤት ለማሠራት ስላሰቡ ከሁለት ዓመት በፊት ሕንፃውን አስጀምረው ነበር:: በዚህም ዓመት ሕንፃው ተጠናቆ ስላለቀ በስማቸው የሰየሙትን የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ሚያዝያ 19 ቀን 1917 ዓ.ም. ሰኞ በ10 ሰዓት መርቀው ከፈቱት::

ለምረቃው በዓል የየሌጋሲዮኑ ሚኒስትሮችና ቆንስሎች ተጠርተው መጥተው ነበር:: እኔም ለግዕዝና ለአማርኛ ትምህርት በአስተማሪነት ተመድቤ ታዝዤ በስፍራው ላይ ነበርኩና ስለ በዓሉ ሁናቴ ያየሁትን በሚከተለው እገልጻለሁ፤

የትምህርት ቤቱ ሹም ሐኪም ወርቅነህ ከ15 ቀን በፊት ጀምረው የመዘገቧቸውን አዳሪዎችና ተመላላሾች ተማሪዎች በአንድ በኩል አሰልፈው፣ አስተማሪዎችንም በሌላው በኩል አቁመው ሲጠባበቁ ቈዩ:: እርባዎቹ

የአርመን ልጆችም[170] በትምህርት ቤቱ ደጃፍ ላይ ተሰልፈው ግቢውን በሙዚቃ ዜማ አደመቁት።



29 አርባዎቹ የአርመን ልጆች

ከዚህ በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽ በመኳንንት ታጅበው መጡና ከትምህርት ቤቱ በር ላይ ሲደርሱ ሹሙ ሐኪም ወርቅነህና ዳሬክተሩ ሙሴ ጕዮን ከአስተማሪዎችና ከተማሪዎች ጋር ሆነው ሰላምታ ሰጥተው ተቀበሏቸው።

[170] በትልቁ የዓለም ጦርነት ጊዜ ቱርኮች በአርመኖች ላይ ብዙ መከራ ስላደረሱባቸውና ስለ ፈጁዋቸው የሙት ልጆች የሆኑት የአርመን ወጣቶች ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ ሌላም ስፍራ እየተሰደዱ እንደየችሎታቸው በየሥራው ተሰማርተው ነበር። ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በ1916 ዓ.ም. አውሮጳን ለመጐብኘት በጕዞ ላይ ሳሉ መጀመሪያ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው ነበርና ሙዚቀኞቹ የአርመን ወጣቶች ሙዚቃ እየነፉ ደስ አሰኝተው በአክብሮት ተቀበሏቸው። ከዚህም በኋላ በኢየሩሳሌም ያሉት የአርመን ሊቀ ጳጳሳት አርኪቢሾፕ ቱሪዚያን ከልዑል ዘንድ ቀርበው የወጣቶቹን ሁናቴና ችግር ስለ አስረዷቸው ከእነርሱ ውስጥ አርባውን ልጆችና አስተማሪያቸውን ወደ ኢትዮጵያ ለመውሰድ እንደሚፈቅዱ ገለጹላቸው። ሊቀ ጳጳሳቱም ስምምነቱ ለአራት ዓመት የሚጸና ሆኖ እንዲሄዱ ከልዑል አልጋ ወራሽ ጋር ተነጋግረው ጨረሱላቸውና በ1917 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ በመርከብ ተሣፍረው በጅቡቲ በኩል ወደ ኢትዮጵያ መጡ። የመንገዱንም ኪሣራ ሁሉ ልዑል አልጋ ወራሽ ከፈሉላቸው።

መስከረም 16 ቀን 1917 ዓ.ም. አዲስ አበባ ሲገቡ ባልደረባ ሙሴ አብርሃም ካራጂያን ተሰጣቸው። የመኖሪያ ስፍራም የልጅ ኢያሱ ግቢ በሚባለው ውስጥ ትልቁ አዳራሽ ተፈቀደላቸውና በነፍስ ወከፍ የወር ቀለብ 35፣35 ብር እየተቀበሉ በአስተማሪያቸው በሙሴ ኬበርክ ናልባንዲያን መሪነት የሙዚቃውን ሥራ ያካሄዱ ጀመር። የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤትም ለሙዚቃ ትምህርት የመረጣቸው ልጆች ከእነርሱ ዘንድ አብረው እየተማሩ በሙዚቃ ሠለጠኑ።

አራት ዓመት በተፈጸመ ጊዜ ስምምነቱን በማደስ አንድ ዓመት ተጨመረላቸው። ከዚያ በኋላ ግን ከመካከላቸው እኩሉ ወደ ውጭ አገር በመመለስ እኩሉም በሞት በመለየት ቍጥራቸው ተቀንሶ የተረፉት አብዛኞቹ በልዩ ልዩ የእጅ ሥራና በንግድ ላይ ተሰማርተው ራሳቸውን እየቻሉ በአዲስ አበባ ተቀመጡ። ልዑል አልጋ ወራሽም የዜግነት ፈቃድና ርስት በመስጠት ደስ አሰኟቸው። መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ "የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ"፣ ገጽ 286።



የአርመን ልጆችም "ማርሽ ተፈሪ" የሚባለውን አዲሱን መዝሙር በሙዚቃ ዘመሩላቸው። ይህ መዝሙር በዚያ ዘመን ገና መጀመሩ ነበር።

ልዑል አልጋ ወራሽ ከትምህርት ቤቱ አዳራሽ ገብተው በተለይ በተዘጋጀው ወምበር ሲቀመጡ መኳንንቱና የተጠሩት እንግዶች በቀኝና በግራ በየማዕርጋቸው ስፍራ ስፍራቸውን ይዘው ተቀመጡ። ከኢትዮጵያ መኳንንት ራስ ሥዩም፣ ፊታውራሪ ደስታ ዳምጠው፣ ቀኛዝማች ዓምዴ፣ ከንቲባ ነሲቡ ዘማኔል፣ ብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴና አቶ ሣህሌ ፀዳሉ ነበሩ።

ከዚህ በኋላ ሐኪም ወርቅነህ በልዑል አልጋ ወራሽ ፊት ቆመው ንግግር አደረጉ። ከዚያም ቀጥሎ ልዑል አልጋ ወራሽ ስለ ትምህርት ነገር ከፍ ያለ ኃይለ ቃል ያለበትን ታሪካዊ ንግግር አደረጉ። ቃሉም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው፤

*የተወሰነ ቦታ የሌለህ በሁሉ የመላህ አምላካችን ሆይ በፈቃድህ ያስዠመርከኝን ያስፈጸምከኝ ይህንንም እንድናገር የፈቀድህልኝ ምስጋና ላንተ ይሁን።*

*ስለ ኢትዮጵያ ታላቅነትና ቀደምትነት ይልቁንም በእረመኔ ተከባ ስለ ሃይማኖቷና ስለ ነፃነቷ እየተጋደለች የቈየች መሆንዋን እንኳን እኛ ገንዘባችን ገንዘቧና የውጪ አገር የዓለም ሕዝብ ሁሉ ያገርዋን መልካምነት የታሪኳን ታላቅነት በቃልም በመጽሐፍ ሲናገሩት የምንሰማው ነው። ነገር ግን ለኢትዮጵያ ሆነኝ ነው እንጂ ነበር ምን ይጠቅማል። በመንግሥታቸው ጽናት ባናኑዋራቸው ሥርዓት ፍጹም ተስፋ እንዳላቸው እንደ ዓለም ሕዝቦች ሁሉ በአፍሪካ ነፃነቷን ይዛ ለቈየችው ለኢትዮጵያ የምትደረጅበትን ለመንግሥቷ ጽናት ለሕዝቧ ጸሎት የሚሆናትን ዕውቀት ፈልጎ አግኝቶ ሥራ መሥራት ነው። ሥራም ለመሥራት አስቀድሞ መሣሪያን ማበጀት ነው።*

*ለኢትዮጵያ ነፃነትና ጽናት ወሰንዋን ጠብቆ አሳፍሮ አስከብሮ ለማኩራትና የሕዝቧ ልብ የታመነ ኃይል እንዲኖረው ለማድረግ መሣርያው ትምህርት መማር ነው። ከዚህ ቀደም ሕዝባቸውን በዕውቀት እንዲሠለጥን ዳግማዊ አጤ ምኒልክ የተማሪ ቤት እንዳቆሙ ሰው ሁሉ የሚያውቀው ነው። ለመማርም ትጋትና ቅን ልቡና ያስፈልጋል።*

*ተማሪ ቤት ለማቆምና ልጆቻቸው ያልሆኑ ተማሪዎችን መርዳት ልጆቻቸውንም እንዲማሩ ማድረግ ኢትዮጵያን ለሚወዱ ሁሉ ይገባል። በንግግር አሁን ማንም ሰው ሲጠይቁት አገሬን ኢትዮጵያን እወዳለሁ የማይል ሰው የለም። ይህ እስካሁን ያፍ ልማድ ብቻ ነው እንጂ ወዳጅ የሚሉትን ሰው በችግሩ ካልረዱት በተጨነቀ ጊዜ ካልደረሱለት የወዳጅነቱ ምልክት እምን ላይ ነው።*

*አሁንም ለሀገሬ ለኢትዮጵያ ወዳጅ ነኝ የሚል ሰው ሁሉ የወዳጅነቱን ምልክት ለማሳየት ለተማሪ ቤት መርዳትና የሚቻለውን ተማሪ ቤት መሥራት፣ ልጁን ማስተማር የሚገባ ነገር ነው። ይህንንም የሚያደርጉ ሁሉ በውነት የሀገራቸውን ፍቅር ገለጹ ማለት ነው።*

*የልጆቹንና የወገኑን መማር የሚወድና ለተማሪ ቤትም የሚረዳ ሰው መጀመሪያ ራሱ ይጠቀምበታል። ሁለተኛም በልጁ በወገኑ ጥፋት*

*ሳይጸጸት ደስ ብሎት ይኖራል። ሦስተኛም ለሀገሩ የውነተኛ ፍቅር እንዳለው ይገልጽበታል።*

*የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የማይፈጽምበት ከሰው ፍርድ የማያመልጥበት የእውነተኛ ባርነት እግዚአብሔር ሳያዳላ የፈጠረውን አእምሮ ሥራ ማስፈታትና ለድንቁርና መገዛት ነው።*

*እናንተም በዚህ ተማሪ ቤት የሰበሰብኋችሁ ልጆች ወደፊትም እተማሪ ቤቱ የምትገቡ ሁሉ ዕውቀት ለሰው የምትጠቅም እንደሆነች በብዙ መጽሐፍ እንደ ተጻፈ ታውቃላችሁ። ወደፊትም የምትማሩት ነው። ዕውቀት የተጨበጠች ማንም የማይወርሳት ገንዘብ ናት። በሰው ልብ ያልታሰበ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምታወርስ በመከራም ጊዜ ጠበቃ ናትና እግዚአብሔር እንደዚህ ለተባለች ጥበብና ዕውቀት ያብቃችሁ።*

*ይህችንም የዕውቀት ምግብ ቀጥታ የምታሳድጋችሁን ተማሪ ቤት በጥበብ አድጋችሁ በአእምሮ በምትጐለምሱበት ጊዜ እግዚአብሔር እንደየዕድላችሁ በሚሰጣችሁ ዕውቀት የሀገራችን መማሪያ ናትና እንዳትጠብ እንድትሰፋ እንዳትወድቅ እንድትበረታ እንድትረዱዋት እለምናችኋለሁ።*

*ይህች ዕለት ዛሬ ለኔ ምን ያህል የደስታ ቀን እንደሆነች ልቤና ፈጣሪዬ ነን የምናውቀው። እግዚአብሔርም ቢያድለኝ ይህች ተማሪ ቤት መከፈቷን አይቼ ደስ እንዳለኝ ተምራችሁ ለሀገራችሁ መርዳትን፣ በኢትዮጵያ ትምህርት መስፋፋቱንና የተማሪ ቤት መብዛቱን እንዲያሳየኝ እመኛለሁ።*

*በአውሮጳ አገር በታላላቅ ተማሪ ቤት ብዙ ብዙ ተማሪዎች የሚማሩበት የሚያድሩበት እንደ ተሠራ አይቻለሁ። ይኸውም በዕውቀት መሣሪያነት ገንዘብ አግኝተው አስፋፍትና ሠሩት እንጂ ምንም ሐሳቡና ምኞቱ ታላላቅ ሥራ ለመሥራት ቢሆን ባንድ ጊዜ ለመፈጸም የሚቻለው የለም።*

*እንደዚሁ በትንሽ በትንሽ እየተጀመረ ከታላላቅ ሥራና አገር ከመጥቀም ይደርሳልና መቶ ሺህ ተማሪ ቤት ለመባል ቍጥር ከ፩ እንዲዠመር፣ ኸያ ተማሪ ቤት ለመባል ቍጥር ከ፩ እንዲዠመር ኢትዮጵያ ባሉ ተማሪዎችና የትምህርት ቤቶች በቍጥር ተራ ውስጥ የምትገቡ እንደሆናችሁ የተረጋገጠ ነው።*

*አሁንም ይህች ተማሪ ቤት ምሳሌ ናትና በኢትዮጵያ ከዚህ በላይ ተናግሬ እንደ ተመኘሁት እንድትሆን ጥርጥር የለበትም።*

*ተማሪ ቤት የመረረችውን ያህል ትጣፍጣለችና ያላችሁትም የምትመጡትም ምክሬን ሰምታችሁ ለተማሪ ቤቱ ያቆምሁትን ደንብ እንድትፈጽሙ እለምናችኋለሁ።*

*በዚችም ተማሪ ቤት ያቆምሁት የውጪ ቋንቋና ጥበብ ብቻ አይደለም። የሀገራችንም ቅዱሳት መጻሕፍት ወልዶ ዋሕድ ሃይማኖት የሚነገርባት ናት።*

*የሀገሩንም ትምህርት ጽሕፈት ቋንቋ እንደሚገባው የማያውቅ፣ የውጪን እማራለሁ የሚል ምሳሌው ቀዛፊ እንደሌለው ታንኳ ነው። የሀገራችንን ዕውቀትና ትምህርት ተግታችሁ ተማሩ።*

*በመጨረሻም የምነግራችሁ ቅዱስ ዳዊት እግዚአብሔር የአምር ሕሊናህሙ ለጠቢባን ከመ ከንቱ ውእቱ ያለው በተማረው መጠን*



*አሳቡንና ዕውቀቱን ወደ ተንኰል የሚመራውን ነውና፣ እውነተኛውንም ጥበብ ለሚፈልግ ሰው ጌታ በወንጌል ፭ ወርቅ የሰጠው ባሪያ ዓሥር አድርጎ ቢመልስ እንደ ተመሰገነና በብዙ አሀጉር ላይ እንደ ተሾመ እንድትሆኑ፤ ፩ ወርቅ የሰጠው ባሪያ ግን ቀብሮ አስቀምጦ ያንኑ ቢመልስ እንደ ረገመውና በሥቃይ እንዲኖር እንደ ተፈረደበት እንዳትሆኑ እለምናችኋለሁ።*

*አሁንም የልቡናችሁ መሠረት እግዚአብሔርን በመፍራት አገርን በመውደድ የተጠመደ እንዲሆን እግዚአብሔር የሁላችንንም የልባችንን መሠረት በዚህ ያድርገው ብዬ ርኅሩኅ ፈቃዱን እለምናለሁ።*

*እግዚአብሔር ንግሥተ ነገሥታትን ይጠብቅ*
*ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር*
*ኢትዮጵያ ሕያው ትሁን።*

ልዑል አልጋ ወራሽ ይህን ተናግረው ሲጨርሱ ሦስት ጊዜ ከፍ ያለ ጭብጨባ ተጨበጨበ። ከዚያም ቀጥሎ የሻይና የብስኩት የሻምፓኝም ግብዣ ተደረገ። ለተማሪዎቹም ብስኩት ታደላቸውና በየክፍላቸው እየገቡ ተቀመጡ። ከዚህ በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽ መኳንንቱንና እንግዶቹን አስከትለው የትምህርት ክፍሎችንና መኝታ ቤቶችን ጐብኝተው ሲመለሱ የበዓሉ ፍጻሜ ሆነ።

በማግሥቱ ሚያዝያ 18 ማክሰኞ የትምህርቱ ሥራ ተጀመረ። በዚያ በመጀመሪያው ጊዜ የተመዘገቡት ተማሪዎች 32 አዳሪዎችና 40 ያህል ተመላላሾች ነበሩ። በኋላ ግን የአዳሪዎቹም ሆነ የተመላላሾቹም ቍጥር በየቀኑ እያደገ የሚሄድ ሆኗል።

በመጀመሪያ ጊዜ የነበሩት አስተማሪዎች የሚከተሉት ናቸው፤

| | |
|---|---|
| ክቡር ሐኪም ወርቅነህ እሸቴ | ዋና ሹም |
| አቶ ደምሴ ወልደየስ | ዋና ጸሐፊ |

*ለፈረንሳዊኛ ክፍል*

| | |
|---|---|
| ሙሴ ዣን ጉዮን | አስተማሪና የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር |
| ሙሴ ፖል ላቡርዳሪ | አስተማሪ |
| አቶ ተዐውቀ ሀብተ ወልድ | አስተማሪ |

*ለእንግሊዝኛ ክፍል*

| | |
|---|---|
| አቶ ኤፍሬም ተወልደ መድኅን | አስተማሪና የሹሙ እንደራሴ |
| አቶ መንገሻ ከፈላ፣ | አስተማሪ |

*ለግዕዝና አማርኛ ትምህርት*

| | |
|---|---|
| አቶ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ | አስተማሪ |

*ለሥዕል ትምህርት*

| | |
|---|---|
| ሙሴ ፓፓጊያን | አስተማሪ ለሙዚቃ ትምህርት |
| ሙሴ ናልባንዲያን | አስተማሪ |

የመጀመሪያው ጊዜ አስተማሪዎች እነዚህ ሲሆኑ ከዚያ በኋላ ግን ቍጥራቸው እየጨመረ ሄዷል። ሰዎቹም በየጊዜው ተለዋውጠዋል። በሚቀጥለው ዓመት በ1918 ዓ.ም. በዲሬክተሩ በሙሴ ጕዮን ስፍራ ሙሴ ቶማሲኒ ተተኩ። እንዲሁም የተጨማሪዎቹ መምህራንና ሹማምንት ስም የሚከተለው ነው፤

| | |
|---|---|
| ሙሴ ሰርኪስ አንታብልያን | እንግሊዝኛ አስተማሪ |
| አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ | ሞግዚት |
| መምህር ራስ ወርቅ | የግዕዝና አማርኛ አስተማሪ |
| አቶ ስመኝ መኰንን | የእንግሊዝኛ አስተማሪ |
| አቶ ገብረየስ ኩርፋ | የፈረንሳይኛ አስተማሪ |
| አቶ ገብሬ ገብረ ጊዮርጊስ | የፈረንሳይኛ አስተማሪ |
| ሙሴ ዲትሪሽ[171] | የጂምናስቲክ አስተማሪ |
| አቶ ሚልኮ | የኤሌክትሪክ ክፍል አላፊ |

በዚህ ጊዜ ለአማርኛ ማስተማሪያ ይሆኑ ዘንድ የተገኙት መጻሕፍት እንደ *ማር ይስሐቅና* እንደ *ዮሐንስ አፈ ወርቅ* የመሰሉት ስለ ሆኑ ለአማርኛ ትምህርት በቂ ነገር አልተደራጀም ነበር። ስለዚህም እኔ «*ትምህርተ ሕፃናት*» በሚል አርእስት አንድ ትንሽ መጽሐፍ ጻፍሁና ለልዑል አልጋ ወራሽ ባቀርብላቸው በቶሎ ይታተም ብለው ስላዘዙ በግንቦት 1 ቀን 1917 ዓ.ም. በማተሚያ ቤታቸው በነፃ ታትሞ ወጣ። ድርሰቱ ግብረገብነትን የሚያስተምር ነበርና ለጊዜው ማስነበቢያ ሆነ። ከዚያም ቀጥሎ ከንቲባ ገብሩ በጻፉት የአማርኛ ሰዋስውና አቶ ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት በጻፈው አጭር የዓለም ታሪክ ማስተማር ተጀመረ። ሆኖም ለአማርኛው ክፍል የተሟላ ማስተማሪያ ገና አልቀረበም ነበር። ተማሪ ቤቱም በክረምቱ ወራት ለዕረፍት ሳይዘጋ እንደ ቀጠለ ከረመ።


በዚያ ወራት የአማርኛ መዝሙር በሙዚቃ እየተዘመረ ተማሪዎች ዜማውን ማጥናት ጀመሩ። የዚህ ዓይነት መዝሙር ገና መጀመሩ ስለ ሆነ ለጆሮአችን እንግዳ ነገር ሆኖ ሰነበተ። መዝሙሩን የደረሱትና ዜማውን ያወጡት አቶ ኤፍሬም ተወልደ መድኅን ሲሆኑ በሙዚቃ ያቀነባበረው ግን ሙሴ ናልባንዲያን ነው።

1. የኢትዮጵያን ብርሃን
   ዘለዓለም ያኑርልን
   የነፃነት አምባችንን
      አምላክ ይጠብቅልን
      ለሦስት ቀለሞች ጽናት
      ላገር ለሕዝባችን ልማት
      ዕውቀት እውነት ሊነግሡበት
      ተፈሪን ያቁምልን
2. የተ፡መ፡ት፡ቤት ተማሪዎች
   ለኩራታችን ሦስት ቀለሞች

[171] የሩሲያ ስደተኛ። ኋላ ኮሙኒስት ነው ተብሎ ተከሶ ከሀገር ተባሯል።



   ክብር መሆን በሕይወት በሞት
   ነው የኛ ምኞት
      ለሦስት ቀለሞች ጽናት
      ላገር ለሕዝባችን ልማት
      ዕውቀት እውነት ሊነግሡበት
      ተፈሪን ያቁምልን።


ት ም ሀ ር ተ ፡ ሕ ፃ ና ት ።

ተጻፈ ፡ ከመርስዔ ፡ ኅዘን ።

ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
ለቤተ ሳይዳ ሆስፒታል በተሰጠ ማተሚያ ቤት ሁለተኛ ታተመ።
፲፱፻፲፯ ዓ ም አዲስ አበባ ።

6 ትምህርተ ሕፃናት፤ የመርስዔ ኅዘን የመጀመሪያ መጽሐፍ

## ስለ ልዩ ልዩ ነገር

በዚህ ዓመት የግዕዝ ፍትሐ ነገሥት [172] በ17 ብር ገዛሁና ከሥራ በኋላ ባለኝ በትርፍ ጊዜያት ሁሉ ከጐንደሬው ከአለቃ አየለ ዘንድ እማር ጀመር። አለቃ አየለ በ1894 ዓ.ም. ከትልቁ መምህር ከአለቃ ኀሩይ ጋር ከጐንደር መጥተው አዲስ አበባ በልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ ባለው በማርቆስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ማረፊያ ቤት ተሰጥቷቸውና ጉባኤ ዘርግተው ሲያስተምሩ የነበሩት ናቸው።

በሰኔ ወር የቀበና አቦ መኖሪያዬን ትቼ በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ውስጥ እቀመጥ ጀመር። ምክንያቱም የትምህርት ቤቱ ሹም ሐኪም ወርቅነህ ለአስተማሪዎች ሁሉ መኖሪያ ቤት ሲያድሉ ለኔም አንድ መኖሪያ ቤት ስለሰጡኝና ስፍራውም ምቹ ስለሆነልኝ ነው። በዚህ ዘመን ባለቤቴ ወይዘሮ እታገኘሁ ባዬ ጸንሳ ነበርና ወደ እናትዋ ዘንድ ሄዳ አድአ ድሬ ላይ በነሐሴ 10 ቀን 1917 ዓ.ም. እሑድ በደኅና ስለተገላገለች ወንድ ልጅ አገኘን። የሕፃኑ ክርስትና መስከረም 14 ቀን 1918 ዓ.ም. ኀሙስ ነበርና በድሬ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ጥምቀት ተፈጽሞለት ገብረ ክርስቶስ ተባለ። የክርስትና ልጅነቱም ለታቦቱ መድኃኔ ዓለም ስለተሰጠ ገባሬ ሠናይ ዲያቆን ጣቱን ይዞ ክርስትና አነሣው።

[172] ፍትሐ ነገሥት የመንፈሳዊና ሥጋዊ ሕግ ሰነድ ነው። ከዐረቢኛ ወደ ግዕዝ የተተረጐመው በ15ኛው ክፍለ ዘመን በአጼ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ ንግሥ (1444-1468 ዓ.ም) እንደሆነ ይታመናል። በዐረቢኛ የመጽሐፉ ርእስ "ንባኤ ቀኖናት" ሲሆን ጸሐፊው ግብጻዊው ኢብን ኤል አሳል ነው። በ1962 ዓ.ም. የፍትሐ ነገሥት ንባብና ነጠላ ትርጓሜው እንዲሁም መጽሐፈ ሕግጋት ዐበይት ክፍል አንድ በብላታ መርስዔ ኀዘን ሊቀ መንበርነት በሊቃውንት ተዘጋጅቶ ለኅትመት በቅቷል። ምንጭ - ሥርግው ሀብለ ሥላሴ፤ የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት።

# ምዕራፍ 25

### 1918 ዓመተ ምሕረት

ስለ ሽልማት፣ ከሥራ ወደ ሥራ ስለመዛወሬ፣ ስለ ሥራው መስፋፋት፣ ስለ አማርኛ ሰዋስው፣ ስለ ልዩ ልዩ ነገር

## ስለ ሽልማት

በ1918 ዓ.ም. የመስቀል ደመራ በዓል ከወትሮው በሚበልጥ ሥርዓት በሰልፍ ደምቆ እንዲከበር ስለታሰበ በዋዜማው መስከረም 15 ቀን በታላቁ ቤተ መንግሥት ለሹማምንትና ለሠራተኞች ብዙ ሽልማት ተሰጠ። ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪም ለግቢያቸው ሹማምንትና ሠራተኞች ልዩ ልዩ ሽልማት ስለሰጡ በየተሸላሚው ቤት እምቢልታ ይሰማ ነበር። ከተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤትም እኔ ለሽልማት ተጠርቼ ወደ ልዑል ግቢ ሄድሁና ድርብና ካባ አብደላከኒ ቀሚስ ተሸልሜ እምቢልታ እያስነፋሁ ወደ ቤቴ ተመለስሁ።

በማግሥቱ መስከረም 16 ቀን ቅዳሜ በፍልውሐ ሜዳ ሰልፍ ተደረገ። በዚህ ጊዜ የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት አስተማሪዎች ከክብር ዘበኛ ቀጥሎ እንዲሰለፉ ስለተፈቀደላቸው ተሰልፈን ዋልን። እኔም ያን ሽልማቴን ለብሼ ተሰልፌ ነበር።

በዚህ ወር መስከረም 4 ቀን ጌታ አለቃ ገብረ መድኅን አሰቦት ላይ ማረፋቸው ስለተሰማ በኀዘን ሰነበትሁ። የእርሳቸው ታሪክ በ*ሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ* የንግሥት ዘውዲቱ የዘመን ታሪክ ላይ ይገኛልና ከዚያ መመልከት ነው[173]።

## ስለ ሥራ መስፋፋት

በዚህ ዓመት የትምህርት ቤቱ ሥራ እየተስፋፋና የአዳሪዎች ቍጥር እያደገ ይሄድ ጀመር። ስለዚህም ሐኪም ወርቅነህ ትጋቴንና የሥራዬን ይዞታ ተመልክተው ቀለቤን ከ10 ወደ 15 ብር አሳደጉት።

አዳሪዎቹ ተማሪዎችም በሚገባ ተጠብቀው እንዲያድጉ በማለት አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ አስተዳዳሪ ሆነው በዚህ ዓመት ተሹመው ገቡ። እንዲሁ ደግሞ በመንፈሳዊ ረገድ የሃይማኖትና ሥርዓት (ግብረ ገብነትን) የሚያስተምርና

[173] ስለ አለቃ ገብረ መድኅን አጭር ታሪክ አባሪ ሐ ገጽ 247 ይመልከቱ።

በቅስና ሥልጣን ተማሪዎቹን የሚያናዝዝ መምህረ ንስሐ ማስፈለጉን ለሐኪም ወርቅነህ ብነግራቸው አሳቡን በቶሎ ተቀበሉት። ስለዚህም በእንጦጦ ማርያም ያሉት ርዕሰ ደብር ራስ ወርቅ ለዚህ ሥራ ተመርጠው በታኅሣሥ ወር ሥራ ጀመሩ።

## ስለ አማርኛ ሰዋስው

በአዲስ ሥርዓት ለመጻፍ የጀመርሁትን የአማርኛ ሰዋስው በዚህ ዓመት ውስጥ የመጀመሪያውን ክፍል ጨርሼ በትምህርት ሥራ ላይ እንዲውል አደረግሁት፤ ጽሑፉ ገና በማተሚያ ስላልታተመ በጥቁር ሳንቃ[174] ላይ እየጻፍሁ ለተማሪዎቹ አቀረብሁላቸው። እነርሱም በየደብተራቸው እየገለበጡ ካጠኑት በኋላ በትምህርቱ ስለተደሰቱበት እንደገና ጨምርልን እያሉ ይወተውቱኝ ጀመር።

ሐኪም ወርቅነህ[175] የሰዋስዉን ጅምር አይተው ደስ ስላላቸው፣ በጽሑፉ እንድተጋና ወደ ፍጻሜ እንዳደርሰው አደራ እያሉ መከሩኝ። ምክራቸውም ለትጋትና ለብርታት ተጨማሪ ምክንያት ሆነልኝ። ሐኪም ወርቅነህ ርኅሩኅነትና ቅንነት የተፈጥሮ ባሕርይ የሆነላቸው እውነተኛ ሰው ናቸው።

## ስለ ልዩ ልዩ ነገር

በዚህ ዓመት ከነጋድራስ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤልና[176] ከባላምባራስ ግርማ ያየህ ይራድ ጋር ተዋውቀን ወዳጅነት ጀመርን። እነዚህ ሰዎች ለሀገር አሳቢዎችና ተቆርቋሪዎች ስለሆኑ፣ ሐሳብ ለሐሳብ እንግባባ ነበርና ግንኙነታችን እየሰፋ ይሄድ ጀመር።

እንዲሁ ደግሞ በዚህ ዓመት ውስጥ «የፍቅርና የአገልግሎት ማኅበር» ስለተመሠረተ፣ እኔም ማኅበርተኛ ሆኜ ከማኅበሩ ገባሁ። የማኅበሩ


[174] ጥቁር ሰሌዳ።

[175] የሐኪም ወርቅነህ አጭር ታሪክ በብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ የተጻፈ አባሪ መ ገጽ 253 ይመልከቱ።

[176] ነጋድራስ (በኋላ ፊታውራሪ) ታፈሰ ግንቦት 28 ቀን 1892 ዓ.ም. አዲስ አበባ ላይ ተወለዱ። አባታቸው ገና በሕፃንነት ሳሉ ስለሞቱ ያደጉት አጎታቸው ፊታውራሪ (ደጃዝማች) አባ ውቃው ዘንድ ነበር። በ1900 ዓ.ም. ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ሲከፈት ከተማሪዎቹ አንዱ ነበሩ። ከሰገሌ ጦርነት በኋላ በልዩ ልዩ የአገር አስተዳደር ሥራና በሥራ ሚኒስትርነት አገልግለዋል። የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ሱማሌላንድ የወሰን ክልል ሥራ ጊዜ በኢትዮጵያ በኩል ለተሾሙት ወሰን ተካላዮች ባልደረባቸውና የጉዳዩ ተከታታይ ነበሩ። በጠላት ወረራ ዘመን በስደት ፈረንሳይ አገር ነበሩ። በ1937 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በፍርድ፣ በሥራና በፖስታ ሚኒስትርነት፣ በአምባሳደርነት፣ በሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አማካሪነትና በምክትል ፕሬዚዳንትነት አገልግለዋል። ሚያዝያ 8 ቀን 1956 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ፊታውራሪ ታፈሰ ከብላታ መርስዔ ኀዘን ጋር እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው በቅርብ ወዳጅነት ኖረዋል።



መሥራችና መሪ ሐኪም ወርቅነህ ስለሆኑ፣ ታላላቅ መኳንንትና የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበርተኞች እየሆኑ ገቡ። የማኅበሩ ደንብ ሲሰናዳ የኮሚቴ አባል ሆኜ ነበር። ደንቡ ከቆመ በኋላም ሐኪም ወርቅነህ ፕሬዚዳንት ሲሆኑ እኔ የዋና ጸሐፊነቱን ሥራ እሠራ ጀመር፤ ይህ ሥራ ከብዙዎቹ ጋር የሚያገናኘኝ ሆኖ ነበር።



30 ሐኪም ወርቅነህ

ፋሲካ በዚህ ዓመት ሚያዝያ 24 ቀን ሆነ። ከፋሲካው በዓል በኋላ ሐኪም ወርቅነህ በአማርኛ የተጻፈ የዓለም ጅዖግራፊ እንዳርም ሰጥተውኝ ከደንበኛ ሥራዬ በላይ በተጨማሪ እሠራ ጀመር። ይህ ጅዖግራፊ ከ17 ዓመት በፊት ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ያስተረጐሙት ነው። ሆኖም በትልቁ የዓለም ጦርነት ምክንያት የጅዖግራፊው ሁናቴ ስለተለዋወጠ እንደገና ማስተካከልና መጻፍ አስፈለገ። ስለዚህም ከቤታቸው እያደርሁ ሌሊት ከእሳቸው ጋር ስንሠራ እናድር ነበር።

በዚህም ወራት ሐኪም ወርቅነህ ስልዑል አልጋ ወራሽ ነግረው ቀለቤን ወደ 25 ብር አሳደጉልኝ።

## ምዕራፍ 26

### 1919 ዓመተ ምሕረት

ስለ አማርኛ ሰዋሰው፣ ስለ ዓለም ጅዎግራፊ፣ ስለ ፍቅርና ስንበግቡት ማኅበር፣ ስለ ልዩ ልዩ ነገር

### ስለ አማርኛ ሰዋሰው

ከአንድ ዓመት በፊት ጀምሬው የነበረውን የአማርኛ ሰዋሰው ባለፈው ክረምት ስለጨረስሁት አሁን በጥቅምት ወር 1919 ዓ.ም. በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ደንበኛ ማስተማሪያ ሆኖ ይሠራበት ጀመር። ይህ ሰዋሰው «የንግግር ክፍሎችና የቃላት አገባብ» በተባሉ በሁለት ታላላቅ ክፍሎች የተመደበ ነው። ሰዋስዉን ሐኪም ወርቅነህ አይተው ደስ ስላላቸው በቶሎ ሊያሳትሙት አስበው ነበር። ዳሩ ግን ጊዜው ባይደርስ በዚያ ዘመን አልታተመም[177]።

የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት በክረምት ወራት ለዕረፍት ተዘግቶ ከርሞ ነበርና በመስከረም 18 ቀን ማክሰኞ ተከፍቶ ሥራውን ጀመረ። በዚህ ዓመት የተማሪዎች ቍጥር እየበረከተ ስለሄደ፣ አዲስ የትምህርት ክፍሎችና አስተማሪዎች ተጨምረዋል። ዲሬክተር የነበረውም ሙሴ ጕዮን ወደ አገሩ ስለተመለሰ፣ በእርሱ ስፍራ ሙሴ ቶማሲኒ የተባለ ፈረንሳዊ አስተማሪ ተተክቷል።

### ስለ ዓለም ጅዎግራፊ


በ1918 ዓ.ም. በሚያዝያ ወር ከሐኪም ወርቅነህ ጋር ለማረም የጀመርሁት የዓለም ጅዎግራፊ ዓሥር ወር ያህል ከደከምንበት በኋላ፣ በዚህ ዓመት በየካቲት ወር አልቆ ሐኪም ወርቅነህ ለልዑል አልጋ ወራሽ አቀረቡላቸው። አልጋ ወራሽም መጽሐፉን አይተው ደስ ስላላቸው በቶሎ እንዲታተም ፈቀዱና ለብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ተላልፎ ይታተም ጀመር። ለዚህ ሥራ ሐኪም ወርቅነህ እኔን አላፊ ስላደረጉኝ ከአስተማሪነት ሥራዬ ጋር በብዙ ትጋት ስሠራ ከረምሁ። ይህ ጅዎግራፊ በተዘጋጀበት ጊዜ ሐኪም ወርቅነህ እኔን እንግሊዝኛ በማስተማርና ጅዎግራፊውን በማስጠናት በብዙ ረድተውኛል። ይህን ሥራ ሁልጊዜ ማታ እየጀመርን ከሌሊቱ እስከ ሰባት ሰዓት ድረስ እንሠራ ነበር። ምክንያቱም ቀን ሁለታችንም በሌላው ሥራ

[177] ይህ ሰዋስው ከጠላት ወረራ በኋላ በ1935 ዓ.ም. ታትሞ ወጥቶ እስከ 1965 ዓ.ም. ገደማ ድረስ የትምህርት ቤቶች መደበኛ የአማርኛ ሰዋስው ማስተማሪያ ሆኖ አገልግሏል።



ተይዘን እንውል ስለነበረ ነው። የሐኪም ወርቅነህን ትጋትና ቅንነት የባሕርያቸውንም ትልቅነት ለማወቅና ለመረዳት የቻልሁትም በዚሁ ጊዜ ነው።

ይህ ጅዎግራፊ ሲዘጋጅ ሳለ ሐኪም ወርቅነህ በትምህርት ረገድ በብዙ ስለረዱኝ አመሰግናቸዋለሁ።



በአዲስ ሥርዓት ፡ የተሰናዳ ።

የአማርኛ ሰዋሰው ።

ከመርስዔ ፡ ኀዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ ፡ ተጻፈ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ. ም.

7 በ1935 ዓ.ም. የታተመው የአማርኛ ሰዋስው መጽሐፍ

## ስለ ፍቅርና አገልግሎት ማኅበር

በሐኪም ወርቅነህ ሰብሳቢነት የተቋቋመው የፍቅርና አገልግሎት ማኅበር የመጀመሪያ ዓመት በዓሉን በዚህ ዓመት በታኅሣሥ 17 ቀን አከበረና ሥራ አስኪያጁን እንደገና በድምፅ ብልጫ መረጠ። በዚህ ጊዜ ሐኪም ወርቅነህ ለፕሬዜዳንትነት አቶ ከበረ ኃይለ ሥላሴ ለምክትል ፕሬዜዳንትነት ሲመረጡ እኔም ለዋና ጸሐፊነት ተመርጬ ሥራውን ተረከብሁ። ይህ ሥራ ከማኅበሩ አባሎች ከነጋድራስ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤልና ከፊታውራሪ ገብረ ማርያም ጋር የቅርብ ወዳጅ እስከ መሆን አደረሰኝ። ማኅበሩ ላቆመው ለድኾች ተማሪ ቤትም የበላይ ሹም እንድሆን ተመርጬ አስተዳድር ጀመር። ከአንድ ዓመት በኋላም የተማሪ ቤቱን ሥራ ለአቶ ያሬድ አስተላልፌአለሁ።

## ስለ ልዩ ልዩ ነገር

ኢትዮጵያን ለመጐብኘት የመጣው የኢጣልያ መስፍን ዱክ ዴል አብሩዚ ግንቦት 12 ቀን በ9 ሰዓት የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ሲጐበኝ በሰልፍ ተቀበልነው። ተማሪዎቹም ከአቶ ኤፍሬም ተወልደ መድኅን የተደረሱትን ሁለት መዝሙሮች እያዜሙ ደስ አሰኙት። መዝሙሩ በሌላው የታሪክ መጽሐፍ ተጽፎ የሚገኘው ነው። ከዚህም በኋላ የሻይ ግብዣ ቀረበና በዚያው ጊዜ የቲያትር ጨዋታ አሳየን። ቲያትሩ በመምህራኑ ኅብረት የተደረሰ ሆኖ በመጨረሻው «ዘገብረ ሠናይ ኢየኀጉለ፤ አሰቦ»[178] የሚል ጥቅስ ነበረበት። ከጨዋታው በኋላ ሐኪም ወርቅነህ ንግግር አደረጉና ፍጻሜ ሆነ።

ግንቦት 29 ቀን ለኝ ባለቤቴ ወይዘሮ እታገኘሁ በቤተ ሳይዳ ሆስፒታል [179] በደኅና ተገላገለችና ሁለተኛ ወንድ ልጅ አገኘን። ይህ ልጅ በኋላ ጊዜ ውብሸት የተባለው ነው። ሐምሌ 8 ቀን ዓርብ አድአ በድሬ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ጥምቀት ተፈጽሞለት ኃይለ ኢየሱስ የሚል ስመ ጥምቀት ተሰጠው። የክርስትና ልጅነቱም ለታቦት ስለተሰጠ ገባሬ ሠናይ ዲያቆን ጣቱን ይዞ ክርስትና አነሣው።

በሐምሌ 18 ቀን ከሐኪም ወርቅነህና ከሌሎች ብዙ ሰዎች ጋር በባቡር ተሣፍሬ ጅቡቲ ወረድሁ። አቶ ደምሴ ወልደ ገብርኤል[180] አብሮኝ ወርዶ

[178] መልካም ጥሩ ነገር ያደረገውን ዋጋውን አያስቀርበትም።

[179] በኋላ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል፣ በደርግ ዘመን የካቲት 12 ሆስፒታል የተባለው።

[180] አቶ ደምሴ ወልደ ገብርኤል ሐምሌ 24 ቀን 1897 ዓ.ም. ደፋት ወምበርያ ሚካኤል ተወለዱ። ከብላታ መርስዔ ኀዘን ጋር በጓደኝነትና በቤተሰብነት ሳይለያዩ ኖረዋል። ሐምሌ 18 ቀን 1988 ዓ.ም. ዐረፉ። ሥርዓተ ቀብራቸው አዲስ አበባ፣ ቀበና አቦ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል።



ነበር። በጅቡቲ የባሕሩን ወደብና መርከቦችን ስንጐበኝ ዓሥር ቀን ያህል ቈየንና ወደ አዲስ አበባ ተመለስን።



31 ሐኪም ወርቅነህ ከወጣቶች ጋር። ከግራ ወደ ቀኝ መስፍን ቀለመ ወርቅ፣ ሐኪም ወርቅነህ፣ ቴዎድሮስ ወርቅነህ፣ መልአኩ በያን

ሐኪም ወርቅነህ ግን ለመንግሥት ጉዳይ ወደ አውሮጳና ወደ አሜሪካ ተልከው ስለነበረ ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅን[181] አስከትለው እንዲሁም

[181] በ1917 ዓ.ም. የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት በተከፈተ ጊዜ ከመጀመሪያዎቹ ተማሪዎች አንዱ ነበር። በ1920 ዓ.ም. የጅጅጋና የውጋዴን አውራጃ ዲሬክተር ሆኖ ያስተዳድር ጀመር። በ1923 ዓ.ም. ሐኪም ወርቅነህ የጨርጨርን አበጋዝነት በተሾሙ ጊዜ ልጅ መስፍንም ዲሬክተርነቱን ተሾሞ በጨርጨር አንድ ዓመት ተኩል ያህል ከሠራ በኋላ በሰኔ ወር 1924 ዓ.ም. በአክሱም የነበረ እድ ዲሬክተርነትንና የአሥመራ ቆንስልነትን ተሾመ። በ1926 ዓ.ም. ገደማ ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ የግራዝማችነት ማዕርግ ተሰጠውና በወለጋ የባሮች ነፃነት መሥሪያ ቤት ዋና ሹም ሆኖ ተሾመ። ኢትዮጵያ በጠላት ከተወረረች በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት በቢትወደድ ወልደ ጻድቅ መሪነት ጎሬ ላይ ተቋቁሞ ነበርና ግራዝማች መስፍን ለዚህ ለተቋቋመው

ግርጌ ማስታወሻ በሚቀጥለው ገጽ ይቀጥላል...

ለትምህርት ወደ እንግሊዝ አገር የሚሄዱትን ሦስት ሴቶች ልጆቻቸውንና የአልጋ ወራሽን ልጅ የሺ እመቤትን (በኋላ ፀሐይ የተባለችውን) ይዘው በመርከብ ተሣፍረው ተጓዙ። ለንደን ሲደርሱ ልጆቹን ከተማሪ ቤት አስገብተውና መልእክታቸውን አድርሰው ጉዞአቸውን ወደ አሜሪካ ቀጠሉ። የሄዱበት ምክንያት ስለ ጣና ባሕር ጉዳይ ነበርና ዋይት ኢንጂነሪንግ ኮምፓኒ የተባለ የአሜሪካ ኩባንያ በጣና ባሕር ላይ ግድብ እንዲሠራ ተነጋግረው ከአምስት ወር በኋላ በታኅሣሥ 10 ቀን 1920 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ። በእንግሊዝ አገር የነበረውን ልጃቸውን ቴዎድሮስን[182] ይዘው የመጡትም በዚሁ ጊዜ ነው።

እኔም ጅቡቲ ላይ በወባ ትኝኝ ተነድፌ ኖሮ ወደ አዲስ አበባ ስመለስ አመመኝና በዶክቶር ላምቤ ሆስፒታል ስታከም ከረምሁ። ሐኪም ወርቅነህ የአደራ ወረቀት ስለጻፉልኝ ሐኪሙ ዶክቶር ፖላክ በብዙ እንደረዱኝና እንደ ደከሙልኝ አስታውሳለሁ።

-----------------------------

*መንግሥት ከፍ ያለ አገልግሎት አበርክቷል። ራስ እምሩ ከፋ ላይ ሲማረኩ እሱም ተማርኮ ወደ አዲስ አበባ በእስረኛነት ተላለፈ። በየካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም. በግራዚያኒ ላይ በተጣለው ቦምብ ምክንያት ብዙ ኢትዮጵያውያን በተገደሉ ጊዜ ግራዝማች መስፍንም በጠመንጃ ተደብድቦ ሞቷል። ምንጭ - የብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ያልታተመ ጽሑፍ።*

[182] ቴዎድሮስ ወርቅነህ ሐኪም ወርቅነህ ከመጀመሪያ ባለቤታቸው ከኤለን ፋብሪክስ መስከረም 1 ቀን 1901 ዓ.ም. የወለዱት የመጀመሪያ ልጃቸው ነው። በጠላት ወረራ ዘመን በእስራት ኢጣልያ ተወስዶ ነበር።

# ምዕራፍ 27

## 1920 ዓመተ ምሕረት

**ስለ ዓለም ጅዖግራፊ፣ በትምህርት ቤት ስለተደረገ ሥነ በዓል፣ ሐኪም ወርቅነህ ከአውሮጳ ስለመመለሳቸው**

## ስለ ዓለም ጅዖግራፊ

1920 ዓ.ም. ዘመነ ዮሐንስ ሰኞ ባተ። ባለፈው ዓመት ተጀምሮ በእኔ አላፊነት ሲታተም የቈየው የሐኪም ወርቅነህ የዓለም ጅዖግራፊ በዚህ ዓመት እትማቱ አልቆ ለሕዝብ ይሸጥ ጀመረ። መጽሐፉ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነትን ስላገኘ ሁሉም ለመግዛት ተሽቀዳደመ።

የመጽሐፉ አርእስት «የዓለም ጅዖግራፊ፤ በአማርኛ፤ ከሐኪም ወርቅነህ፤ 1920 ዓ.ም. በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ» የሚልና 335 ገጽ ያለበት ነው።

ሐኪም ወርቅነህ ጅዖግራፊውን ለማስተርጐምና ለማሳተም መነሻ የሆናቸውን ምክንያት በመጽሐፉ መቅድም ከገለጹ በኋላ በሥራ ስለረዷቸውም ሰዎች በሰፊው ጽፈው ነበር። ቃሉም፤

> *ይህ የጅዖግራፊ መጽሐፍና ትርጓሜ የትምህርት ዕውቀት ባላቸው ወዳጆቼ በአቶ ኅሩይና (አሁን ብላቴን ጌታ ኅሩይ) በአቶ ወልደ ተክለ ሃይማኖት እርዳታ ተጽፎ በ1904 ዓ.ም. ተጨረሰ። ነገር ግን በዚያ ዘመን በአዲስ አበባ የመጻሕፍት ማተሚያ መዘውር[183] ስላልነበረ፤ ወደ ውጭ አገርም ሰድጄ እንዳላሳትመው የሚበቃ ገንዘብ ስላልነበረኝ ለጊዜው መታተሙ ቈይቶ ነበር። እኔም ቀድሞ ወደነበርሁበት ወደ ውጭ አገር ሹመቴ እንደገና ለመመለስ የሚያስፈልገኝ ስለሆነ ተመልሼ ሄድሁ። ከስድስት ዓመት በኋላ ግን በጭራሽ ወደ ሀገሬ መጣሁ። በመጣሁም ጊዜ ለኢትዮጵያ ልማትና ለሕዝባቸው ጤንነት በትጋት የሚያስቡ ለሥልጣኔ ሥራ መሪ የሆኑ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንን የመጽሐፍ ማተሚያ መዘውር ከዩሮፕ አስመጥተው የማተሚያ ቤት አሠርተው ሥራው በኢትዮጵያውያን ልጆች እጅ ሲሠራ አይቼ በብዙ ደስታ አደነቅሁ። በአማርኛም ቋንቋ የተተረጐመው ጅዖግራፊ በዚሁ ባቆሙት ማተሚያ ቤት እንዲታተም ፈቀዱልኝ። ነገር ግን ጅዖግራፊው የተተረጐመው ከትልቁ የዩሮፕ ጦርነት አስቀድሞ ነበርና እንደገና ሊታረም የሚያስፈልግ ሆነ። ይህንም ለማረም ምሁር የሆነ ወዳጄ አቶ መርስዔ ኀዘን በትዕግስትና በልበ ፈቃድ ከእኔ ጋር በማረም ረዳኝ። ቀጥሎም መጽሐፉ ሲታተም ግድፈቱን እያረመ አሳተመልኝ። ይህን*

[183] የኅትመት መኪና።

*የመሰለ እርዳታ ባላገኝ ኖሮ ይህ የጅዖግራፊ ትርጉም ወደ ፍጻሜም ባልደረሰ ነበር። ስለዚህ ለሁሉም ከልብ የሆነ ጥልቅ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡*

የሚል ነው።



የዓለም

ጅዖግራፊ

በአማርኛ


በሐኪም ወርቅነህ

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ እንደራሴ ተፈሪ መኰንን

8 በ1920 ዓ.ም. የታተመው የዓለም ጅዖግራፊ መጽሐፍ



እኔም ለዚህ ሥራ ያደረግሁትን ትጋትና ድካም ሳስታውሰው አሁንም የሕሊና ደስታ ይሰማኛል።



ይድረስ፡ከልጄ፡ከወዳጄ
ከቶ፡መርስዔ፡ኀዘን፡ወልደ፡ቂርቆስ፡
ስለ፡ጠየቁኝ፡እኔ፡ከጻፍሁት፡ከአማርኛው፡የዓለ
ም፡ጂዖግራፊ፡በመላው፡ሆነ፡በክፍሉ፡ለመጻፍ፡ብ
ትፈልግ፡የመጻፍን፡የማሳተም፡መብት፡በመልካም፡
ፈቃዴ፡ሰጥቼሃለሁ። አሁንም፡የሚጠቅመውን፡
መልካም፡ሥራውን፡ሁሉ፡ለመፈጸም፡ብርታትን፡እ
ንድሰጥኽ፡እመኝልሃለሁ።—
አዲስ፡አበባ፡ሰኔ፡፩ቀን፡፲፱፻፵፫፡ዓ፡ም፡
አዛዥ።

9 ሐኪም ወርቅነህ የጅዖግራፊውን መጽሐፍ የማሳተም መብት ለታሪክ ጸሐፊው የሰጡበት

## በትምህርት ቤት ስለተደረገ ሥነ በዓል

የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ለተማሪዎችና ለአስተማሪዎች ስለ ዕረፍት ተዘግቶ ሦስት ወር ከቈየ በኋላ ጥቅምት 1 ቀን 1920 ዓ.ም. ረቡዕ ሲከፈት ሥነ በዓል ተደረገ። ተማሪ ቤቱን ለመክፈት ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ ከመኳንንት ጋር ከቀኑ በ10 ሰዓት መጥተው ነበርና ተማሪዎች ተሰልፈው መዝሙር እየዘመሩ ተቀበሏቸው። ከዚያም በኋላ አዲስ ዲሬክተር ሙሴ ቶማሲኒ በልዑል ፊት ቆሞ ንግግር አደረገ። ከእርሱም ቀጥሎ አቶ ኤፍሬም ተወልደ መድኅን ከዚህ በታች ያለውን ቃል ተናገሩ።

*ልዑል ሆይ፣*
*የተማሪ ቤቱ ሹም ክቡር ሐኪም ወርቅነህ ወደ አውሮጳ አገርና አሜሪካን አገር ተልከው ስለሄዱ በዛሬ ቀን እመካከላችን ባለመዋላቸው እያዘንሁ፣ በእርሳቸው ስምና በሙሉ በተማሪ ቤቱ ስም ሆኜ ተማሪ ቤታችን ከዕረፍት ወራት በኋላ በሚከፈትበት በዚህ ቀን በመምጣታችሁ የተገባ ምስጋናችንን ላቀርብላችሁ እለምናለሁ። ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለተወደደችው አገራቸው ከሚያስቡላት ትልልቅ አሳቦች*

*አንዱ ኢትዮጵያ በትምህርትና በእውቀት ከፍ እንድትል ስለሆነ ይህን ተማሪ ቤት በብዙ ኪሣራ አቋመው ሲያበቁ እያደገና እየሰፋ እንዲሄድና የበለጠ ተማሪዎች ሊማሩበት ፈቃዳቸው ስለሆነ ይኸው አዲስ የመማሪያ ክፍሎችን ያሠራሉ፤ የትምህርቱንም ሥራ እንዲስፋፋ ብለው አዲሶች የፈረንሳዊና የእንግሊዝ አስተማሪዎች ለማስመጣት ስለተላላኩ ከትንሽ ቀን በኋላ ይገባሉ ብለን እንጠብቃለን:: ደግሞም የቋንቋዎች ትምህርት ብቻ አይበቃም ብለው የኢትዮጵያ ልጆች የእጅ ሥራና ጥበብ እንዲማሩ ብለው በዚህ ተማሪ ቤት ግቢ ውስጥ የእጅ ጥበብ ሥራዎች መማሪያ ቤቶች አቋመዋል::*

*ልዑል ሆይ፣*

*ሰው ለሚደክምበት ነገር ሁሉ ዋና ተስፋው የድካሙን ፍሬ ለማየት ነውና በዚህ በተማሪ ቤትዎ የሚማሩ የኢትዮጵያ ወጣቶች በብልህነታቸውና በትጋታቸው ባለ ተስፋዎች መሆናቸውን አረጋግጠልዎ ዘንድ እየለመንሁ፣ ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥት፣ ዕድሜ ለልዕልናዎ፣ ሰላምና ደስታ ለኢትዮጵያ ይሁን እያልሁ እመኛለሁ::*

ከዚህ በኋላ ለመኳንንትና ለአስተማሪዎች የሻይ ግብዣ ተደረገ:: ለተማሪዎቹም ጣፋጭ ምግብ ታደለና የትምህርት ቤቱ መከፈት ሥነ በዓል ተፈጸመ::

## ሐኪም ወርቅነህ ከአውሮጳ ስለመመለሳቸው

ለመንግሥት ጉዳይ ተልከው ወደ አውሮጳና ወደ አሜሪካ ሄደው የነበሩት ሐኪም ወርቅነህ በታኅሣሥ 7 ቀን ጅቡቲ እንደሚደርሱ ስለተሰማ ብዙ ሰዎች እስከ ጅቡቲ ወርደው ተቀበሏቸው:: እኔም የፍቅርና አገልግሎት ማኅበር ዋና ጸሐፊ ስለሆንሁ ከምክትል ፕሬዜዳንቱ ከአቶ ክበረ ኃይለ ሥላሴ ጋር ጅቡቲ ወርደን ተቀበልናቸው:: ከዚያም ተመልሰን አዋሽ ጣቢያ ባደርንበት ቀን ስለ ሐኪም ወርቅነህ ክብር ለብዙ ሰው ትልቅ የራት ግብዣ አደረግን:: በሻምፓኝ ጊዜም አቶ ክበረ፤

*ክቡራን ሆይ፣ የፍቅርና አገልግሎት አለቃ ክቡር ሐኪም ወርቅነህ ሆይ፣*

*ስለ ሀገርዎ ስለ ኢትዮጵያ ክብርና ለእኛም ለልጆችዎ ታላቅ የሆነ የደስታ ምልክት ነው:: ይህች ማኅበር የቆመችበት ጊዜያት ምንም ቅርብ ቢሆን ሥራዋን ከጀመረች አንሥቶ እስከ አሁን ድረስ በልዑል አልጋ ወራሽ ትጋት በርስዎ በአባታችን ብርታት እነሆ 700 የሚያህሉ ባሮች ነፃነትን ተቀብለው ደስ ብሏቸው ይኖራሉ::*

*ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አገርዎ የምትወነጀልበትንና[184] መንግሥትዎ የምትከሰስበትን በዛሬ ዘመን የተናቀውን ሁናቴ ለማስወገድ ዘወትር አሳባቸው ስለሆነ በባርነት ተይዘው የነበሩት ወንድሞቻችን ነፃ እንዲወጡ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የሰጠው ደንብ ስለተፈጸመ፣ ወደ ሀገራቸው ለመግባት ያልፈቀዱ ባሮች እንደገና መንገላታት እንዳያገኛቸው ይህ ማኅበር ተቀብሎ ያሳድጋቸዋል:: በአዲስ አበባም በየስፍራው የተቀጠሩት ከ4 ሺህ በላይ ደርሰዋል:: ስለዚህ ይህች ማኅበር በሁለት ዓመት ውስጥ ይህን መልካም እርምጃ የሠራች እስከ አምስት ዓመት ፈጽማ ወደ ሌላ አገልግሎት የምትራመድ ናት ብለን ተስፋችን የተስፋፋ ነው:: ሐኪም ወርቅነህ ለዚህ ሁሉ ሥራዎ መንፈሳዊ ኩራት ይገባዎታል:: የምንወዳቸውን ወንድሞቻችንን ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅንና ልጅ ቴዎድሮስ ወርቅነህን፣ እርስዎን አባታችንን አቅፎ ደግፎ የመለሳችሁን አምላካችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን እረጅም ዕድሜ ሰጥቶ የተጀመረው አዲስ ሥርዓት እየሠሩ ሄዶ ቀድሞ እንደዚህ ነበር ለማለት ያብቃን*

ብሎ ተናገረና ተጨበጨበለት:: ከዚህ በኋላ ሐኪም ወርቅነህ፤

*ክቡራን ወንድሞቼና ልጆቼ፣*

*በእናንተና በእኔ መካከል ያለውን ፍቅር ለማስረዳት ስትሉ ዛሬ በተደረገው ግብዣና አገራችሁን ለማገልገል በተነሣችሁበት አሳብ ላመሰግናችሁ ላበረታታችሁ እወዳለሁ:: ዛሬ እኔንና ከእኔ ጋር የመጡትን የመንገድ ጓደኞቼን ይልቁንም የጀርመን መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትርን ከነሚስታቸው በመጋበዛችሁ ጥልቅ ምስጋናዬን አቀርባለሁ:: እንዳላችሁት ሁሉ ኢትዮጵያ ነፃነቷን በጥንቃቄ ጠብቃ የቆየች መንግሥት ናትና አገሩን የሚወድ ክርስቲያን ከአእምሮው ተማክሮ መልካም አገልግሎት ቢያደርግ ከመመስገን በቀር ጉዳት የለበትም:: አሁንም ወደፊት ለግርማዊት ንግሥታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን እረጅም ዕድሜ እየተመኘን ያሰባችሁትን አስፈጽሞ ተፋቅረን ኢትዮጵያን አቅፈን ለመኖር ያብቃን::*

ብለው ተናገሩና ተጨበጨበ::

በግብዣው ላይ የነበሩት የውጭ አገር ሰዎች ሲሆኑ ከኢትዮጵያውያንም እልፍኝ አስከልካዩ ግራዝማች ለጥ ይበሉና አቶ ዮሐንስ (የጀርመን ትርጁማን)፣ አቶ ተድላ አበባየሁ ነበሩ::

ሐኪም ወርቅነህ በታኅሣሥ 10 ቀን አዲስ አበባ ሲገቡ ብዙ መኳንንት ሳጋር ላይ ጠብቀው ተቀበሏቸው:: ተማሪ ቤቱን የሚያስተዳድረው አቶ ያሬድም በተማሪ ቤት ያሉትን ነፃ የወጡትን ባሮችና የድኾች ልጆች መብራት አስይዞና አስልፎ በመዝሙር ስለተቀበላቸው በአቀራረቡ ተመሰገነ::

ሐኪም ወርቅነህ በሁሉ ዘንድ ተወዳጅ ስለሆኑ በዚህ ወራት በየስፍራው ስለ እርሳቸው ክብር ግብዣ ሲደረግ ሰነበተ:: ለምሳሌ የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት አስተማሪዎችና ተማሪዎች በታኅሣሥ 12 ቀን ብዙ የውጭ አገር ሰዎችንና መኳንንትን ለግብዣ ጠርተው ስለ እርሳቸው ክብር በዓል አደረጉ:: በዚህ ጊዜ አቶ ኤፍሬም ተወልደ መድኅንና ሌሎች ሰዎች ንግግር አደረጉ:: ሐኪም ወርቅነህም መልስ ሰጡ::

[184] ኢትዮጵያ ዓለም ማኅበር (League of Nations) ልትገባ ስትሞክር ባሮችን በተመለከተ የቀረበውን ውንጀላ የሚጠቅስ ነው::

## ስለ ፍቅርና አገልግሎት ዓመታዊ በዓል

የፍቅርና አገልግሎት ማኅበር ታኅሣሥ 17 ቀን ሰኞ በፕሬዜዳንቱ በሐኪም ወርቅነህ ቤት ትልቅ ግብዣ አድርጎ የሁለተኛ ዓመት በዓሉን አከበረ። በዚህ ጊዜ ፕሬዜዳንቱና ምክትል ፕሬዜዳንቱ ሌሎች አባሎች ንግግር አደረጉ። ሐኪም ወርቅነህ የሥራውን ፍሬ በንግግር የገለጹት ስለሆነ ዲስኩሩን እነሆ ጽፌዋለሁ።

የሐኪም ወርቅነህ ንግግር።

*ክቡራን ወዳጆቼና ወንድሞቼ ማኅበራችን የተመሠረተበትን ሁለተኛውን ዓመት ለማክበር ሁላችሁም ከዚህ ተሰብስባችሁ በማየቴ ብዙ ደስ ይለኛል። ባለፈው ዓመት ስለ አገራችን አገልግሎት ነፃ የወጡ ባሮችንና ድኾች ልጆችን ከፊተኛው ዓመት ይልቅ ብዙዎች ሰብስበናል። በፊተኛው ዓመት 4 ሴቶችና 12 ወንዶች ልጆች ነበሩ። አሁን ግን 13 ወንዶች ልጆች ሆነዋል። እነዚህም የአማርኛ ንባብና ጽሕፈት ሸማኔነትና መኪና ስፌት እንዲማሩ አድርገናል። ሴቶቹም የቤት ሥራና ፈትል ይማራሉ።*

*ካሰባሰብናቸው ልጆች ዓሥራ ዘጠኙ ሥራ እያገኙ በፈቃዳቸው ሄደው አሁን ያሉት የምናሳድጋቸው 25 ናቸው።*

*ጌታችን ልዑል አልጋ ወራሽ በሰጡን ቦታ ላይ የተጀመረው የተማሪ ቤቱ ሥራ በቶሎ ተፈጽሞ ልጆቹን ከዚያ አግብተን ሥራችን እንዲከናወን ተስፋ አደርጋለሁ። አሁን ሁሉን ቤት ለመሥራት የሚበቃን ገንዘብ የለንም። ግን ሥራችን እግዚአብሔር የሚወደው ስለሆንና አገራችንንም የምናገለግልበት ስለሆነ ገንዘብ ለማግኘት እግዚአብሔር እንዲረዳን ተስፋ እናደርጋለን።*

*ባለፈው ዓመት የማኅበርተኞቻችን ቍጥር 40 ነበር። አሁን 64 ሆናአል። ቍጥራችን እንዲህ እየበዛ በመሄዱ የአገራችን ሰዎች ሥራችንን እንደ ወደዱትና ደስ እንዳላቸው ያስረዳል።*


*የማኅበራችን አሳቡና ምኞቱ እንደ ሌላ ማኅበር እንዳይደለ አዲሶቹ ወዳጆቻችንና ማኅበርተኞቻችን በጣም ማወቅና ማሰብ ይገባቸዋል። የማኅበራችን ትምክህት (አርማ) «ሌላ ሊያደርግልህ የምትወደውን አንተም ለሌላው አድርግ» ነው። መለዮቻችንም እንደምታውቋቸው ሃይማኖት፣ ቅንነት፣ ነፃነት፣ እውነት፣ ንጽሕና፣ ፍቅር፣ አገልግሎት ናቸው። እነሆ የማኅበራችን አሳቡና ምኞቱ ከሌላ ልዩ እንደሆነ በዚህ ይገለጻልና ማኅበርተኞች ሁሉ አካሄዳችንን በነዚህ ቃላት ልናደርግ ይገባናል። ወደዚህ ማኅበር መግባታችንም ለየራሳችን ጥቅም ሳይሆን የምንወዳትን የአገራችንን ነፃነት ለመጠበቅ ነውና ይህንኑ አሳባችንን ለመፈጸም እግዚአብሔር እንዲረዳን እለምናለሁ።*

*ይህንንም በዓላችንን ያሰናዱልንን ሁሉ በማኅበሩ ስም አመሰግናለሁ።*

*ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለልዑል አልጋ ወራሽ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን።*

የማኅበሩ ጽሕፈት ቤትና የተማሪ ቤቱ ጥበቃ የበላይ ኃላፊነት በእኔ ላይ ስለሆነ ከመንግሥት የተሰጠውን ቦታ ለመመራትና ድንጋይ ለማስፈለግ በመመላለስ ብዙ ድካም አገኘኹ። ቦታው በትንሹ አቃቂ ዳርቻ ነው። በዚህ ሥራ ላይ የማኅበሩ አባል ፊታውራሪ ገብረ ማርያም በብዙ ረድተውኝ ነበር።





32 በልዩ የቆመ ትምህርት ቤት (ነፃ ለወጡ ባሮችና የድኾች ልጆች)



33 የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች